ጣራ ሥር ባለ ቆጥ ላይ የሠፈሩ የሩብያ አራት አውራ ዶሮዎች ደግመው ደጋግመው “ ኩኩሉ! ኩኩሉ! ” እያሉ የሰሚዎቻቸውን ጆሮዎች እስኪያደነቍሩ ድረስ ጮኹ።

“ ዛሬ ወፍጮውም መቅረቱ ነው! ጨዋታችንን ይዘን ስንደልቅ፣ ለካስ ሌሊቱ ሊነጋ ተቃርቦ ኖሯል! ” አለች ሩብያ። ባሏም ከመቀመጫው ተነስቶ ከቤታቸው ውስጥ በስተቀኝ በኩል ካለው ሰፊ የመኝታ ደረቅ መደብ ላይ፣ ድርቆሽ ሣር ይጐዘጉዝ ጀመር።


“ እኛ ቤት ይኸውላችሁ፣ የንጨት አልጋ እንኳ የለንም አለ! ” እንግዶቹን ይቅርታ እየጠየቀ።

“ የሁላችንም ያው መደብ ነው ” አለች ሁለተኛዪቱ እንግዳ። በየቅል የያዙትን ጠላቸውን ሁሉም ጨላለጡና ኬሻ ብቻ በለበሰ የመደብና የድርቆሽ መኝታቸው ላይ ክልትው አሉ።

በማግስቱ ሁለቱ እንግዶቿ ወደ ስብሰባው ሲያመሩ፣ ሩብያ ሌሊት ያለፈበትን ወፍጮዋን ተያያዘችው። በቀበሌያቸውም ስብሰባው ባስከተለው ጦስ፣ ብዙ ሰዎች ተጋደሉ፣ ብዙ ሰዎች ተፋቱ፣ ብዙ ሰዎች ታሠሩ። በየት አምልጠው እንደሔዱ አይታወቅም እንጅ፣ እነዚያ የመጀመሪያውን የስብሰባ ዱብ ዕዳ ገፈት የቀመሱ ሁለት የሩብያ እንግዶች፣ ጂቡቲ ገብተው ” ሴተኛ ኣዳሪ ” ከሆኑ መንፈቅ አልፏቸዋል። ሩብያና ባሏም፣ “ ስብሰባውን ንቆ ባለመካፈልና፣ የሴቶችን እኩልነት መብት በማርከስ ” በተሰኙ ሁለት የወንጀል ዐይነቶች ተከሠው፣ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ፣ ከሚኖሩበት ቀበሌያቸው ወደ አውራጃው ዋና እሥር ቤት ተወስደው፣ ያለፍርድ ከታሠሩ፣ ይኸው ሁለት መስቀሎችን ተኩሰዋል።



# “ ዘሊባኖስ ”



መፈጠሬ ብቻ ፣ አርጎኝ ወንጀለኛ፣
ስማቅቅ ኖሬአለሁ ፣ ሆኜለት እስረኛ!

(የጠፍ. ቁ.7)

# መንደርደርያ

በዓለማችን፣ እላይ ያለው ወደ ታች ላለመውረድ፣ እታች ያለው ወደ ላይ ለመውጣት ሲሉ፣ ትግል በየመልኩ ይካሔዳል። አንዱ ክፍል ጉልብቶ ድል ያገኘ እንደሆነ፣ ምርኮኞውን በእግሩ ስር ረግጦ አፈር ሲያስግጠው ይኖራል። ተረጋጩም ክፍል ተራ ደርሶት ድል ሲመታ፣ ሲረግጠው የኖረውን ድባቅ ይመታል። በነዚህ የትግልና የድል ለውጦች መካከል፣ ምንም ዐይነት ለውጥ ሳይኖረው፣ በነባርነት የሚገኝ፣ በምርኮኛነት የሚማቅቀው ክፍል፣ የሚታሠርበት እሥር ቤት ብቻ ነው። ሰው ነኝ የሚለው ፍጡር፣ ሰብዓዊነት በተለየው የሚያሠቅቅ ሁኔታ፣ ድል በማግኘቱ ብቻ፣ ጠላቴ ነው ብሎ ያመነበትን መሰሉን ፍጡር፣ እንዲያ በሚያሰቅቅ ወህኒ ቤት አሽጉግፍና ደባ ሲፈጽምበት ከማየት የከፋ ሌላ ነገር አይኖርም። በተለይም የሰው መብትና ክብር እንዲጠበቅ፣ በየትኛውም ክፍለ ዓለም፣ የእሰጥ አገባው ክርክር በጦፈበት ዘመን፣ ያገራችን የዓለም በቃኝ እሥር ቤት በዚያ ሁኔታ ዛሬም መገኘቱ ያስደንቃል። ምናልባት የዓለም በቃኝን ውስጣዊ ሁኔታና አሠቃቂነት የማያውቅ ቢኖር፣ ዘሊባኖስን ያዳምጥ!

“ (141) (10) (67) (98) (48) ”

---

“ ዓለም በቃኝ ” ብለው ይጠሩታል። በመላው አፍሪቃ በጠቅላላ ይዘቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት፣ የትልቁ ወህኒ ቤት አንደኛው ክፍል ነው። በመናገሻ ከተማይቱ ምዕራባዊ ዳርቻ ላይ ይገኛል። የሕንፃው መሠረት የተጣለው በአፄ ምኒልክ መቅድማዊ ዘመን ላይ ሲሆን፣ እንዲያ አርገው የነደፉትና ያነፁት ግን የፈረንሣይ መሐንዲሶች ናቸው ይባላል። ከው ስጡ ገብቶ ያየው ሰው ቊጥር ይነስ እንጅ፣ “ ዓለም- በቃኝ ” የሚል ስሙን የማያውቅ በመላው ምድረ-ኢትዮጵያ አይገኝም። ከቶውንም፣ ይህ ገናና ስሙ፣ የሃገሪቱን ድንበር ቆርጦ፣ የዓለም ታሪክ ፀሐፊዎችና ጋዜጥኞችን ብዕሮች እንዳሠለቸ ይነገር ለታል። ይህ ሕንፃ በመጀመሪያ ላይ ሲታነፅ፣ ለምን አገል ግሎት እንዲውል እስከዛሬ ድረስ ያልተጣራ ቢሆንም፣ ባለፈው ረዥርም ዘመኑ፣ “ የነፍሰ ገዳይና የከፍተኛ ወንጀለኞች ” ማጐ ሪያ ጉረኖ ሆኖ ሲያገለግል ኖሯል።

ከአንድ አግጣጫ ላይ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ አግጣጫ ዎች አንፃር ሲያዩት ተመሳሳይ ቅርፅ አለው። አውቀው የገለበ

ጡት በርሜል ይመስላል። ካለአንድ በር በስተቀር፣ መስኮት
የሚሉት ነገር ለምልክት ያህል እንኳ አይታይበትም። ልሙጥ
ምልምሉን የቆመ ነው። “ አያድርግብዎትና ” እውስጡ
ቢገቡ፣ ደመና ከጐረሠ ሰማይ በስተቀር ምንም ነገር ሊያዩ
አይችሉም። የሕንፃው ተንቀዋሎ በረዥሙ መሠራት ለተን
ቀሳቃሽ ትኩስ አየር ወደ ሕንፃው የመግባት ዕድል አይሰ
ጥም። ይህም በመሆኑ፣ እውስጡ ያለው መከረኛ ፍጡር፣
ምንጊዜም በተቃጠለ ዐየር እንደታጀለ ነው። ስለዚህም ነው
በውስጡ የሚኖሩት እሥረኞች ሁሉ፣ ከመጠን በላይ ገርጥተው
ትኰስ ገመምተኛ የሚመስሉት። በተቃጠለ አየር ከመታጀል የተ
ነሳ፣ አንዳንዱን እሥረኛ ዘመዶቹ ሳይቀሩ፣ ሊለዩት የማይችሉበት አጋጣሚ አለ። የዐየሩ አፈና እንደ አራቱ የዐመት ወቅ
ቶች የዐየር ጠባይ፣ በሙቀትና በቅዝቃዜ መካከል ቅይር ባሕርይ
ስለሚያሳይ፣ አብዛኛውን እሥረኛ ጤና ቢስ ያደርገዋል። ይህ
ሕንፃ ባለ አንድ ፎቅ ሆኖ የተሠራ ሲሆን፣ በጣም ጠባብ
የሆኑ፣ ከግማሽ መቶ በላይ ክፍሎችን ይዟል። በብረት በሮቻ
ቸው የታሸጉት እነዚህ ክፍሎች፣ ሁለት ሰዎች አጣበው ማስቀ
መጥ ቢችሉ ነው። ግን ከስድስት በላይ ያጉሩባቸዋል። ፎቁ፣
ዳር ዳሩን የብረት አሸንዳ ያጠረው፣ ባለግማሽ ሜትር ስፋት
በረንዳ አለው። ከክቡ ሕንፃ መካከል፣ አንዲት ጩምባሳ ፊን
የምትል ውሃና፤ ክብ የሆነች የሲሚንቶ መስክ አለች። ያ ሁሉ
እሥረኛ ተራ ሲደርሰው፣ ከሚቆለፈው የክፍል ጉረኖው
ውስጥ ወጥቶ ለተወሰኑ ደቂቃዎች የሚዝናናው በዚችው
ደረቅ የሲሚንቶ መስክ ላይ ነው። አበባ ቀርቶ፣ ርጥብ ቅጠ
ልና ለምለም ተክል እሥረኛውን የሚናፍቁት፣ እነሱን ማግኘት
ቀርቶ ማየት እንኳ ከማይችልበት ከዚህ ደረቅ አካባቢ በመኖሩ





ነው። ምዕራብም ሆነ ምሥራቅ ወይም ሰሜን ሆነ ደቡብ፣
ተገላምጦም ሆነ ተንጠራርቶ ባለው አቅም ሁሉ ቢሞክር፣
የተስፋና የሕይወት ምልክቶች የሆኑትን ለምለም እፀዋት ማየት
አይሆንለትም። ከተራው ፍላጎቶቹ ታግዶ በእሥር ላይ የሚኖር
ሁሉ፣ ዐለም በቃኝ ውስጥ እስካለ ድረስ፣ ከፍተኛ ትዝታ ከሚፈ
ጥሩበት ነገሮች አንዱ፣ መታየት እንኳ ያልተቻሉት እፀዋት
ናቸው። እነዚያ የፈረንሣይ ቅኝ ገዥዎች “ ምን ይሆነን ”
ብለው እንደሠሩት ባይረጋገጥም፤ ግዛታቸውን ለሚቃወም የነ
ፃነት ታጋይ ማሠቃያ ምሽጋዊ ዋሻ እንደነበረ፣ ሁኔታውን ያየ
ሁሉ ይፈርዳል።

ለዚያ ሁሉ እሥረኛና ለዚያ ሁሉ ክፍል፣ ያለው ሽንት
ቤት አንድ ብቻ ነው። ተራ ሲጠብቁ የወጠራቸው የሚያመ
ልጣቸው ታይተዋል። የሽንት ቤት እንደፈለጉት ለማግኘት፣
የጉቦው ሥርዓት የሞቀ ነው። ሌላውንማ ጥቁር ገበያ አለማ
ንሳቱ ይሻላል። እጅግ የጦፈ ነው። በዚሁ የደራ ገበያ፣ ነባር
እሥረኞችና ፖሊሶች፣ ሁለትና ሦስት የቪላ ሕንፃዎች አሠር
ተው በሺ ብር ያከራያሉ። ሲጋራ ማጨስ ቀርቶ፤ ይዞ መገኘት
እንኳ በሚያስቀጣው በዚያ የዓለም በቃኝ ልዩ አካባቢ ውስጥ፣
የተራው ግሥላ አንዷ ቀጠና ሲጋራ እንኳ የምትሸጠው በአ
ንድ ብር ነው። እንግዲህ አንዷን በ አስራ አምስት ሳንቲም
ገዝቶ ያስገባ ፖሊስ፣ ኻያ ብር ነግዶባት ይወጣል ማለት ነው።
ከሌሊት ልብሱና ከቀን ልብሱ በስተቀር፣ ምንም ነገር ይዞ መግ
ባት በማይፈቀድበት ዐለም በቃኝ ውስጥ፣ የጥቃቅን ምጢጢ
ሬድዮኖች ገበያ ሳይቀር የደራበት በመሆኑ፣ ዐለም በቃኝን የተ
ለየ መልክ ከሚሰጠው ባሕርዩ አንዱ ነው። የዚያንው ያህል፣
ብጫቂ ወረቀት የተገኘበት ኩታራ እሥረኛ፣ ወንጀል ሠርተ

ሃል ተብሎ፣ ሲቀጠቀጥ የሚውልበት ቦታ ነው።

ይህ አሠቃይነቱ የተለየና በመከራ ቦታነቱ ከፍተኛ ዝናን ያተረፈ ይህ እሥር ቤት ባጠቃላይ ሦስት የተለያዩ ክፍሎች አሉት። እነዚህም ክፍሎች በሦስት የተመደቡት እንደ እሥረኛው የወንጀል ይዘትና እንደሚበየንበት የፍርድ አፈጻፀም ዐይነት ነው። እነዚህም ክፍሎች፣ ቀጠሮኛ፣ ፍርደኛና ሞት ወይም ዕድሜ ልክ እሥራት በመባል የተሠየሙ ናቸው። የመጀመሪያው፤( ቀጠሮኛ ክፍል ) አንድ ሰው በፍርድ ቤት ተከሶ፣ ፈፅሟል የተባለው ወንጀል በዋስ የማያስለቅቀው ሲሆን፣ የፍርድ ውሣኔ እስኪሰጠው ድረስ፣ በቀጠሮ የሚቆይበት የመታሠሪያ ክፍል ነው። ዳኞቹማ የሚጠሩት "ማረፊያ ቤት" ብለው ነው። በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው፤ እስከ ሰባትና ስምንት ዐመታት በቀጠሮ ነገሩ ሲጐተት ኖሮ፣ በመጨረሻ ላይ፣ እነዚያ ምናምንቴ ዳኞች "የተከሰስክበት ወንጀል በሚገባ ሲጠና ቈይቶ በቀረበው ማስረጃ ረገድ፣ የተባለውን ወንጀል ያልፈጸምክ መሆኑ አሁን ስለተረጋገጠ፣ ፍርድ ቤቱ እስከዛሬ ድረስ የታሠርከው ያላግባብ በመሆኑ እያዘነ ይቅርታ በመጠየቅ፣ በነፃ መለቀቅህን ያረጋግጣል" የሚሉት ቀልድና ፌዝ ነው። ለረዥም ጊዜ ባልፈፀመው ወንጀል ተከሶ፣ በዚያ የሚያሠቃይ እሥር ቤት ውስጥ መከራውን ሲጠብስ ኖሮ፣ በንፁህነት የሚወጣው ወንጀለኛ ቊጥር ብዙ ነው። ገድለሃል ያሉት ሰው፣ መቀበሩ ሣይቀር በሦስት ምስክሮች የተረጋገጠለት ሟች፣ ከሦስት ዐመት በኋላ፣ ከነሙሉ ጤናው በሕይወት እየተገኘለት በነፃ የሚወጣው " ወንጀለኛ " ቊጥር ትንሽ አልነበረም።

ይህ " ቀጠሮኛ ቤት " የሚጠጡት ውሃ እንኳ እንደ ልብ የማይገኝበት የማሠሪያ ክፍል ነው። ከቤቱ መጥበብና ከእሥረኛው ብዛት የተነሣ፣ እግር ዘርግቶ ለመቀመጥ እንኳ አይቻልም። ለመተኛትማ የማይሞከር ነው። አንድ እሥረኛ ከተወሰነለት ሰዓትና ተራ በስተቀር፣ ውጭ ወጥቶ ፀሐይ መሞቅ አይፈቀድለትም።አብዛኛውን ጊዜ ግን፣ በዚያ ቅጥ የለሽ ቤት ውስጥ ታፍኖ መቀመጥ ነው። ከሰው ብዛትና ከዓየሩ መቃጠል የተነሣ ትንፋጉ አይጣል ነው። ምሣና ራት ብለው በነፍስወከፍ የሚያድሏት ድቡልቡል ቂጣ፣ በዓለም ለታወቀ ከፍተኛ ኤግዚብሽን፣ ለላንቲካ የምትቀርብ ትንግርት ነበረች። ከምን ዐይነት እህል እንደምትሠራ አይታወቅም። እንክርዳድና ጓያ ያሉባት መሆኑ ግን፣ የበላት ሰው ሁሉ ወዲያውኑ ራስ ምታት ሲለቅበትና ሲያዞረው፤ ለመነሣትና ለመቆም የሚሞክረውንም፣ ሲያጥወለውለውና ሲያንገዳግደው ማየቱ ምሥክር ይሆናል። የሚገርመው ደግሞ፣ እሁድ በመጣ ቊጥር እንጀራና ሥጋ ብለው የሚያድሉት ትርኪ ምርኪ ነው። የጤፍ ነው የሚሉት እንጀራ ገና ግቢውን ሲገባ፣ አፍንጫ ይሰነፍጣል። ከምላስ ጋርማ ሲገናኝ አቤት ያለው ምሬት። ገና መልኩን ሲያዩት፣ የሚታይበት ጥቁረት አስቀድሞ የመብላት ፍላጐትን ይዘጋል። የሸመጠረ ምናምን፣ ግግር እንጀራ ነው ብለው ሲሰጡ፣ ይታዘቡናል ብለው አለማሰባቸው ያሳዝናል። ሥጋዋማ የፈገፈጉባት ላጺስ ትመስላለች። ምን መምሰል ብቻ፣ ታህላለችም። ከምን ዐይነት ከብት (እንስሳ) ቆርጠው እንዳመጧት ማን ያውቃል? ከብትኮ ባለቀንዳምም ባለጋማም ነው። የዚያ ቤት አራጅ፣ ሠኰናም አይመለከት ይሆናል። ያ መከረኛ እሥረኛ በዚያ ቀጠሮ ቤት፣ ይህን አይነት ምግብ እየበላ፣ ቀኑን ውሎ በመሸ ቊጥር በነባር እሥረኞች፣ የሻማ ፍራንክ አምጣ እየተባለ በመደብደብ ይኖራል። ከዚህም የተነሣ የስኳር አራጣ የሌለበት የለም።

ትንሽ የተሻለ ይዞታ አለው የሚባልለት ሁለተኛው ክፍል ነው። “ ፍርደኛ ቤት ” ይሉታል። ለዐመታት በቀጠሮ ሲማቅቅ ኖሮ፣ እንደወንጀሉ ዐይነት ፍርድ ተሰጥቶት፣ ለተወ ሰኑ ዐመታት የሚኖርበት ክፍል ነው። ከዕድሜ ልክ እሥራት በታች ለተወሰኑ ዐመታት የተፈረደባቸው ሰዎች የሚኖሩበት ምድብ ቦታ ነው። በሣምንት ሁለት ቀናት ያህል፣ ከቤተ-ሰቡ ምግብ ሊገባለት ስለሚችል፣ ረዳት ያለው፣ ብዙ የምግብ ችግር አይገጥመውም። እስከዚህ ንፁህ ነው ባይባልም፣ መለስተኛ መሻሻል በመኝታውም ሆነ በቤቱ ይዞታ ላይ ይታያል። እንደ ፈሰሰው ላብ መጠን፣ አይከፈለውም እንጅ፣ እንደሙያው ዐይ ነት ጊዜ የሚያሳልፍበት የትንሽ ሰዓቶች የሙያ ሥራ ይሰጠ ዋል። “ ጥቁር ገበያ ” እጅግ የደራበት ክፍል ይኸኛው ነው። በሕልማቸው የሚመጡባቸውን ሴት ወዳጆች ለማግኘት እስከመቻል ድረስ፣ በልዩ ዘዴ ከተማ ደርሰው የሚመጡ፣ የእ ሥር ቤት መሣፍንት ቍጥር ጥቂት አልነበረም። ይህን ለማስ ፈፀም የሚከፈለው የዲናር መጠን ግን የትየለሌ ነው። በእ ሥር ቤት እንኳ፣ በመደብ መካከል ያለውን የኀብተረ-ሰብ ልዩ ነት የሚያንፀባርቅ፣ ይህን መሳዩ ላላቸው እሥረኞች ብቻ የሚ ከናወን ድርጊት፣ ቍልጭ ያለ ማሳያ ነው። ሦስት አራተኛው የጠቅላላው የእሥር ቤቱ አስተዳደርና ተግባር የሚመራውም ሆነ የሚከናወነው፣ ከብዙ የእሥር ዘመናቸው፣ ታማኝነት ባተ ረፉ ዛሬም በእሥር ላይ በሚገኙ፣ ጮሌ እሥረኞች ነው። እነ ዚህ ብልጣ ብልጥ እሥረኞች “ ጥቁር ገበያ ” ባስገኘላቸው ከፍተኛ ጥቅም የተነሣ፣ ያን ወህኒ ቤት ለዘለዓለም ሊለቁ አይፈ ልጉም። ከፍርድ የእሥር ዘመናቸው በኋላም፣ በዚያው በወህኒ ቤት፣ በእሥረኛነት ስም ሙጥኝ ብለው የሚኖሩ አሉ። ሳያስ





ቡት ያገኙትን ጥቅም ሙጥኝ ብለው፣ እሥረኛው ላይ የሆነ ያልሆነ ምክንያትና ወንጀል በመፍጠር፣ ቤሣ ውለድ እያሉ ሲያሰቃዩት አሉ። እንደነገሩ ላሉት የጊቢው፣ ቤተ ክርስቲያን፣ መስጊድ፣ መጻሕፍት ቤት፣ ለመሔድ እነዚህን አልቅቶች ማስፈ ቀድ ግዴታ ስለሆነ፣ ለጉቦ መብሊያ ሰፊ ዕድል አፍርቶላ ቸዋል። በፍርደኛ ክፍል ኪራይ መክፈል ያስፈልጋል እንጅ፣ ለወጉ ያህል የሚጐረብጥ የንጨት ድርብርብ አልጋም አለ። በተላላኪነት የሚያገለግሉ በጊቢው ውስጥ ዝናን ያተረፉ “ እስኩፒኛዎች” ም ስላሉ፣ ሻይ ቡናም ማለት ይቻላል። ወን ጀል ይበዛ የነበረው ከተማ ውስጥ ሆኖ ሳለ፣ በዚያ እሥር ቤት ውስጥ ከሚገኘው እሥረኛ አብዛኛው፣ ከገጠር የሚመጣ ነበር። ያን መራራ የእ ሥ ር ቤት አሠቃቂ ኑሮ ገጠሬዎች በብ ዛት የሚሠቃዩበት ምክንያት የሚያጠያይቅ ቢሆንም፣ ባጠቃ ላይ ወህኒ ቤቱ፣የሚመጡትን ሰዎች በዚያ የዘቀጠ የኑሮ ደረጃ በማጉላላቱ፣ እሥረኞቹ “ወንጀለኞች” ቢሆኑም፣ ሰዎች መሆና ቸውን የረሳው ይመስላል። በዚህም ኢሰብአዊ ድርጊቱ፣ በታ ሪክ ይጠየቅበታል።

እንደ አውሮፓ ባሉ ሀገሮች የሚገኙ እሥር ቤቶች፣ ለመኖሪያነት ሳይቀር የሚያጓጉ ናቸው። የሚቀርብላቸው ምግብ፣ እያንዳንዱ የቅመም ዐይነት ሳይቀር በሚዛን እየተመዘነ የሚዘጋጅ ነው። የቤቱን፣ የልብሳቸውን፤ የጊቢያቸውን ጊዜ ያዊ ሁኔታ በየጊዜው እየሔደ የሚቆጣጠር፣ ገለልተኛ የተቆ ጣጣሪ ቡድን አለ። ለላው ቀርቶ በየበዓላቱ እሥረኞችን ለማስ ደሰት ሲባል፣ የታወቁ ኦርኬስትራዎች ከእሥር ቤቱ አዳራሽ በመገኘት፣ የዳንስ ምሽት አዘጋጅተው ያዝናኑአቸዋል። በእሥ ረኞቹም ቍጥር ተመጣጣኝ የሆኑ፤ የበጐ ፈቃድና የኪራይ

የዳንስ አጣማጆች በዕለቱ ምሽት ይቀርቡላቸዋል። ለየበዓላቱም
ከተለያዩ ድርጅቶች ልዩ ልዩ ስጦታ ይደረግላቸዋል። የእነዚህ
መሰሉ ሀገሮች የማሠር ዓላማና ግብ፣ ከኛው ዐይነት የተለየ
ነው። የኛው፣ ወንጀለኛውን ለመቅጣት ሲሆን፣ የነሱ ግን
ለማረም ነው። የመቅጣቱና የማረሙ ግብና ዐላማ፣ በሁለቱ
የእሥር ቤቶች ይዞታና ድርጊት ስለሚንፀባረቅ፣ በፍትህ ላይ
ያላቸውን አቋም ለማሳየት ትርጁማን አያስፈልገውም።

ሦስተኛው አስፈሪው የወሀኒ ቤት ክፍል፣ ዐለም በቃኝ
የተሰኘው ነው። ምንነቱን አበጥሮ ለማስረዳት፣ ስያሜው ብቻ
ይበቃል። የመነኑ ባሕታውያን፣ የዚህን እሥርቤት ይዞታ
ቀደም ብለው አላወቁም እንጅ፣ በርግጥ " ዓለም በቃኝ "
ብለው ከእስር ቤቱ ጠቅለው በመግባት፣ እጅግ በጣም ርቀው
ከሚገኙ ገዳማት፣ ዱሮች፣ በረሀዎች ዘንድ ለመመነን ባልቃ
ጣቸው ነበር። ከዛሬ አሥራ አምስት ዐመት በፊት፣ በዚህ የዐ
ለም በቃኝ፣ የማሠሪያ ጉረኖ ውስጥ ቊጥራቸው ከአምስት
መቶ በላይ የሆኑ ነፍሰ ገዳይ እሥረኞችና ጥቂት ከፍተኛ የፖለ
ቲካ እሥረኞች ታጉረው ይኖሩ ነበር። የሲጋራ ሱስ ያለበት
እሥረኛ የግስላ ብጣቂ ጥንባሆ፣ ከላይኛው ከንፈሩ ስር እንደ
ሠረት ለግጦ ሦስት አራት ቀናት ያለንግግር የሚውል እሥረኛ
ማየት፣ ተራው ትርዒት ነበር። እንዲያ መሆኑ፣ የገጠጠ ችግር
ወጥሮ ይዞት ነው። በስንት ሥቃይ በኰንትሮባንድ የሚያገ
ኛትን ሲጋራ ለማጨስ ዕድል አልነበረውም። እሳት በጊቢው
ድርሽ አይልም። እንዳይተወው የሱሱ ኃይል አቅበጥብጦታል።
ታዲያንን ከላኛው ከንፈሩ ስር ጥንባሆውን ለብዶ፣ መናገር
እንኳ አይሆንለትም ነበር። " ነገ ይበቅላል " ብሎ ከዚያ ደረቅ
የሲሚንቶ መናፈሻ ወለል ላይ፣ ብልቱን ቈርጦ የጣለ ወፈፍቱ





እሥረኛ፣ ሌላው አሠቃቂ ትርዒት ነበር። " ሁለተኛ ሞት
አይፈረድብኝም " ብሎ፣ እዚያው የእሥር ጓደኛውን አንቆ የገ
ደለ እሥረኛም እዚያው ውስጥ ጀግንነቱን እየተረከ፣ ሦስተኛ
ለመግደል ይዘጋጅ ነበር። የሥጋ ናፍቆትና አምሮት አስቸ
ግሮት፣ የእሥረኛ ጓደኛውን ፍሬዎች ያኰላሸም፣ ወፈፍቱ
እሥረኛ ታይቷል። " ወንጀላችሁ ተሻሽሎ፣ ፍርዳችሁ ይቀል
ላችኋል " የተባሉ፣ በእሥረኛ ነጭ-ለባሽነት የተመለመሉ
ደግሞ፣ ለስለላ ተግባራዊ ውጤት ያሳዩ ለመምሰል፣ ራሳቸው
ያዘጋጁትን አስወንጃይ ጽሑፍም ሆነ ተንኰል፣ በሌላው
የዋህ እሥረኛ ላይ በመለጠፍ፣ ሲያስደበድቡትና፣ እነማሚቶ፣
እነጅቦ በተባሉ ምሕረት የለሽ የእግር ብረቶችና እግረሙቆች
ሲያስጠፍሩት ማየት፣ በጠቅላላ መፈጠርን ያስጠላል። ከነገ
ዛሬ እገደል ይሆናል እያለ፣ ምግብ መብላት የተሣነው፣ ያ
ሁሉ የሞት ፍርድ እሥረኛ ከክሳቱና ከጥቊረቱ የተነሳ፣ ሌላ
ፍጡር መስሏል። በተለይም ቊጥር 17 በመባል የታወቀው
ያበዱ እሥረኞች መኖርያ ክፍል ውስጥ፣ በየዕለቱ የሚፈፀ
መውን አሳዛኝ ድርጊት መስማትም ሆነ ማየት፣ ሰው መሆን
ከማስጠላት አልፎ፣ የዚያን እሥር ቤት " ዓለም- በቃኝነት "
በርግጥ ያረጋግጣል። ........... በተለይም " የቀይ ሽብር ጊዜ "
የተፈፀመውን ግፍ ሌላ ታሪክ ፀሐፊ ያወራዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይቆይና፣ ያ ሁሉ ሠራዊተ እሥ
ረኛ፣ በሥቃዩ አንፃር ምን ተስፋ ነበረው? ምኞቱስ ምን ለመ
ሆን ነበር? በየቀኑ በሚፈፀምባቸው ግፍና በደል፣ ሥቃይና
መከራ፣ መራራነት የተነሣ፣ እያንዳንዱ እሥረኛ፣ በሃገሪቱ
ውስጥ የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ፣ ከፍተኛ ምኞቱ ነበር።
ከቶውንም ከእሥር ቤቱ ኑሮ ምሬት የተነሳ፣ ከየትኛውም የኢ

ትዮጵያ ሕዝብ ክፍል በዚያ የነበረ እሥረኛ ሁሉ ስር ነቀል ለውጥ እንዲመጣለት ተስፋ ነበረው። ምኞቱና ተስፋው፣ ለውጡ ሲመጣ፣ ነፃ ለመውጣት አስቦ ሳይሆን፣ ባግባብ ለመታሠር ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረው ነው። (ምፀት ባይሆን!)

ይህ ምኞቱ በየሰዓቱ ያጉላላው የነበረ አንድ የ 19 ዐመት ወጣት፣ በዚያን ጊዜ ወንጀለኛ ተብሎ ዐለም በቃኝ ውስጥ በመማቀቅ ላይ እንዳለና፣ የመጣውም ለውጥ፣ በእሥረኛው ላይ የባሰ ሥቃይና ግፍ ይበልጥ የጫነበት መሆኑን የሚገልጽ ምሥጢራዊ ደብዳቤ በዚያው ሰሞን በመገኘቱ፣ የዚህን ደብዳቤ ይዘት መነሻ በማድረግ፣ የጊዜውን የእሥር ቤት ሁኔታ ከሞላ ጐደል በጨረፍታ ይታተታል። ከዚያ ሐተታ በፊት ግን፣ ይህ የ 19 ዐመት ጉብል ወጣት፣ በዚያ ዕድሜው፣ እንዴት በዓለም በቃኝ ውስጥ እሥረኛ ሊሆን የቻለበትን መነሾ ባጭሩ ማስረዳት ይገባል።

ይህ ወጣት፣ ሸንኮራና ምንጃር ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ሀገር ተወልዶ ያደገ፣ ያንድ ብርቱ ገበሬ ልጅ ነው። አባቱ እንደጢሰኛ ገበሬ አደርነቱ፣ መሰል የሙያ ባልንጀሮቹን ካንድ ሁለቱ እየሰበሰበ፣ የባለርስቶችን መሬት ለገዛባለቤቱ ለአራሹ ገበሬ ለማድረግ፣ አድማ አስመትቶ፣ ከመንግሥትና ከርስት ባለቤቶች ቅጣትና ዛቻ ደርሶበታል። እንዲያውም ከነቤተሰቡ፣ በሳር ቤቱ ውስጥ እንዳለ በተንኰለኞች ሌሊት በተለኰሰ እሳት ተቃጥሎ በመንደድ የሞተው፣ እንደነገ ፍልሚያ ከባላባቶች ጋር ለማድረግ፣ መሰል ገበሬዎችን ባስተባበረበት ዕለት ነው። ይህ ወጣት ልጁ ግን፣ እንዳጋጣሚ ጨውና ላምባ ለመግዛት፣ ናዝሬት ካለው ገበያ ሔዶ አልተመለሰም ነበርና፣ ከቃጠሎው በሕይወቱ አምልጧል። ይሁን እንጅ፣ በተወለደበት አካባቢ





የሚረዳው ሌላ ሰው ባለማግኘቱ፣ ዘመዶቹ እንደማገዶ የነደዱበትን መንደሩን ትቶ፣ የቀን ሥራ ወደ እሚአገኝበት ወደ ናዝሬት ከተማ ተሰዶ ሲኖር ሁለት ወራት ያህል ሆኖታል። ወንጀል ሠርተሃል ተብሎ የተያዘው በዚሁ ከተማ ውስጥ ነው።

ራሱ በገዛ አንደበቱ ያስረዳ እንደነበረው ከሆነ፣ በናዝሬት ከተማ ይኖር የነበረው፣ በኩሊነት ሥራ ነው። እንዳጋጣሚ ሆኖ አንድ ሰሞን ለአራት ቀናት ያህል ሥራ አጥቶ ይቸገራል። ረሀብ ጊዜ አይሰጥምና፣ ምግብ የሚያገኝበት ሌላ ዘዴ ይፈልጋል። አንዱ፣ ከመንገደኛም ላይ ሆነ በየቤቱ ተዟዝሮ መለመን ነበር።

" ጤነኛ ነህ! ወጣት ነህ! ሠርተህ አታድርም! " የሚል መልስ ሆነ በልመና ያገኘው ውጤት። ሌላ ነፍሱን ከረሀብ ለማዳን ያለው ምርጫ፣ መሥረቅ ሆኖ ይታየዋል። አልዘገየም፣ አንድ ቀን ማለዳ ላይ፣ በዚሁ ውሳኔው ፀንቶ፣ ማታ ማታ ከሚያድርበት፣ ከማርያም ቤተ ክርስቲያን እድሞ ጥጋት ሥር፣ ለስርቆት ተዘጋጅቶ ይወጣል።

ረፋድ ላይ፣ ከአንድ በሩ ገርበብ ካለ የቤት ደጃፍ ላይ፣ ሁለት አዳዲስ ብርድ ልብሶች በሽቦ ላይ ተሠቅለው ያያል። " ዛሬ የመጣው ይምጣ " ይልና፣ ቶሎ ደርሶ እጁ የያዘለትን አንዱን ብርድ ልብስ ይዞ ይሸመጥጣል። ለካስ ሁለት ትንንሽ ሕፃናት ከቤቱ ደጃፍ ላይ ቁጭ ብለው ይጫወቱ ኖሮ፣ ብርድ ልብሱን ይዞ ሲሄድ አይተውት ኖሯል። ሕፃናቱ ተጣድፈው ወደ ቤት በመግባት፣ የመንደሩ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ የተፈላውን ቡና በመከስከስ ላይ እንዳለ፣ " ብርድ ልብሱን ሌባ ወሰደው! " የሚል ሪፖርት እየጮሁ ያቀርባሉ።

መላው የቡና ተሳታፊ ተጣድፎ ወዲያው በመነሳት

ብርድ ልብሱን የወሰደውን ሰው ይከተላል ። ያ መሥረቅ የመጀመሪያ ጊዜው የሆነ ወጣት፣ ብርድ ልብሱን ይዞ ሠከም ሠከም ሲል፣ ከበስተኋላው መዓት ሕዝብ ሲመጣበት ያይና በጣም መሮጥ ይጀምራል ። ሊይዘው የሚከተለውን ሰው ብዛት እየተገላመጠ በማየትና በመፍራት፣ “ ብርድልብሱን ስተውላቸው ይተዉኛል ” በሚል ግምት፣ የሠረቀውን ብርድ ልብስ ጥሎ በተራበ አንጀቱ ሩጫውን ይቀጥላል ።

ትንሽ ሮጦ ዞር ብሎ ቢያይ፣ ብርድ ልብሳቸውን ቢያገኙም፣ እሱን እንዳልተዉት ይረዳል ። የኋላ ኋላም መሮጥ ስለተሳነው ይወድቃል ። ያ ሁሉ “ ሌባ! ሌባ! ” እያለ የተከተለው ሕዝብ በሙሉ፣ መንገደኛውም ሳይቀር፣ የተቻለውን ያህል ይቀጠቅጠዋል ።


በመጨረሻም፣ ጐትተው ሙት ሬሣውን ለፖሊስ በመስጠት፣ ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ፣ በሦስተኛው ቀን ወጣቱ ነፍስ ሲዘራ፣ ለምርመራ ያቀርቡታል ። ሌባ መባሉ ኃፍረት ያሳደረበት በመሆኑ፣ ራሱ በፈጠረው ዘዴ፣ ለምርመራ በቀረበበት ወቅት፣ የዕብደት በሽታ እንዳለበት ሰው ወፈፍቱ ዐይነት ሆኖ ይቀርባል ። መርማሪው ፖሊስ ሲጠይቀው ያልሆነ ነገር ይዘላብዳል ። አእምሮው የተነካ እውነተኛ ዕብድ መስሎ በመታየቱ፣ በዚያው በታሠረበት ጣቢያ ሁለት ሳምንት ያህል ቆይቶ፣ በመጨረሻ ላይ መርማሪው ፖሊስ ለጣቢያው አዛዥ ያቀርበዋል ። የጣብያውም አዛዥ የምርመራውን ሪፖርት ከተመለከተ በኋላ፣ “ ይኸማ አደገኛ ወጣት ነው ። እብደቱ ሲብስበት ከመስረቅ አልፎ ሰውም ሊገድል ይችላል! ” በሚል ውሳኔ ላይ በመድረስ፣ የእብዶች መናኸርያ ወደሆነው፣ አማኑኤል ሆስፒታል ተወስዶ እንዲታከም አዲስ አበባ እንዲላክ ትዕዛዝ ይሰጣል ።





ውሳኔው አልዘገየም፣ በማግስቱ የፊጥኝ ታስሮ አማኑኤል ይላካል ። እዚያም እንደደረሰ፣ በሆስፒታሉ ሁለት የታወቁ ዶክቶሮች መቅድማዊ ምርመራ ይደረግለታል ። ወጣቱም፣ ዶክተሮቹ ላቀረቡለት ጥያቄዎች ጤነኛ መልስ ከሰጠ በኋላ፣ የገጠመውን ሁኔታ በዝርዝር ምንም ሳይደብቅ ይነግራቸዋል ። በረዳትና በሥራ ማጣት፣ የሚቀምሰው ባለማግኘቱ ለመስረቅ እንደተገደደና ሰዎቹም ሌብነቱን እንዳያምኑበት በማሰብ፣ ልክ እንደእብድ ሆኖ በመርማሪ ፖሊሶች ዘንድ አውቆ ማድረጉንና፣ በተረፈ ንፁሕና ጤነኛ መሆኑን ጭምር ያስረዳል ። ዶክተሮቹ ግን የወጣቱን ሐቀኛ መግለጫ በመጠራጠር “ ይኸማ አደገኛ እብደት ነው ። ሲነሣበት ሕይወት እስከ ማጥፋት አይመለስም፣ ሲበርድለት ደግሞ ሙሉ ጤነኛ ሰው ይመስላል ። ከዚህ ቀደምም፣ይህን መሳይ በሽተኛ ብዙ ጊዜ አጋጥሞናል ። ጤነኛ ነው ብለን ብንለቀው፣ በመስረቅ ወንጀሉ መከሠሱ አይቀርምና፣ ኋላ በሚያመጣው ጠንቅ እኛን ሊያስወቅሰንና ኃላፊነት ውስጥ ሊያስገባን ይችላል ። የአእምሮ ሕመም እንዳለበት ብንመሰክር ደግሞ፣ ፍርድ ቤት አይቀርብምና፣ ለጊዜው ሁኔታው በሰፊው እስኪጠና፣ ዓለም በቃኝ ቍጥር 17 ይቈይ ” ብለው ይወስናሉ ።

በዚህም ውሳኔ መሠረት፣ ዓለም በቃኝ ተወስዶ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሚኖሩ እብዶች ጋር በክፍል ቍጥር 17 ውስጥ ሲኖር፣በዚያን ጊዜ ብቻ ሦስት ያህል ዓመታት አድርጐ ነበር ። ይህ ወጣት፣ አንደኛ የት ደረሰ ብሎ የሚከባከበው አንድም ዘመድና አዝማድ የሌለው በመሆኑ፣ ሁለተኛ በፈፀመው ወንጀል እንኳ ቢከሠስ፣ ከዓመት ጊዜ ያልበለጠ የእሥራት ቅጣት እንደሚበቃው ሲታወቅ፣ ወንጀለኛነቱን የትኛውም ፍርድ ቤት




**ዓለም _ በቃኝ**

ጀሐነብ (ዮት) እንዳለ፣ ግወት ለሚፈልግ፣
ዓለም-በቃኝ ቢሔድ፣ ያገኘዋል በወግ።
የሥቃያት ዐይነት፣ ይረዳል በዝርዝር፣
ብዙ ዘመን ሳይፈጅ፣ በአንዲት ቀን አዳር።
ባስቲል ይሉ ባርካ፣ ሜሪ አብዮቶች፣
አይወዳደሩም፣ ካለም-በቃኝ ገጾች!!
አቃጥሎ የሚጠብስ፣ የሠቆቃው ዓይነት፣
በዚያ ዓለም-በቃኝ፣ መኖሩን ሲያይበት፣
ጀሐነብ መሆኑን፣ ያውቀዋል በቅፅበት!





ስለማያውቅና የፋይል መዝገብም የሌለው በመሆኑ፤ እነዚያ የአማኑኤል ሆስፒታል ዶክቶሮችም፣ " ልዝብተኛ እብድ " ብለው፣ ያለፋይል ወደ ዓለም በቃኝ ከላኩት በኋላ ስለለ ረሱት፤ አራተኛ ስለግለ-ሰቦች ሕይወት ጥንቃቄ የሚከታተል ድርጅት በሃገራችን ባለመኖሩና በመሰል ምክንያቶች፣ ያን መሳይ ሎጋ ወጣት፣ በዚያ አሠቃቂ እሥር ቤት ውስጥ፣ ከሐ ቀኛ እብዶች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ታፍኖ ሲኖር፣ ብዙ ዓመታት አልፈዋል።

ድሮ የዛሬ አሥራ አምስት ዓመት፤በዓለም በቃኝ ውስጥ ያውቀው ለነበረ አንድ የእሥር ጓደኛው፣ ሰሞኑን እድል አጋ ጥሞት፣ በቀይ መስቀል ረዳትነት የሚከተለውን ደብዳቤ ይጽ ፋል። በተለይም ያ የድሮ እሥር ቤት ሁኔታ፤ዛሬ ምን መልክ እንዳለው በሰፊውና በዝርዝር የሚገልጽ በመሆኑ፣ " ለውጥ አመጣሁ እያለ የሚፎክረውንና የሚደነፋውን የጊዜያዊ አምባ ገነን የፋሽስቶች መንግሥት፣ በሚገባ ሠቅስቆ የሚያጋልጥ በመ ሆኑ፤ ደብዳቤው እንዳለ ከነሙሉ ይዘቱ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሚያዝያ (ፋሲካ) 1980
ዓለም በቃኝ
ክፍል፣ 17
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

እንደ እንጀራ የምትርበኝ፤
እንደውሃም የምትጠማኝ፤
ምንጊዜም የምትታሰበኝ፤
የዓለም በቃኝ የእስር ጓዴ..........
ጓዴ ሆይ፤ ሰላምታየ ይድረስህ ብዬ እንዳልጽፍ፣

ሰላም የለኝም ። ሰላምን የት አውቃትና ። ደኅና ነኝ እንዳል
ልህም ፣ ደኅና አይደለሁም ። ደኅንነትን የት አውቄው?............
ትመስገን እንዳልልህ፣ ምን ስላደረገችልኝ ። አሥራስምንት
ዐመታት ሙሉ ፣ ረሃቤ በፈጠረው ወንጀሌ በመማቀቄና ፣ በዚያ
የሳት ቃጠሎ ቤተሰቦቼ ስለነደዱ ፣ ሕይወት የሚሉት ነገር ትዝ
ታው ጭምር ጠፍቶብኛል ። ይህን ደብዳቤ የጻፍኩልህ፣ መድ
ረቅ ላይ የተቃረበውን እምባዬን ፣ ከዚያች ከምታውቃት ድቡል
ቡል ቂጣ ጋር ተሳስቶ የመጣ ከሰል አግኝቼ ፣ ከፈጨሁት በኋላ ፣
ባቀለምኩት የእምባ ቀለም ነው ። ብዕርማ አይፈቀድም ። ጓዴ ፣
ሰው ሆኖ መፈጠር ትልቅ ዕዳ እንደሆነ ፣ የኔ ታሪክ ምስክር
ነው ። እድል ገጥሞህ፣ እንደገና ልታየኝ ብትችል ፣ በጭራስ
አትለየኝም ። ለትንግርት የምታይ ልዩና ቅይር ፍጡር ወጥቶ
ኛል ። “ Forgetful of the world by whom they arᵉforgotten ”
እንዳለው ጂቦን ፣ የረሳኝን ዓለም እኔም ረስቼዋለሁ ።

ከሌላው አንጻር ባይገርምህ ፣ እሳት የላሰው ተማሪ ወጥ
ቶኛል ። ከምሁራን ጓድ እሥረኞች እየተጠጋሁ ፣ ያጠናሁት
እውቀት ፣ ነፃ ወጥቼ አልሠራሁበትም እንጅ ፣ ብለቀቅ ኖሮ ፣
ለሀገሬ ፣ ፀሐይ ዘንድ የሚደርስ ሮኬት ሳይሆን ሲፐር ሮኬት
እፈጥርላት ነበር ። ቋንቋውንማ ተወው ፣ ሊቅ ሆኜልሃለሁ ።
ከሀገራችን የብሔረሰብ ቋንቆች አንስቶ በዓለም እስከታወቁት
እነ እንግሊዝኛን ፣ ፈረንሳይኛን ፣ ጣልያንኛን በሚገባ በሙሉ አን
ደበቴ ልናገርባቸው ችያለሁ ። ግን ምን ያደርጋል? ምንስ
ፋይዳ አለው? ስለ ሕይወትም ሆነ ስለ ሰው ህላዌ ያለኝ አስተ
ሳሰብ በደረሰብኝ ስቃይ ተሞርዶ ተሞርዶ አልቋል ። እንደገና
ሰው መሆኔ ያጠራጥራል ።

ጓዴ ሆይ ፣ እንዲህ ያለውን ልተውና ፣ ባጠገቤ ያለ





ውን “ ገብስ ገብሱን ” ላውራህ ። ያኔ ያ ሁሉ እሥረኛ ሲመ
ኘውና ሲያልመው የኖረው ፣ የመንግሥት “ ለውጥ ” እንደ
ምኞቱ መጣ ። “ ለውጡ ” መጣ እንጅ ምኞቱና ተስፋው
አሁንም በአዲስ መልክ እንዳለ ነው ። የመጣው “ለውጥ” ሳይ
ሆን “ ነውጥ ” ነው ። ተሳስተው አሳሳቱ እንጅ ፣ ቤሣ ሣን
ቲም የተሻሻለ ነገር የለም ። ስለውጭው ከተማና ገጠር ፣ በወሬ
ጠግቤዋለሁ ። እልፍ አእላፋት እሥረኞች በእሥር ቤታችን
ተሞጅረው ታጭቀው ፣ ስለሁሉም አስረድተውኛል ። በወሬ የሰ
ማሁትን አላወራህም ። ላንተ ፍላጎት ያህል ፣ የዚሁ የግቢያችን
መግለጫ ይበቃሃል ።

ያ ፣ ድሮ የምታውቀው ዓለም በቃኝ ፣ እስካፍ ጢሙ
በእሥረኞች ጢም ብሎ በመሞላቱ ፣ መንቀሳቀሻ እንኳ አጥተ
ናል ። አብዛኛውም እሥረኞች ምሁራን ናቸው ። ከሞት ተር
ፈው የታሠሩትንማ ፣ ጭቁኖችና የጭቁን መደብ ወገኖች ፣ ልቆ
ጥርልህ አልችልም ። ምን አለፋህ ድሮ ፣ ስድስት በዝቶባታል
ብለን የምናማርርባት ያቺ ያለም በቃኝ ክፍል ፣ ዛሬ ከእጥፍ
በላይ ታምቆባት ፣ ከአስራ አምስት እሥረኞች በላይ ያጉሩ
ባታል ። ሠርዲን አይቶ ማየት ነው ። ሌላው ቀርቶ ፣ ላበዱ
እሥረኞች ብቻ ተመድባ የነበረችው ቍጥር 17 የኛ ክፍል ፣
ዛሬ በጤነኞች እሥረኞች ሣይቀር ፣ ጢቅ ብላለች ።

ከእሥረኛው ሠራዊት ብዛት የተነሳ ፣ ድሮ የቀጠሮኛ ፣
የፍርደኛ ፣ የእድሜ ልክ እሥራት ፣ የሞት ፍርደኛ ፣ እየተባለ
እንደ እሥራት ዘመኑና እንደ ወንጀሉ ፣ እየከፋፈሉ መድቦ
ማስቀመጡ ቀርቶ ፣ የመጣውን እሥረኛ ሁሉ ፣ ካገኙበት ቦታ
ዝም ብሎ መሞጀር ሆኗል ። ከእሥረኛው ብዛት የተነሣ ፣ ያቺ
ድሮ በቀን ሁለቴ እናገኛት የነበረችዋ አሎሎ መሣይ ቂጣ

እንኳ፣ ዛሬ በሣምንት አራት ጊዜ ብቻ ስትመጣ፣ እንደብርቅ እናያታለን። ያ እሑድ እሑድ ይሰጠን የነበረው የሾመጠጠ እንጀራና፣ ያቺ ላጺስ ስጋቸው፣ መቅረት የጀመሩት፣ ገና አብዮት ተጀመረ ተብሎ፣ ወታደሩ ሥልጣን መያዝና ሀብት ማስከበር በወጠነበት ጊዜ ነው።

" ቡና" እየተባለ ጠዋት ጠዋት ይሰጠን የነበረውም ያረረ የገብስ ቅቅል ጭማቂ፣ ከቀረ ብዙ ጊዜ ስለሆነው፣ ጭራስ ከነመኖሩም ረስተነዋል። እሱስ እንኳን የቀረልን። ያኔ አንተ እንኳ በነበርክበት ዘመን፣ ያን ሁሉ እሥረኛ ጥላሸት አስመስሎት እንደነበረ አትዘነጋም። ምን አለፋህ፣ በዚያ ግቢአችን ያልቀሩትና፣ በይበልጥም ተባዝተው ያሉት፣ " እነማሚቶና እነጅቦ " (እግረ-ሙቆች) ናቸው። ሁኔታው አላስችል ያለውና መታገስ ያቃተው ታጋይ እሥረኛ፣ በረበሸና በተሳደበ ቍጥር፣ እንደአሽን ከቦን ያለ ወታደር፣ ወዲያው እግሮቹንና እጆቹን እየጠፈረ ሲቀጠቅጠው ይውላል። አንተ ያኔ ያላየኸው፣ አራት አምስቱን እሥረኞች አንድ ላይ ጨብጦ የሚያቆራኝ ግንድ ግንድ የሚያህል ሠንሠለትም፣ ዛሬ ዓለም በቃኝ ውስጥ ሥራ ላይ ውሏል። በነዚህ ሠንሠለቶች የታሠሩ ሁሉ ለመንቀሳቀስ ምንም ዕድል ስለሌላቸው፣ መብላትም ሆነ መሽናት በጭራሽ አይችሉም። ደግነቱ ይህ ዓይነቱ ቅጣት፣ ለተወሰኑ ቀኖች ብቻ መሆኑ በጀ እንጅ፣ ጊዜው ረዥምም ቢሆን ኖሮማ፣ ብዙ ሬሣዎችን በየቀኑ ማየት ይቻል ነበር። ሌላው፣ እሥረኛ በየጥቃቅኑ ምክንያት አጥፍተሃል እየተባለ በጉማሬ መገረፉ ተራ ነገር ሆኗል። በጊቢያችን ውስጥ፣ ከዚያ ሁሉ እሥረኛ፣ ጠባሳ የሌለበት ቢገኝ፣ ቍጥሩ እጅግ በጣም ጥቂት ነው።

" አንዳንድ የኢንተርናሲዮናል ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያን





እሥር ቤቶች ጐበኙ " የሚል ፈጠራ ወሬ ስትሰማ፣ " እሥር ቤቾት ከድሮ ይዞታቸው ተሻሽለዋል " ብለህ ታስብ ይሆናል። ደረቅ ፕሮፓጋንዳ ነው። ሀገራችን ከምትሰጠው ጥቅም ለመሻማት አሰፍስፈው ከሚገኙት የሩስያ፣ የኩባና የምሥራቅ አውሮፓ የስም ሶሻሊስት ሀገሮች፣ የተውጣጡና እንዲሁም አንዳንድ በገንዘብ የተገዙ የአውሮፓና ያሜሪካ ኤጀንቶች፣ ሁለት ጊዜ ያህል ጐብኝተውን ነበር። እነሱ በመጡባቸው ሁለት ቀናት፣ አቤት የበላነው ምግብ፣ የጠጣነው መጠጥ፣ ሌላ ነበር! የፍትፍቱ ሽታ ለስምንት ቀን ያህል፣ መላውን የወህኒ ቤት ክልል ያውድ ነበር።

መጠጡማ ተወኝ ! ካልኮል በስተቀር ያልቀረበልን ለስላሳ የመጠጥ ዘር አልነበረም። ጐብኝዎቻችን ከጊቢያችን ሲወጡ፣ ወዲያው እያወለቅን አስረክብን እንጅ፣ ለወቅቱ ተሰጥቶን ለብሰነው የነበረ ጨርቅ፣ ግቢውን ሳይቀር አድምቆት ነበር። ቀለሙ ቀይ የሆነ እጀጉርድ እጀጠባብና፣ ግማሽ ባት ላይ የምትደርስ ሱሪ ተሰጥቶን፣ ለጥቂት ሰዓታትም ቢሆን ሸር ብለን ዋልን። ጐብኝዎቹ ሲመጡ፣ ምንም ዓይነት ጥያቄ እንዳናቀርብና በጭራሽም እንዳንነጋገር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን ስለነበረ፣ ከጥቂት ቈራጥና ደፋር እሥረኞች በስተቀር፣ በዚያ ቀን የተናገረ እሥረኛ አልነበረም። እነዚያ የተናገሩ ጥቂት እሥረኞችም ቢሆኑ፣ በዚያው እለት ምሽት ለቅጣት ተወስደው እስከ ዛሬ የት እንደደረሱ የሚያውቅ የለም።

በዚያ እለት ብቻ እንዲያ ለብሰን፣ እንዲያ በልተን፣ እንዲያ ጠጥተን ያዩ፣ የኢንተርናሲዮናል ታዛቢዎች፣ ምናልባት " አዲስ አበባ ያለው ትልቁ እሥር ቤት መንግሥተ ሰማያት ነው " ባይሉም፣ ከምድራዊ " ገነት " ጋር አወዳድረው፣

ለዓለም ህዝብ መግለጫ ሰጥተው ይሆናል። ይህም አባባል፣ የነሱ ብዕርና አንደበት የተፋው ምናምንቴ መግለጫ ይሆናል እንጅ፣ የኛ የእሥረኞቹ ሁኔታና የእሥር ቤቱም ተጨባጭ እውነታ ሌላ ነው።

የሚገርምህ፣ ያን ዕለት እንግዶቹ ጐብኝዎች ሲያዩን ሲመጡ፣ አዲሱን ለዚያ ዕለት ብቻ የተዘጋጀውን ልብስ ልበሱ ሲባል፣ አሻፈረኝ ያሉ እሥረኞች በሙሉ ቍጥር 17 ክፍል ውስጥ አግረው፣ ያበዱ ወንጀለኞች ናቸው በማለት፣ ለጐብኝ ዎቹ ካሳዩ በኋላ፣ እነዚያን እሥረኞች ከዚያ ቀን ጀምሮ በልዩ እግረ-ሙቅ ገብተው እስከ ዛሬ ድረስ ሳይፈቱ በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ። አንዳንድ አሳዛኝ ሁኔታ ልጥቀስልህ ብዬ ነው እንጅ፣ የሚፈፀምብን ግፍ ይህ ነው አይባልም።

በጣም የሚገርመው ግን፣ ድሮ ባለፈው መንግሥት ጊዜ ለይስሙላም ቢሆን፣ አብዛኛው እሥረኛ ወደ እሥር ቤት የሚላከው፣ ፍርድ ቤት ቀርቦ፣ ዳኞች አይተውት ነበር። ዛሬ ግን፣ በዚህ ጊቢ ከሚገኘው እሥረኛ 90ው እጅ ፍርድ ቤት ከሚባለው፣ ከደጁም ያልደረሰ ነው። አብዛኛውም እሥረኛ በምን ወንጀል እንደተከሠሰም አያውቅም። ብቻ ሰብስበው አምጥተው ይሞጅሩታል። ፍርድ የለ! ቀጠሮ የለ! በዚህ በኛ ዓለም በቃኝ ጊቢ ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን እስረኞች አነጋግ ሬአለሁ። የወጣቱ አጠቃላይ ወንጀል " ፀረ ሕዝብ " ና " አና ርሺነት " የሚል ሲሆን፣ ጠና ጠና ያሉት እሥረኞች ደግሞ " አድኃሪነት " እንደሆነ ነግረውኛል። ባይገርምህ አብዛኛው፣ ወጣትና ገና በአፍላ ዘመኑ የሚገኝ ነው። ጠጋ ብለህ ስታነጋ ግረው፣ መንግሥት ይሠረው እንጅ፣ ስለ ሀገሩ ፍቅርና ስለ ጭቁኑ ሕዝብ አርነት ያለው ስሜት አሁንም እጅግ የጋለና





ትኩስ ነው። የታሠረበት ምክንያት በዓይነቱ ይለያይ እንጅ፣ የሁሉም እሥረኛ መነሻ ምክንያት የጊዜያዊውን አምባገነን የፋ ሽስት መንግሥት ጥላቻ፣ የሀገሩ ብሔራዊ ክብር በባዕዳን ሠርጐ ገብ ወራሪዎች መደፈር፣ ለሕዝቡ የመጣለት ዐብዮት መኰላሸት...... ያበሳጨው መሆኑን ያለመጠራጠር ትረዳለህ።

ይሁን እንጅ፣ ያን ሁሉ ታጋይ ጓድ ሲያስሩ፣ የተለያየ ስምና ወንጀል በመስጠት ነው።

" ፀጕርህን ለምን አጐፈርክ?
የቀበሌ ሹም ለምን ሰደብክ?
ጌቶች ሊቀ መንበር በመኪና ሲያልፉ ለምን ገላመጥክ?
ያልሆነ ቃል ለምን ተናገርህ?
በጥናት ጉባዔ ላይ ለምን አልተገኘህም?
"የኢትዮጵያ ትቅደም" ፍልስፍናን ለምን አንጓጠጥህ?
ራሻኖችን ለምን ሪቪዢኒስት አልህ?
የማኦን መጣፍ ለምን ይዘህ ተገኘህ?
የጴንጤዎች አባል ለምን ሆንህ?
የድሮ ነገሥታት ፎቶ ለምን ከቤትህ አስቀመጥህ?
ከድሮ ጢሰኛህ ጋር ለምን ተናገርህ?
ይኃፓን ለምን ደገፍክ?
አምስት ኪሎ ቡና ለምን ደብቀህ ተገኘህ?
ውጭ አገር ለሚኖር ዘመድህ ለምን ደብዳቤ ጻፍህ?
የድል በዓል ላይ ለምን አልተገኘህም?
አለፈቃድ ለምን ከሥራህ ላይ ጠፋህ?
ሰዓት እላፊ ለምን ጠጣህ?"......እነዚህን የመሳሰሉ ልዩ

ልዩ ምክንያቶች ይገኙበታል። በውነቱ እያንዳንዱ ዝርዝር ወን ጀል ቀርቶ፣ ጠቅላላው

ወንጀል ባንደት ተጨምቆ እንኳ የሚገኘው የወንጀል ጠብታ አምስትና ስድስት ዐመታት ማሣሠር ቀርቶ፣ አንድ ነጠላ ዓመት እንኳ ማሣሠር አይችልም ነበር። አንድ ሌላ ትንግርታዊ ዜና ላጫውትህ። በጊቢያችን የመጨረሻው ወጣት እሥረኛ አሥራ አምስት ዓመት የሆነው ተማሪ ነው። ፈፅመሐል የተባለው ወንጀል ያስቅሃል።

ሰምተህ ይሆናል፣ ደርግ የሚሉት ምናምንቴ ገና የተቋቋመ ሰሞን፣ ይሆነኝ ብሎ ያዘጋጀው አንድ የኢትዮጵያ ካርታ አለ። በዚያ ካርታ ላይ እስከ ዛሬ ፍቺው ምን እንደሆነ በግልጽ ያልታወቀ አንድ ዐይን መኻሉ ላይ ተሥሎበታል። ምናልባት፣ አንድ ብር ኖት ላይ በሥውር እንደተጻፈው ያለ ዐይነት አንድ ታንኪረኛ ሰው ያዘጋጀው ሥዕል ይሆናል። ይህ ወጣት እሥረኛ፣ ያን ባለ አንድ ዐይን ካርታ ለመጀመርያ ጊዜ ሲያይ፣ በቅንነትም ይሆናል ወይም በብልህነት፤ " ምነው የናት ኢትዮጵያን አንድ ዐይን ደርግ አጠፋው! ዐይንሁሉ ሁለት አልነበረም እንዴ? " ብሎ በመገረም ይናገራል። ማታ ብዙ ሰዎች ባሉበት፣ ቴሌቪዥን ሲያይ እንደ ልጅነቱ የመጣለትን የተናገረው ነበር። ግን ከቴሌቪዥን ተመልካቾቹ ውስጥ ሦስቱ ወታደሮች ስለነበሩ፣ ሪፖርት አርገውበት፣ በማግ ሥ ቱ፣ ይኸው ንግግሩ ብቻ አስወንጅሎት ዓለም በቃኝ ከገባ ሦስት ዐመቱን ይዟል። የዚህን ወጣት ወንጀለኛነት፣ ፍርድ ቤትም ሆነ ፖሊስ ጣቢያ ስለማያውቀው፣ ፋይልም ሆነ ቀጠሮ የለውም። አሁን፣ በዚያ አሠቃቂ ቦታ ላይ በለጋነቱ ዘመን በመግባቱ አልፎ አልፎ ወፈፍ ያደርገዋል። ከየት እንደሰማው አላውቅም እንጅ፣ ራሱን ነካ ያደረገውዕለት፣ እንደሚከተለው እየጮኸ ይዘምራል።





" ናፖሊ ናፖሊ ያሠለጠናቸው፣
ኰፍያው ገዳዳ ጫማው ምሥማር የለው፣
እነመቶ አለቃ፣ እነሻምበል ናቸው፣
ታምቡር እየመቱ ይሔዳሉ እኛው!"

አጠቃላይ መግለጫ ከየዓይነቱ እየጠቃቀስኩ የምፅፍልህ፣ ዝርዝሩን በማተት እንዳላስለችህ ብዬ ነው። ድሮ እያንዳንዱ ዓለም በቃኝ ክፍል ውስጥ መፀዳጃ እንዲሆን አንዳንድ ገረወይና ይቀመጥ ነበር። ለዚያች ሽንት ቤት ተራ ባልደረሰን ጊዜ፣ ይህን ገረወይና እንጠቀምበት እንደነበር ትዝ ይልሃል። ዛሬ እነዚያ ገረወይናዎች በሙሉ ተወስደዋል።ያለው ምርጫ፣ የክፍሉን አንድ ጥጋት ለገረወይናው አገልግሎት ምትክ አርጎ መጠቀም ስለሆነ፣ ምን አለፋህ እያንዳንዱ እሥረኛ በወር ውስጥ ለተወሰኑ ሣምንታት በጉንፋን መታመም አለበት። ድሮ እንደነገሩም ቢሆን ዶክቶርና ሐኪም ቤት ነበር። ሰምተህ ይሆናል የሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ወጣት ልዕልታትና ልዑላን ሳይቀሩ፣ ከሰው ያልተፈጠሩ ይመስል፣ ከሕዝቡ ጋር እንደ ሕዝቡ እንዳይታሠሩ፣ በተለይ ለይተው በሆስፒታሉ ውስጥ አስረዋቸዋል። ገና ለገና የነገሥታት ዝርያ አላቸው ብሎ፤ ገና ጡት ያልጠገቡ ሕፃናትን ሕዝባዊነት ባሕርይ እንዲሠርፅባቸው ከሕዝቡ ጋር ደባልቆ በማስተማር ፋንታ፣ በሆስፒታሉ ውስጥ ከርችሞ በማኖሩ፣ መሪዎቻችን ምን ዐይነት የሞራል ዝንባሌ እንዳላቸው የሚያሳይ ያምባገነንነት ፋሽስታዊ ጠባይ ማንፀባረቂያ መስተዋቶች ሆነዋል። ታዲያ ከእንደዚህ ዐይነቱ መንግሥት ምን ዐይነት ተስፋ ትጠብቃለህ? መታከሚያ ሆስፒታልና ሐኪም ባለመኖሩ፣ የሚሞተውም ሆነ የሚታመመው የእሥረኛ ቍጥር ተመጣጣኝ ነው። ባስፈለጋቸውም ጊዜ

የተወሰኑ እስረኞች እየመረጡ ወስደው በመረሸን በጥይት
ያንዷቸዋል። የዚያንው ያህል እስረኛ ከሚመጣበት አይታወ
ቅም፣ በማግሥስቱ ሞልቶ ጢም ይላል። ከእሥረኛው ብዛት
የተነሳ፣ የሚያሰፍሩበት ቤት ቢያጡ፣ ድሮ የሙያ ተግባር
መሥሪያ ቤት የነበረውን አዳራሽ ሳይቀር፣ ሞቶሮቹን በሙሉ
አውጥተው፣ የእሥረኛ ማጐሪያጉረ አድርገውታል። ምን
የሙያ ቤቱን ብቻ፣ ቤተ መስጊዱ፣ ቤተ ክርስትያኑና መጻሕ
ፍት ቤቱ ሳይቀሩ በሙሉ፣ ለእሥረኞች ማፈጊያነት ተለው
ጠዋል። ጉቦኛው ካቦ፣ ካድሬ በሚል አዲስ ስያሜ፣ ሲያረ
ጠርጥ ብታይ ልዩ ድራማ ነው!

እሑድ በመጣ ቍጥር፣ የዚያ ሁሉ እሥረኛ ቤተሰብ
ይመጣ ይመጣና፣ የእሥር ቤቱን ማርገጃ መተናፈሻ ሲያሳ
ጣው፣ መላው የአዲስ አበባ ሕዝብ ተነቅሎ የመጣ ይመስላል።
እንደድሮው ገብቶ እሥረኛን መጠየቅ አይፈቀድም። ከስንቅ
አቀባዩ ብዛት የተነሣ፣ ስንቁ ሳይቀር እየተሳከረ፣ ያንዱ ስንቅ
ለሌላው ሲደርስ፣ ስንቅ ያልተላከለት እሥረኛም በፎርፌ
ያንዱ ስንቅ ያንተ ነው ተብሎ የሚሰጥበት ጊዜ ይበዛል። ያ
ሁሉ ጠያቂ ሕዝብ በየእሑዱ እየመጣ በወህኒ ቤቱ ደጃፍ ላይ
ሲተምና ሲርመሰመስ፣ እኛ ከውስጥ ሆነን ድምፁንና ሁካታ
ውን ስንሰማ፣ የጥ ም ቀት በዓል፣ ወይም ምፅአት የመጣ ይመ
ስለናል። በጣም የሚገርምህ ደግሞ፣ እሥረኛ ዘመዳቸው በሕ
ይወት አለመኖሩን ሳያውቁ፣ በየሣምንቱ እሑድ እሑድ፣ ለሌላ
ባይተዋር ወገናቸው ስንቅ የሚያቀብሉ መኖራቸው ነው። ይኸ
እንኳ አይከፋም!

ድሮ የወህኒ ቤቱ ዙሪያ የታጠረው በተራ ሽቦ እንደ
ነበር ታስታውሳለህ። ዛሬ ዙሪያው በስሚንቶ እድሞ ታሽጓል።





ድሮ አልፎ አልፎ ታያቸው የነበሩ ማማዎች፣ ዛሬ ቍጥራቸው
በርክቶ፣ በሮንድነት የሚጠብቁትም ወታደሮች ሦስትና አራት
ሆኗል። ስለማይተማመኑ ይመስላል፣ በአንድ ማማ ላይ ሦስት
ወታደሮች ካሉ፣ ሦስቱም ከተለላየ ሥፍራ የሚመጡና በተለ
ይም፣ አንዱ ኢትዮጵያዊ ሌላው ኩባዊ፣ የቀረው ደግሞ ምሥ
ራቅ ጀርመናዊ መሆን አለበት። ድሮ የእሥር ቤት ፖሊሶች
በመጠበቂያነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ መሣሪያዎች፣ እንደ ናስ
ናስርና አልቤን የነበሩ ጠብመንጃዎች በሙሉ፣ በአዱዱስና ኡዚ
ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ተተክተዋል። በአዲስ አበባ የሚገኝ ታን
ክና መትረየስ ሳይቀር፣ በወህኒ ቤቱ ዙርያ ተደግኖ ይውላል፣
ተደግኖ ያድራል። በዚያንው ልክ፣ እነዚያ የምታውቃቸው
ባውዛዎች በሙሉ ተለውጠው፣ በላምባ መሥራቱ ቀርቶ፣
በኤሌትሪክ ከፍተኛ ዋት የሚንቀሳቀሱ፣ ከመቶ ያላነሱ ባውዛ
ዎች በየአቅጣጫው ተተክለው፣ ምሽት በመጣ ቍጥር ባበሯ
ቸው ጊዜ፣ መላውን የወህኒ ቤት ጊቢ፣ የቀኒን ፀሐይ ያህል
ወለል አርድጐ በማሳየት፣ ጤፍ ሳይቀር ያስለቅማል።

የእሥር ቤቱ ጠቅላላ የአስተዳደርም ሆነ የኃላፊነት
ሥልጣን የተሰጠው፣ የሀገሪቱን ጠቅላላ የፀጥታ ቍጥጥር
የያዘው፣ የምሥራቅ ጀርመን መንግሥት ቢሆንም፣ የሩሲያና
የሌላ መንግሥታትም በአማካሪነት አሉበት። የድሮው የወፍጮ
ቤት ትልቅ ሕንፃ ታድሶ፣ ተጨማሪ ያስተዳደር መምሪያ ቢሮ
ሆኗል። በነጭ ለባሽነት ያሠሩት የወታደር ቍጥር አይነገርም።
የሚገርምህ፣ ወንጀል ሠርተዋል ተብለው፣ ለዚሁ ለስለላ ተግ
ባር የተሠማሩ ፣ባእዳን ጭምር በእሥረኛነት ስም መገኘ
ታቸው ነው።

ድሮ ጅምር የነበረው የጥቁር ገበያ ኮራፐሽን፣ ዛሬ

ከምንጊዜም ይልቅ ጦፎልሃል። ብዙ ብር ጉቦ መስጠት የቻለ፣ በደርግ አባል አማላጅነት፣ ከታሠረበት በቅፅበት መፈታት ይችላል። እነዚያ የድሮዎቹ ስኩፒኖዎች በሙሉ ጠፍተው፣ ዛሬ፣ በእስኩፒያንት ለሚገኘው ጥቅም ሲል፣ ወታደሩ ራሱ ስኩፒኖ ሆኗል። ገንዘብ እስካለ ድረስ፣ ወታደሮችን በመደለል፣ እሥረኞቹን ሴቶች ለእሥረኞቹ ወንዶች ለተወሰነ ሰዓት ቆይታ ማቃጠር ይቻላል።

በሥልጣን ላይ ያሉ አዲሶቹ የወታደር መሣፍንት፣ በጣም የሚፈሩትና ያሠጋቸው ቦታ ቢኖር፣ የመጀመሪያው ሥፍራ ወህኒ ቤቱ ነው። አብዛኛው ከሞት ያመለጠው ምሁራንና ሊቃውንት፣ ተራማጅ አስተሳሰብ ያለው ወታደሩ ዲሞክራቱ፣ ተማሪው፣ የብሔረ-ሰቡ ታጋይ፣ ታፍኖ የታጐረው በዚሁ ታላቅ ወህኒ ቤት ውስጥ ስለሆነ፣ መንግሥት ያለ የሌለ ኃይሉን በጥበቃ ላይ ያዋለው በዚሁ ሥፍራ ላይ ነው።

አንዳች ነገር አጋጥሞ፣ ከተማው ውስጥ አንድ ድምታ የተሰማ እንደሆነ፣ የጊዜው ባለሥልጣኖች በሙሉ፣ ለወህኒ ቤቱ ከያለበት አቅጣጫ ስልካቸውን ያቅጨለጭላሉ። ወደዱም ጠሉ ግን፣ አንድ ቀን ያ  የታፈነ ኃይሉ መፈንዳቱ አይቀርም። እንዲውም አሁን የሚገኝበት ደረጃ ቋፍ ላይ ነው። ያኔ ታስታውስ እንደሆነ፣ በ1953 መንግሥት ለመገልበጥ ሞክረው የነበሩት የነገርማሜ ጭፍሮች በሥር ቤቱ ሲማቅቁ ኖረው፣ ይህ ያሁኑ መንግሥት፣ ለፕሮፓጋንዳውና ለሥልጣን ላይ መወጣጫ እንዲሆነው በዘየደው መላ፣ እሥር ቤቱ ውስጥ ባላቸው ኤክስፔርያንስ ሤራ መተው እንዳያሣምፁ በማሰብ፣ “የፖለቲካ እሥረኞች ሁሉ በነፃ ተለቀዋል ” በሚል አዋጅ በየቦታው በታትኖ ነበር። ዛሬ ከነሱ ወስጥ ለዘር ያህል የተረፈ





ቢገኝ ያ እበላ ባዩ ሻለቃ ብቻ ነው። እሱንም ቢሆን እስኪ ጠቀሙበት ድረስ እንጅ፣ ኋላ  የራሺያ ጥይት ራት ማድረጋቸው አይቀርም። በዚያን ጊዜ ታስረው የነበሩትን እነታደሰ ብሩን፣ እነመኰንን ወሰኑን ታስታውስ የለም? ዛሬ የትናቸው? ነፃ ተለቃችኋል ባላቸው ባመቱ አይደለም ያስረሸናቸው!! እንግዲህ እኔ፣ በእንደዚህ ዐይነቱ ሕይወቴ ውስጥ ይህንሁሉ አየሁ። ከኔ በዕድሜና በመራራ ኑሮ ይበልጥ የኖሩት ወገኖቼ ስንቱን ትንግርት አይተው ይሆን?

ለዚህ የመጀመሪያም የመጨረሻም ደብዳቤዬ፣ ማለቢያ የሚሆነኝን አንድ ቁም ነገር ያዘለ አረፍተ ሐሳብ ሳልሰጥህ፣ ልዘጋ አልፈልግም። “ ፋሽስቶችም ሆኑ መላው አድኃሪ ኃይሎች፣ የሚፈልጉትን ያህል ለተወሰነ ጊዜ የተራማጆችን አካላዊ ሰውነታቸውን ብቻ ሊያሥሩ ይችሉ ይሆናል። ግን አላማቸውንና ትግላቸውን የሚያቀናጁበት ውስጣዊ ልባቸውን ማሠር አይሆንላቸውምና ትግል ይቀጥላል። እነሳሱ ያላማረኝ የፋሽስት መንግሥት፣ አወዳደቁን ለማየት ጓጉቻለሁና፣ የደብዳቤዬን የብዕር ስም እንደሚከተለው ሠይምልኝ። ባንገናኝም ደኅና ሁን።




ያንተው

141  10  67  98  48


( ስ መ — ም ሥ ጤ ር )





# ዋርድያሽ ብዛቱ

" አይ አንቺ እመቤት ፣ ዋርድያሽ ብዛቱ!
ሲለው አንበሳ ነው፣ ወይም ንሥር፣ ዐይነቱ!
ሲወጣ ሲገባ ፣ ሲቀየር ባመቱ።
ኧረ መቼ ይሆን? ራስሽን ችለሽ!
ያን ዐይነት ዋርድያ፣ የማያስፈልግሽ።
በፊት ጥሎሽ ሔዶ፣ የገባው ጐረቤት፣
ጥሞታል መሰለኝ፣ ያስባል ለመምጣት፣
እንደገና ሲያድር ፣ ላንቺ ዋርድያነት!!"



# የእብደት አንድምታ

ምንድር ነው ይባላል፣ደግሞስ ምን ይሉታል?
መሰሉን ሰው ፍጡር፣መሰል ሰው ሲያጋድል!

  ኧረ ምን ይሉታል፣ይህ ዓይነቱን ድርጊት?
  ሰው በሰው ጨክኖ፣ እየሰጠ ብረት!
  አንድን ሕዝብ ሰያዩቶ፣እርስ በርስ ሲያራኩት፣
  ሌላ ትርጉም የለው፣ነው እንጅ ተራ እብደት!!

መሰሉ ሰው ፍጡር፣ አውሬ እየመሰለው፣
እያቀጣቀጠ፣ድራሹን ካጠፋው፣
ከዚህ የተለየ፣እብደት ምን ቦታ አለው?!


  ካላበደ በቀር፣ ልቡ ካልተነካ፣
  አይችልም የሰው ልጅ፣በግዳይ ሊረካ!

ጤነኛ የሆነ፣ ኅሊና ያለው ሰው፣
ሰተራብ እንጀት፣ጥይት ሊሰግሠው?

  ብናምንም ባናምንም፣እንዲህ አድርገዋል፣
  ባሩድ ነጋዴዎች፣ በሰው ነፍስ ከብረዋል።

ወደድንም ጠላንም፣ያለንበት ምድር፣
መለወጡ አይቀርም፣"ግሎባሉ ኦርደር"!
የሚያጋድል ኃይልም፣ለዘለዓለም አይኖር ።

  እስከዚያው ድረስ ግን፣በጣም የሚገርመው፣
  ቀራጡን አጥፍተው፣ምሁሩን አግረው፣
  ስንቱን ሀገር ወዳድ፣ጎልጎታ ከተው!
  እንደወፍ አከናፋት፣ትውልዱን ሰጣብረው፣
  አሁን "ሰላም" አለህ፣"ነፃነት"ጠቅላላው!
  "እንደፈለግህ ብረር!"፣የሚሉት ዕብሪት ነው!



# እየመረረ የሚጣፍጥ



## አብርሒት

ዛሬም ትጥቋን አልፈታችም!

የሚያታግለው እስካለ ድረስ ፣ የጠብመንጃዋ

አፈ-ሙዝ ፣ የጠላትን ፉሽስታዊ ጠረን እያነፈነፈ

በመቅጣት ላይ ነው።

(የጠፍ. ቁ.8)

# መንደርደርያ

ዩኒቬርስ ወይም ፅንፈ–ዓለም፣ በመንታ ባሕርያት ይመሠረታል። ውጥኑም ሆነ ጭርሱ ይኸው ነው። "ይን–ያን"። የሥምረትና የፅርረት መሠረቶች ናቸው። አንፃርያንም። ጥምር ሰማይ ስንል መሬት አለ። እሳት ስንልም ውሃ። ከብናኝቱ ዐካለ–አቶም፣ የነዚህ መንታ ዐካላት መፈልቀቅ፣ ይህን ያህላል ብለው የማይገምቱትን ኃይል–ጉልበት ያበረቁትን ያህል፣ በሌላም ገጻቸው ያንኑ ያህል ለተለያዩ ውጤቶችና ምርቶች ምንጮች ናቸው። ዓለማችን ባጠቃላይ፣ ባሕርየ–መልካቸው ይለያይ እንጅ፣ የነዚህ መንታ ግማደ–አካላት (ኤሌመንትስ) ነፀብራቅ ነው። በነሱ መጋባትና በነሱም መፋታት፣ የዓለማችን መንገኒቃዊ ኩነት ይካሔዳል።

ከነዚህ ባሕርያት መግለጫ አንዱ ሰው ነው። የሰው አካላዊ ምንታዌነት፣ ከተገኘበት ወቅት ጀምሮ እውቅ ነው። ምንታዌነቱ ላዲስ ምርታዊ ልደት ምክንያት ነው። አንዱ ያለ ሌላው፣ ሌላውም ያለ አጣማጁ መኖር የሚችል ቢሆንም፣ መባዛትም ሆነ መሰሉን ማምረት አይሆንለትም። ስለዚህም ወንዱና ሴቱ በየራሳቸው ቅርፀ–አካላት እንዲኖሩ ሆነ። በመሆኑም በግንኙነት ይራባሉ። ይህ ነባር ሕግ ሆኗል።

ሌላው የምንታዌ ባሕርያት መግለጫ፣ ጠባይ ነው። እንደማናቸውም ሌሎች ጥምር ባሕርያት ሁሉ፣ ጠባይም በመሠረቱ ሁለት ዐይነት ነው። እነዚህ በየበኩላቸው ደግሞ፣ የየራሳቸው ዘርፎች አሏቸው። ዋናዎቹ ግን፣ ክፋትና በጐነት ናቸው። በተለያዩ መልኮቻቸው ይገዝፋሉ። ክፋት በራስ ወዳድነት ቀርቦ እንደሆነ፣ በጎነት ደግሞ በጋርዮሽ አፍቃሪነት ይከሰታል። እነዚህ ጠባዮች በመሠረተ–ባሕርያቸው፣ በባለ ኅሊናው ሰው የሚገለፁ እንጅ፣ የነጠላ ራሳቸው ግለኛ ሕላዌ የላቸውም። ሰውን ተዋሕደው፣ ሰውን ሙጥኝ ብለው፣ በጥገኝነት የሚኖሩ ናቸው። እንዲያም ሲል፣ በሌሎችም ፍጡራን ላይ አልፎ አልፎ መታየታቸው አልቀረም።

ይህች አጭር ልቦለድ ታሪክ በነዚህ መንታ የሰዎች ባሕርያት ላይ የተነደፈች ናት። ጭብጡ፣ በሀገራችን የለውጥ ሣኒታ ላይ የበረቀ ነው። ለማኅበረ–ሰባዊ በጐነት የምታስባዋን አብርሒትን፣ ለግሉ ደኅንነት ከሚያስበው ወንድሚ ጋር እየነፃፀረ ማቅረቡ፣ የክፋትንና የበጎነትን እርቃነ–ምንነት ባደባባይ ለማጋለጥ ታስቦ ነው። ይህችን ስንጣሪ ሓሳብ፣ በትልቁ አጉልተን ብንመለከተው፣ በጊዜያችን ያለውን የሥልጣን ቡድንና፣ ለነፃነቱና ለመብቱ፣ ለፍትሕና ለማኅበራዊ ብልፅግናው ከሚታገለው ህዝባዊ ኃይል ጋር ያለውን ሁኔታና ትንቅንቅ ቁልጭ አርጎ ያሳያል። እግረ መንገዱንም ነፃነትን ያህል ክቡር ነገር ለማግኘት፣ ምን ያህል የመረረ ትግልና መሥዋዕትነት እንደሚጠይቅ ለማሳየት፣ ከትግሉ ጎራ ይወስድና ያለውን ቸነፈር፣ መከራ፣ ሥቃይ ያሳያል። የትግሉንም ክቡርነትና ቆራጥነት ለማዘከር ካንድ አብራክና ካንድ ማኅፀን የተገኙትን ያንድ አባትና እናት ልጆች፣ በደም ደረጃ ያታግላል። ድርጊቱ ልቦለድ ይባል እንጅ፣ በዚች በኩንትሿ የትግል ዓመታት ውስጥ፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ቤተሰቦች ውስጥ በብዛት የተፈፀመ ነው። የአስተሳሰብ ዝምድና ከሌለ፣ የሥጋ ዝምድና ብቻውን ሰዎችን ማወዳጀት እንደማይችል በማዘከር፣ የሰው ልጆችን የርዕዮተ–ዓለም አንድነት የሚጠይቅ የገድላዊ ታሪክ ትይታ ነው። የገድሉን ታሪካዊ ርዕስ፣ "አብርሒት" ብሎ መሠየሙ አቋራጭ በሆነ ነበር። ግን በተመሳሳይ የገድል ታሪክ ይዘት ላይ፣ ተቀዳሚነት ሊሰጠው የሚገባው፣ የገድሉ ታሪክ አቀንቃኝ ግለ ሰብ ሳይሆን፣ የገድሉ ታሪክ አቀንቃኝ ሐሳብ መሆን ስላለበት፣ ከ "አብርሒት" ርዕስነት ይልቅ የ "እየመረረ የሚጣፍጥ" ርዕስነት ተመረጠ። ትግል በተካሔደባቸው ሀገሮች ውስጥ፣ ይህን መሰል የገድል ታሪክ ሥነ ጽሑፋዊ ዥማ የሳንሡር ግድቦችን ሳይቀር እየደረመሠ ጐርፏል። በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ በጅምላ አነጋገር ሳቢያ፣ ለጭቁን ወገን የሚቀጩ የወታደር ወገኖች ቢኖሩ "ከኑግ የተገኘህ ሠሊጥ፣ አብረህ ተወቀጥ !" እንዲሉ፣ በድምር ተኩንነው ይሆናል። ይሁን እንጂ ያ ክቡር ዝንባሌ ያላቸውን ተራማጅ ወታደሮች፣ ታሪኩ አይመለከታቸውም። የፋሽስት አርጋጅ አንጋጅ የሆኑትን ግን አይምርም። አብርሒት ወንድሚን እንደ አባት እናት





ልጅነቱ፣ የተፈጥሮ ስሜት ነውና፣ አልጠላችውም ነበር። ግን የወንድሚ የበስተኋላ ኢኩኖሚአዊ ዝንባሌውና፣ ለገዛ ጥቅሙ ብቻ የመንሰፍሰፍ ስሜቱ፣ ያስከተለበት ባሕርዩ ነው፣ ያጣላትና ወንድምነቱንም ያስጠላት። በዓለማችን ላይ፣ ዘርዝረንና መንዝረን ሳናየው እየቀረን ይሆናል እንጅ፣ በየትኛውም ምድርና በማናቸውም ሕዝብ መካከል የሚኖሩ ተቃርኖ ሁሉ አብርሒትን ከወንድሚ ጋር ሊያቃቅራት የቻለው፣ ለግለ–ሰብ ርካታ የሚደረግ የኢኩኖሚ፣ እንስፍስፍታ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ግለ–ሰብአዊ የኢኮኖሚ እንስፍስፍታ፣ እርቅ አይፈታውም። ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ ያህል ፋታ ይሰጥ እንጅ፣ እንስፍስፍታው ለሚፈጥረው ተቃርኖ፣ እርቅ ብቻውን መሠረታዊ ዋስትናም ሆነ ውጤት ሊወጣው አይችልም። ስለዚህም ነው፣ የኢኮኖሚ እንስፍስፍታ ያናከሳቸው ሁሉ፣ ወደዱም ጠሉ፣ ለፍልሚያ የሚቀርቡት። የበዝባዥና የተበዝባዥ መደቦች ትንቅንቅና ፍልሚያ፣ ከዚህ ዓይነቱ የነአብሪሒት ገድል ተለይቶ አይታይም።

በጎነት ከነቤተሰቡ፣የክፋትን ጆሌ ድል ለመምታት፣ የሚጠይቀው መሠዋዕትነትና ቆራጥነት፣ ቀላል እንዳይደለ፣ በጨረፍታም ቢሆን ታሪኩ ያሳያል። ከጠቅላላ ሠንኰፉም ጋር እስከ መጨረሻው በታትኖ ለመጣል፣ የረዥም ጊዜ ትግል እንደሚጠይቅ ይጠቁማል። በረዥም ዘመናት አታጋይነቱ አንፃር ሲታይ፣ መራራነቱ እሬት ነው። ከበጋና ክረምት፣ ከሞያሌና ተባይ፣ ከቀንጥርና ከአሜከላ፣ ከንዳድና ከበረሐ ... ጭምር ስለሆነ፣ ትግሉ መራራ ነው። የኋላ ኋላ ግን ድል የማይቀር ነውና፣ ጣፋጭነቱ የምሬቱን ያህል ማርማ ነው።

ይህች ልብ–ወለድ ታሪክ፣ በሌላ ገጿ አንድ እውነታ ፍንትው አርጋለች። "ኢትዮጵያውያት በትግሉ ዓለም የሉበትም" በሚለው ሐሜታ አንፃር፣ ቁጥራቸው አይብዛ እንጅ፣ እነ አብርሒትም ከነሞግዜራቸው ጋር ዛሬም እንዳሉ ጠቁማለች። በተለይ ደግሞ፣ የጐራው ትግል እየተራዘመ በሔደ ቁጥር፣ በሚያከማቸው ተመክሮ፣ ይብልጥ እየደረጀና እየደመቀ መሆኑ ባይዘነጋም፣ በመጀመርያ ወቅት የነበረውን ችግር አጉልቶ መግለጹ፣ የ "እየመረረ የሚጣፍጥ" እድገታዊ ሁኔታውን ለማብሠር ተብሎ ነው። ለማንኛውም፣ የግል ፍላጐቱን ገድሎ፣ ከሕዝብ ጋር የቦደነ ሁሉ፣ መጨረሻ ግቡ ጣፋጭ እንደሆነ ይረዷል።

# እየመረረ የሚጣፍጥ

( በጉራው የትግል ትዝታ ላይ የተመሠረተ ገድል )

"...በተጨማደደችና በቀረፈደች የስልቻ ኮፋዳ ውስጥ፣ ጭብጦ አዝላለች። የገብስ ወይም የስንዴ ቢሆን በበጀ። የጓያ ጭብጦ ነው። ገንፎ ቢሆንማ ኖሮ፣ እግር ያንሻፍፍ ነበር። የአኮፋዳው እንዲያ መቀርፈድ፣ የጭብጦውን ቅባት–አልባነት ያስረዳል። ይህችም ጭብጦ፣ ለወር ዕድሜ የማታወላዳ፣ የወር ስንቅ መሆንዋ ነው። የጥይት ፋጨትና የባሩድ ጠረን ጥቂት ሰከኖ፣ እፎይታ ስታገኝ ጠዋትና ማታ የምትቀምሳት ቁርስና ራት ናት።

ከጭብጦዋ ድርቀት የተነሳ፣ ያለ ውሃ አትቀመስም። ካነገበቻት ኮዳ ውስጥ ባላት ውሃ፣ መዳፍ የምታህለውን ቁራሽ አርሳ፣ በውሃይቱ ጉርጉጭ ታረጋታለች። በየጉራው እሳት አይገኝም እንጅ፣ የነፈረ ውሃ ይበልጥ አርሶ፣ ለጉሮሮዋ እንንዲያመች ባደረገች ነበር። በየጉራው ስትወጣና ስትወርድ፣ "በልቶ መጥገብ" የሚባለውን ሐሳብ፣ ከረሳችው ዓመታት አልፈዋል። አልፎ አልፎ ቢያጋጥማትም ልምዱን ስለረሳችው፣ እምብዛም አትጨነቅለትም። ከተውንም የጉራውን አባል ጓዶች፣ በምግብ እጦት አንፃር፣ አልፎ አልፍ የሚያጋጥማቸውን በማስመልከት፣ ቀደም ሲል የነፃ ማውጣት ትግል በተካሔደባቸው ሀገሮች፣ የቬትናም፣ የቻይናና የሌሎችንም ታጋዮች፣ የደረሱባቸውን መሰል ችግሮችና የተቋቋሙባቸውን ዘዴዎች በመጥቀስ፣ እንደ ተመክሮ በማቅረብ ታፅናናቸዋለች፣ ታጉለብታቸዋለችም። በተለይም አዘውትራ ከምትነግራቸው "የችግር መቋቋም" ታሪክ ውስጥ፤ ፋሽስቱ ሙሶሊኒ ሀገራችንን ሊወር መጥቶ በነበረበት ጊዜ፤ ሀገራችንን በባዕዳን ወራሪዎች ላለማስደፈር፣ በዱር በገደሉ ተሠማርተው ግራዚያኒን ከነሠራዊቱ

ያንበረከኩት ታጋይ አባቶች፣ የከፈሉት መሥዋዕትነት ይገኝበታል። ከዚህም አንዱ ትንግርት፣ ስንቃቸው ቢያልቅባቸው፣ የዘየዱት መላ ነው።

ሕይወታቸውን አራዝመው፣ የጀመሩትን ትግል ከግብ ለማድረስ ሲሉ "ስንቅ የጫኑበትን ስልቻና መጫኛ፣ በውሃ እያራሱ አኝኩ ከመምጠጥ ጀምሮ፣ በመጨረሻም፣ አህያዋን ራሷን ነፍስ–አድን እስከማድረግ ድረስ"፣ ተጠቅመውባታል። እንዲህ መሰሉን ማበረታቻ ተመክሮ፣ ላብሮ ዘመት ጓዶች በማስረዳት፣ ልባቸው ሆነ ቀራጥነታቸው፣ ከብረት የጠነከረ እንዲሆን በማድረግ፣ ለማንኛውም ዐይነት ችግር የማይበገሩ ታጋዮች ለመሆን አብቅታቸዋለች። በበኩሏም፣ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ያለበትን አብዮታዊ ግዴታ ለመፈጸም ስትል፣ በፍፁም ቆራጥነት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፖርቲ "ኢሕአሠ" በመባል ለታወቀው የጦር ክንፉ፣ ከአንደኛው የብርጌድ ሠራዊት ውስጥ፣ በአባልነት ተሠልፋ፣ ከግፈኛው የፋሽስት ጦር ጋር ስትፋለም፣ ዐመታት አልፏታል።

ስሟ አብርሒት ይባላል። ኸያ ስድስተኛ ዐመቷን ያገባደደች፣ የዩኒቨርሲቲ ምርቅት ናት። ለነገሩማ፣ ካንድ ኩባንያ ውስጥ ተቀጥራ፣ ብዙ ገንዘብም ትዝቅ ነበር። ረዥም ጊዜ ግን አልሠራችም። አከባቢዋን ለማረጋጋት በማሰብም፣ እንደ ዘመኑ ኩረዳ፣ መኪናም ቤትም ነበራት። ወላጆቿም፣ ደህም ሀብታምም ያልሆኑ የማዕከላዊ ኑሮ ባለቤቶች ነበሩ። ለቤቶቿ ሁለተኛ ልጅ ናት። "ወንድም ጋሼ" የምትለው ታላቅ ወንድሟ፣ ከሐረር የጦር አካዳሚ የተመረቀ፣ የሺ አለቃ ነው። ወታደር ከሆነበት ወቅት ጀምሮ እስኪጨረስ፣ ከወንድሟ ጋር ተጣጥመው አያውቁም። ገና ድሮ፣ ወታደር ለመሆን የቀረጠለት ነው፣ የከረረ ጠብ ያበቀሉት።

ወላጆቻቸው፣ እንዳህያ ጡት ሁለት ብቻ የሆኑ ልጆቻቸውን፣ በወንድምነትና በእህትነት ደረጃ ለማቀራረብ ያልጣሩበት ጊዜ የለም። ከቶውንም በማስታረቁ የረዷቸው መስሏቸው፣ ያልሠገዱለት ጠንቋይ፣ ያልተሣሉለት ታቦት አይገኝም። ሊያስታርቃቸው የሞከረ፣ የወዳጅና የሽማግሌ ጋጋታ፣ ቁጥሩ አይታወቅም። በልጆቻቸው አለመስማማት፣ ቤተ–ሰባቸው ከቀሰለ ዘመናት አልፎታል። ከዚህም የተነሣ፣ ወላጅ አባትና እናት፣ ደስ ብሏቸው የዋሉበትና ያደሩበት ዘመን፣ በቁጥር





ነው። አንዴ አብርሒትን፣ አንዴ ሻለቃ ልጃቸውን ለማስታረቅ ሲያባብሉ፣ አፍላ ዘመናቸውን ገፍተው፣ በማዕከላዊ እድሜ ፍፃሜያቸው ላይ ይገኛሉ። በልጆቻቸው መናቆር የተነሣ፣ "ምን አልንህ" እያሉ የቁልቢውን ሳይቀር ያማርራሉ።

አብርሒት፣ ገና ከሕፃንነቷ ጀምሮ፤ ጠሊቅ አስተሳሰብ ያላት፣ በረዥሙ የምታስብ፣ የኅብረተ–ሰብ ችግሮች ዘወትር የሚከነክናት፣ ኋላም በትምህርት ከጐለመሰች አንስቶ፣ ማንኛውንም ሁኔታ፣ ሣይንሳዊ በሆነ ዐይን የምትመለከት፣ ችግሮችን ሁሉ፣ ከጭብጡ ሁኔታ በመነሣት፣ በሳይንስ ይዘት የምትመረምር፣ የሶሻል ፍልስፍና ጠበብቶችን ትምህርት፣ ከአከባቢዋ ሁኔታ ጋር የምታገናዝብ፣ ሀገሯም ሆነ ጠቅላላው ዓለም ቅንና ትሁት በሆነው በሠራተኛው የላብ አደር መደብ የሕዝብን ዲሞክራሲያዊ ትርታ የሚያዳምጥ የበላይነት መተዳደር እንዳለበት የምታምን፣ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ጥቂት መሰል ሔዋንያት ልጆቿ ውስጥ አንዲቱ ናት። በማታምንበት የኅብረተ–ሰብ አድኀሪ ሥርዓት ውስጥ ያለ ውዴታዋ ስትኖር፣ ዓመታት አልፈዋታል። ግን ያን ሁሉ ዓመታት፣ በዝምታ አላቃጠለቻቸውም። ቀዳዳ ባገኘች ቀጥር፣ አድኀሪውን ሥርዓት ስትቦረቡርና ስትገዘግዝ ኖራለች። ይህን ሁሉ ታደርግ የነበር፣ በኅቡዕ ነው።

ታላቅ ወንድሟ፣ ወታደር እስከሆነበት ጊዜ ድረስ፣ ነፍሷ እስኪጠፋ ትወደው ነበር። የሁለቱም ዕድሜ እየጨመረ በሔደ ቁጥር፣ ያስተሳሰብ አድማሳቸው እየሰፋና የኑሮ ምርጫቸው እየጠበበ መጥቶ፣ ከማይጣጣሙበት ደረጃ ላይ ደረሱ። ቀደም ሲል ግን፣ በዚያ በሞቀ ወላጆቻቸው ቤት ውስጥ፣ በዚያ ተድላ ደስታ በሰፈነበት ቤት ውስጥ፣ በዚያ ወላጆችና ልጆች እኩል ይናገሩበት፣ ይዝናኑበት በነበረበት ቤት ውስጥ፣ ለሰዓት ዕድሜ እንኳ ሲለያዩ፣ ናፍቆታቸውን አይችሉትም ነበር።

በልጅነታቸው ዘመን ወላጆቿ፣ ለሷ አዲስ ልብስ ገዝተው፣ ለወንድሟ ሳይገዙ ሲቀሩ፣ ታቀልጠው የነበረውን የተቃውሞ እሪታ፣ አሁን አንታረቅም ብለው ላስቸገሯቸው ልጆቻቸው፣ የቀድሞ ፍቅር፣ ትዝታ ሆኖ፣ ውስጥ ውስጡን ይበላቸዋል፣ ይቆጠቁጣቸዋል፣ ወላጆቻቸውን። አብሪሒትና ወንድሟ በትምህርት

ዘመናቸው ጊዜ፣ የነበራቸውን ፍቅር የተመለከተ የጉረቤት ሰው፤እንዲያ ይተሳሰቡ ይረዳዱ በነበሩበት የወጣትነት ውቅት፣ ያጤናቸው የትምህርት ቤት ጓደኛ፣ በወላጆቻቸው ጠለላ ስር፣ ባንድነት ይኖሩ በነበሩበት ዘመን፣ ያስተዋላቸው አዛውንት ሁሉ፣ በነበራቸው ፍቅር፣ በሚያሳዩት መተሳሰብና መረዳዳት፣ አበክሮ ያልቀናባቸው ሰው አይገኝም ነበር። እንዲያው በሰፈራቸው ውስጥ ተንኳሽና በጥባጭ፣ ዓመለኛና ረባሽ የሆነ ልጅ ያለው ወላጅ ሁሉ፣ "ምነው እንደ ነአብረሒት ብትሆን !" እያለ የጥሩ ምግባርና ፀባይ፣ ምሳሌና አርአያ እስኪሆኑ ድርስ፣ በይፋ መስክሮላቸው ነበር። የሠፈራቸው ፋደት ሁሉ ባስቸገረ ቁጥር፣ "ምንው ከነአብርሒት ብትማር !" ያልተባለ አይገኝም። በርግጥም፣ አብርሒትና ወንድሟ፣ ዕለት በዕለት ያሳዩት በነበረው መልካም ምግባርና ጥሩ ጠባይ አንፃር፣በጎ አርአያነታቸው፣ በተመክሮ ደረጃ መቅረቡ አያስደንቅም ነበር። በመንደራቸው ውስጥ፣ በሕመም ወይም በእርጅና ምክንያት መጓዝ ተስኖት በመንገድ ላይ ያገኙትን ሰው ሁሉ፣ ከሚፈልግበት ስፍራ ሳያደርሱት እንደሌሎች አይተው እንዳላየ አያልፉትም።

ባካቢያቸው የሚገኙ አረጋውያንና ባልቴቶች ሁሉ፣ በየመልኩ በነአብርሒት የልተረዳ አይገኝም። የዘመመ ጎጆውን ያላቃኑለት፣ የተቀደደ ልብሱን ያልሠፉ ለት፣ የሚየንገበግብ ሞያሌውን ያልፈነቀሉለት፣ እንዲያም ሲል የተጠማ ጉሮሮውን፣ የተራብ አንጀቱን ያላረሱለት፣ የመንደሩ ችግርተኛ አይገኝም። በዚያ የትምህርት ዘመናቸው ጊዜ፣ የኢኮኖሚ እጥረት አንበርክኳቸው እንጅ፣ እንደምኞታቸውማ ቢሆን ኖሮ፣ ስንቱም ባራመዱ ነበር። ሆኖም በዚያ አቅማቸው እንኳ፣ የማታ ትምህርት ቤት ከፍተው፣ መሠረተ–ትምህርት በነፃ ሰጥተዋል። ለአርአያነት የምታበቃ ትንሽ መጻሕፍት ቤት ከፍተው፣ አንባብያንን ረድተዋል። እግረ መንገዳቸውንም፣ ከኅብረተ–ሰቡ ያስተሳሰብ እድገት ጋር የሚሔድ፣ የንቃት ቅስቀሳ፣ ዐቅማቸውና አካባቢያቸው እስከመጠነ ድረስ፣ በየጊዜው አካሒደዋል። የነሱ ጊዜያዊ ርዳታ በቂ አለመሆኑን በማስረዳት፣ ቀዋሚና መሠረታዊ ለውጥ





ማስፈለጉን፣ ባደባባይ ተናግረዋል። በዚህና በመሰለ ሌላ ድርጊት ተወንጅለውም፣ በዚያ በወጣትነታቸው ዘመን፣ ላጭር ጊዜ ታስረዋል፣ ቸብ ቸብ ተደርገዋልም።

ያ የወጣትነትና አፍላ የትምህርት ዘመናቸው፣ እንዲህ የመሳሰለውን ተግባራት ሲያንፀባርቅ ቆይቶ፣ አንደኛው ጎን በድንገት ሸብረክ አለና፣ ሌላ ያልተጠበቀ መልክና ሁኔታ ማሳየት ጀመረ። ይኸውም፣ ያብርሒት ታላቅ ወንድም፣ የድሮው ተማሪ፣ የዛሬው ሻለቃ፣ የጠባይ አዝማሚያ ጉዳይ ነው።

አብርሒት፣ ገና አሥረኛ ክፍል ሳለች፣ ወንድሟ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ላይ ነበርና፣ የሁለተኛ ደረጃን መልቀቂያ ፈተና መውሰድ ነበረበት። እንዳጋጣሚም፣ ለስድስት ፈተናዎች ተቀምጦ፣ በአራቱ ብቻ ሲያልፍ፣ በቀሩት ወደቀ። በዚህም ውጤቱ ምክንያት፣ ዩኒቬርሲቲ የመማር ምኞቱ፣ ለጊዜው ተቀጨ። ያልጠበቀው አጋጣሚም በመሆኑ፣ እድሜ ልኩን ታይቶበት በማይታወቅ ሁኔታ ተበሳጨ። ይህ በሆነ፣ በመንፈቅ እድሜ ውስጥ፣ ያ፣ በጎ ምግባሩና ተራማጅ ባሕርዩ ሁሉ ነፍተው እንዳስተነፈሱት የላስቲክ ነፋሪት፣ ጨርሶ ሚሸሸ። እንዲያ ይንሠፈሰፍላቸው የነበሩትን ወላጆቹን፣ የመንደሩን ችግርተኞችና የነፍሱን ያህል ይወዳት የነበረውን፣ እህቱን አብርሒትን ሳይቀር፣ ርግፍ አርጎ ተዋቸው። የደረሰበትን የመንፈስ ጭንቀት የተቋቋመ መስሎት፣ አንዳንድ ጓደኞቹ እንዳደረጉት ሁሉ፣ ሐረር የጦር አካዳሚ ለመግባት፣ በግሉ ወሰነ። በዚያም ወቅት ይህ ውሳኔው ሌላ አማራጭ የማይገኝለት መሰለው።

ይህን ውሳኔውን የነገራት ለት ነው፣ ከእህቱ ከአብርሒት ጋር፣ እርቅ የለሽ ጸባቸው የተጠነሠሠው። ለወራት ያህል ገሸሽ አርጓት ከቆየ በኋላ አንድ ቀን ማለዳ፣ ቁርሳቸውን በልተው እንደጨረሱ፤

"አብርሒት ! አንድ ውሳኔ አድርጌያለሁ !" አላት፣ እንደምትቆጣው፣ እንደምታዝን፣ እንደማትቀበለው አውቆ፣ ሲፈራ ሲቸር።

"የምን ውሳኔ ?" አለችው እንደመደንገጥም እንደመቆጣትም እየቃጣት፣

"እንደምታውቂው፣" አለ በሰላላ አንደበት እንደመዝናናት ብሎ፣ "ፈተና ከወደቅሁበት ጊዜ ጀምሮ፣ ደስ ብሎኝ እንዳልኖርኩ፣ በቅርብ ሆነው ካዩኝ ሰዎች

ውስጥ፣ አንቺ አንዷ ነሽ። ጭንቀቴ ከጊዜ ወደጊዜ እየባሰና እየከፋ ሔደ እንጂ አልቀነሰም። ከአሁኑ የመቆጣጠሪያ ዘዴ ካላገኘሁ፣ ለሌላ ችግር ይጥለኛል ብዬ ስለሠጋሁ ...” ብሎ ሊናገር ሲቀጥል፤

“እኮ ምን ልትሆን አሰብክ” ሐሳቡን ለማወቅ እየትቅበጠበጠች ጠየቀችው፡

“እንደምታውቂው በአራት የማትሪክ ፈተናዎች አልፌአለሁ። ተመሳሳይ ውጤት አግኝተው እንዳደረጉት ሁሉ፣ ሰሞኑን ሐረር ለመሔድ ወስኛለሁ።” አላት እየተርበተበተ።

“ደኅናም አይደለህ እንዴ ! በዚህ ዐመቱ ማትሪክ መወደቅህ፣ ምንም እንዳይደለ ብዙ ጊዜ ተነጋግረናል። ያንድ ጊዜ ፈተና መወደቅ፣ ያንተን የመማር ዕድል እስከ መጨረሻው የሚወስን እንዳይደለ፣ ተወያይተን አምነህበት፣ ለመጭው እንድትዘጋጅ አድርገናል። አሁን ደግሞ፣ ምን ዓይነት የሐሳብ ማዕበል ነድሎህ ነው ሐረር ልሒድ የምትለው ! ይህ ሐሳብህ፣ እማማና አባባ ጆሮጋ እንዳይደርስ አስብበት ...” ሐሳቡን ችላ ብላና አዋድቃ፣ ለመሔድ ከመቀመጫዋ ልትነሳ ስትከጅል፣ እጇን ያዘና፣ እንባ እየታነቀው፣ ከልቅሶ ባላነሰ አንደበቱ፤

“አብርሒት ! ውሣኔዬ ነው። ወታደር ለመሆን ቆርጫለሁ። የሐረሩ የጦር አካዳሚም ተቀብሎኛል። ይኸውልሽ ደብዳቤያቸው !” ብሎ ደብዳቤውን ሊያሳያት ወደ ኪሱ ሲገባ፤ አብርሒት፣ የቀትር ብራቅ የመታውን ሰው ይመስል፤

“አልሰማም ! ጆሮዬ አይሰማም ! ...” እሪ እያለች፣ እናትና አባቷ ወደ ሥራ ለመሔድ ከሚዘጋጁበት ክፍል ሮጣ ገብታ፣ መርዶውን ነገረቻቸው። በዚያንም ወቅት ነው፣ ወንድሟ ለጉዞ ያዘጋጃትን ትንሽ ሻንጣ ይዞ፣ በሚያስደንቅ ፍጥነት ባጠገቡ ባለ መስኮት ዘሎ፣ ወላጆቹም ሆኑ እህቱ ሳይገናኙትና ሳያማክሩት፣ ወደ ሐረር የመረሸው።

አብርሒትና ወላጆቿም፣ እንደ ዝማ የጐረፈውን እንባቸውን ጠርገው፣ እቅታቸውን ውጠው፣ በድንገት የተለያቸውን የቤተሰብ አባላቸውን፣ በአካል ሥጋ ሳይሆን፣ በልባዊ ተውኔት ተሰነባብተው፣ ከዚያችም ቀንና ሰዓት ጀምሮ፣ ለሁለት ዐመታት ጊዜ ሳይገናኙት ኖሩ። የሚያገኛቸው ሰው፣ ስለሱ በጠየቃቸው ቁጥር፣





“አጉቱን ሊጠይቅ ባላገር ሔዷል” እያሉ ይዋሹ ነበር። አብርሒትም፣ የወንድሟን፣ የቀድሞ በጐነት፣ ቅንነት፣ ታታሪነት፣ አርቆ አሳቢነት፣ በጠቅላላውም የነበረውን ተራማጅ አስተሳሰቦች እያስታወሰች፣ ስለ ወንድሟ የነበራት የጋለ ትዝታ፤ ጊዜ፣ ቀስ በቀስ እያለ፣ እስካበረደው ድረስ እየተንሠቀሠቀች ታዝን ነበር።

እንዴውም የምታለቅስበት ዐይኖቿ ጉድጉደው፣ የባሌ ውሃ ማቆር የሚያስችሉ ይመስላሉ። ወንድሟ ትዝ ባላት ቁጥር “ያን መሳይ ተራማጅ ወንድሜ፣ ወታደር ይሁን ‼ የገዥ መደብ ዋርድያ ! ለሚዘርፉትና ከጭቁን ሕዝብ ለሚበዘብዙት ሀብትና ንብረታቸው፣ ሕጋዊ ዘበኛ ! የጠሉትን ሁሉ ለመረሸን የሚታዘዝ፣ ሕጋዊ ገዳይ ! በጠቅላላው፣ የቦጥቧጭ መደብ፣ ሳይሠራና ሳይደክም ለሚዝቀው ጥቅም፣ ከተራው ውሻ ባላነሰ አገልጋይነት፣ ወታደራቸው ሆኖ ‘ለፓራሳይት’ ሕይወታቸው ሕጋዊ ጠባቂና አስከባሪ ይሁን ! ...” እያለች ሌት ከቀን ታነባዋለች።

አንዳንዴም፣ ቤተሰቡን ጥሎ ከጠፋበት ቀን አንስቶ፣ በዚያ የሐረሩ የጦር አካዳሚ የሚገኝበትን ሁኔታ፣ በዓይነ– ኅሊናዋ ስትመለከተውና በእህትነት ልቦናዋ ስታስበው፣ አንዳንድ ትርዒቶች እየተደቀኑ ይረብሿት ነበር። “ይኸኔ፣ ያን ሳንጃ የተለጐመ ጠበንጃ ተሰጦት፣ ያን ያልታደለ ጭቁን ሕዝብ፣ እንዴት ማረድ እንዳለበት፣ እንዴት ማሰቃየት እንዳለበት፤ በፈንጂ፣ በቦንብ፣ ባዳፍኔ፣ በመትርየስ፣ በታንክ፣ ለነፃነቱ፣ ለዲሞክራሲው፣ ለኢኮኖሚያዊ ፍትሁ፣ ለተስተካከለ ኑሮው፣ አምፆ የሚነሳን ጭቁን ሕዝብ፤ እንዴት አድርጐ ያለርኅራኄ ማጨድና ማጥፋት እንዳለበት፣ ይማራል ‼ በባዕዳን መንግሥታት ብሔራዊ ክብራችን ተደፈረ፣ ብለው የሚነሱትን ሀገር ወዳዶች፤ አምባገነን መሪ አንፈልግም፣ ብለው የሚነሱትን ዲሞክራቶች፣ በሳይንስ ላይ የተመሠረተ ኅብረተ–ሰብ እንፈልጋለን ብለው፣ የሚታገሉትን ተራማጆችና ሌሎችንም የነፃነት ታጋዮች ሁሉ፤ እንዴት አድርጐ በማያዳግም ሁኔታ፣ ማጥፋት እንዳለበት፤ ይኸኔ በሐረሩ የውትድርና ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት፣ ትምህርቱ እየተሰጠው ነው ‼ ይኸኔ መሠረታውያን የወታደር ዲሲፕሊንና ግዳጆች ተብለው፣ የሚቀርቡትን፤

እንደ "... የበላይ የሚያዝህን፣ አለአንዳች ተቃውሞ ተቀበል፣ ለበላይህም ሆነ ለቅርብ አለቃህ፣ ፍፁም ታማኝና ታዛዥ ሁን፤ ለግዳጅ ስትጠራ ለምን ብለህ አትጠይቅ፤ ለግዳይ ግዴታህ ምሕረት አታሣይ፣ ለቆምህለት ዓላማ ለሕይወትህ ሳትሣሣ ተሠዋ ..." ያሉትን፣ የሞራል ምናምንቴዎች በሰላ አንደበታቸው በመስበክ፣ ያንን ሕዝባዊ የነበረ አእምሮውን፣ ጠዋት ማታ ቱር አርገው ያጥቡታል። ይኸኔ፣ "ለጭቁን ሕዝብ መሞት አለብኝ" ይል የነበረውን ውሣኔውን "ለመሪህ ክብር ስትል፣ ሞትን አትፍራ" በሚለው ትምህርታቸው እየለወጡት ነው፡ ..." እያለች፣ አብርሒት ብቻዋን፣ በሐሳብና ባሳዛኝ የትዝታ ባሕር ውስጥ የምትሰጥምባቸው ጊዜያቶች፣ አጭር አልነበሩም። አንዳንድ ቀንማ፣ በብስጭት ተውጣ፣ አንጉሉን ነካ አርጐት እንደወፈፈ ሰው፣ ብቻዋን እየተናገረች በየመንገዱ ትሔድ ነበር። አዘውትራ የምታነበንበው የብቸኛ ንግግሯ፣ እንዲህ የሚል ይዘት ነበረው፤

"...አውቃለሁ፣ ወንድሜ በፊት ተራማጅ አስተሳሰብ ነበረው። ባንዳንድ ነጥቦች ላይ ብስለት እንዳልነበረውም አምናለሁ። አንዳንድ ጊዜም፣ እስኪወጣለት ድረስ፣ በስሕተቶቹ ላይ እንጨቃጨቅ ነበር። ያላሟላቸውን ጥራቶች ወደፊት እንዲዘጋጅባቸው እየተስማማን ያለፍንባቸው፣ የንትርክ ጊዜዎች ጥቂት አልነበሩም። ያስተሳሰብ ብቃት፣ እኔም ቢሆን እንደሌለኝ አምናለሁ። ... ግን ለምንድር ነው ! የፈተናውን መውደቅ አጋጣሚ ይዞ በመነሳት፣ ለዚህ አስደንጋጭና አሳዛኝ ውሳኔ የበቃው ? ይህን ጥያቄ፣ መላልሼ መመርመር ይኖርብኛል ‼ እንደሚታየኝ ከሆነ፣ ለዚህ ርካሽ ውሣኔው፣ የፈተናውን መውደቅ ሰበብ አርጐ ተነሳ እንጅ፣ በመሠረቱ ሁኔታው ሲተነተን፣ የተደበቀ ባሕርይ ክስተት ይመስለኛል። ፈተናው ሰበቡ ይሁንለት እንጅ፣ ማናው መነሾ፣ የራሱ ባሕርይ ለውጥ ይሆናል።

በርግጥኮ፣ ወንድሜ እንዴት ያለ፣ የጭቁን ሕዝብ ተቆርቋሪ ነበር ! ምናልባት በቅርብ ጊዜ፣ ከዚያች የቱጃር ልጅ ከሆነችው ሣፊያ ጋር፣ እንዲያ ብን ማለት፣ ያስከተለበት የባሕርይ ለውጥ የሆናል። አዎ በመኪናዋ እያዘለች በየ ሲኒማ ቤቱ፣





ቡና ቤቱ፣ ዳንስ ቤቱ ... ስታዞረው፣ ብዙ ጊዜ ሒስ አቅርቤለት ነበር። ለዚህ ወታደር የመሆን ውሳኔውና፣ ለባሕርዩ መንሸራተት፣ ዋናው ጉዳይና የዚቁ እንብርት፣ ከሣፊያ ጋር መግጠምና፣ በሱዋም በኩል ጭለንጭሉና ብልጭታው ለተያው፣ የካፒታል መሠብሰብና፣ ቱጃር የመሆን ስሜቱና ዝንባሌው ነው። ሌላው ቀርቶ፣ እንዲያ በትምህርት ችሎታው ታውቆ "ብልህ" የተባለው ወንድሜ፤ አድርጉትና ደርሶበት የማያውቀው፣ የፈተና መውደቅ ሁኔታ ያጋጠመው፣ ከዚችው ልጅ ጋር ተያይዞ፣ እፍ እፍ በማለቱ አይደል !

... እኔን ይበልጥ የሚያሳዝነኝ፣ ስንት ከባድ ምስጢር ስንካፈል ኖርን፣ ስንት የመሠረታዊ ለውጦች እቅድ፣ ስናውጠነጥንና ስናካሒድ ቆይተን፣ አሁን ለጠላት አገልጋይ ለመሆን፣ ወታደርነት መግባቱ ነው። ምስጢሬ ምስጢሩ በመሆኑና፣ በአሁኑ ወቅትም፣ የገዢው ክፍል የጥቅም ጠባቂ ወታደር በመሆኑ፣ ባሳየው፣ የመደብ ባሕርዩን የመክዳት ድርጊት፣ ከእንግዲህ መጠንቀቅ ይኖርብኛል። ማንነቴን፣ ከማንም ሰው ይልቅ ይበልጥ ስለሚያውቅ፣ አንድ ቀጥር ጠላቴ እንደሆነ ማመን አለብኝ። ወንደምነቱንም በጠላትነት መተካቱን ማመን ግዴታዬ ነው። በጣም የደነቀኝ ግን፣ ለብዙ ጊዜ እንዲያ የነበረ ሰው፣ ባንዳፍታ ቅፅበታዊ ለውጥ ማሳየቱ ነው። ..." እያለች በየመንገዱ ታነበንብ ነበር። ደግነቱ የምትናገረው በለሆሣሥ መሆኑ በጀ እንጅ፣ የሚሰማ ቢሆን ኖሮ፣ ለራሷም ሕይወት ያሰጋት ነበር።

አያልፍ የለምና፣ ጊዜና ወቅት፣ እንደፈሳሽ ዝማ፣ ዘወርዋራ የሕወይት ኪደቶችን እያሳየ ያልፋል። በአብርሒት ቤተሰቦች ላይ፣ የወንድሟ ወታደርነት መግባትና፣ የሱም ወላጆቹን ብቅ ብሎ አለመጠየቅ፣ እንዲያ ሞቆ በኖረው ቤተሰባቸው ላይ፣ የሐዘን ድባብ አጥልቶበት ቆየ። ይሁን እንጅ፣ በዚያ ረዢም የትካዜ ጊዜ ውስጥ፣ ወንድሟ ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ ከቤታቸው ባይመጣም፣ ከሉብት ከተማ ብቅ እያለ፣ ከዚያች ቱባ ወዳጁ ከሣፊያ ጋር መታየቱ ታውቋል። በተለይም፣ ባጭር ጊዜ በቀሠመው የሐረሩ ጾሮር ትምህርት አማካይነት "በመጀመርያ፣ በደንብ የሚያውቅህንና የቅርብህን ጠላት ባስቸኳይ ማጥፋት

አለብህ !" በሚለው መመሪያ ተሎ፣ ኀሊናው ብቻ ሳይሆን፣ ልቡናው ጭምር ታጥቦ ኖሮ፣ ያቺን ተራማጅ እህቱን አብርሒትን፣ በጅ አዙር ለማስገደል፣ ያልሞከረው ዘዴ አልነበረም።

ዓመት ባልሞላ ጊዜው ውስጥ፣ በሠፍያ ረዳትነት፣ ሦስት ጊዜ በመኪና ሊያስገጯት ሞክሮ፣ ለጥቂት አምልጣለች። ከተላኩ ዱርዬዎች፣ የድብደባ ሙከራ አንስቶ፣ ማንነቷን፣ ለፀጥታ ሰላዮች ሹማምንት እስከማጋለጥ ድረስ፣ እህቱን ለማጥፋት፣ ያልሮጠበት ሙከራ አይገኝም። በዚህም ሙከራው፣ እህቱን ለማጥፋት ባይሣካለትም፣ አብርሒት የሕይወቷን ያህል የምትከባከባቸውን፣ የጭቁን ሕዝብ መረጃ እንቡጥ ድርጅቶቿን፣ ለማዘጋት በቅቷል። አብረው አቋቁመውት የነበረውን፣ የማታውን ትምህርት ቤት፣ መጻሕፍት ቤትና የጥናት መካን፤ የፖለቲካ መልክ በመስጠት፣ ፖሊስ እንዲዘጉ አድርጓል። ለናትና ላባቷ አልነገረቻቸውም እንጅ፣ ሦስት ጊዜ ያህል፣ ከተማ ውስጥ ከሠፍያ ጋር አግኝታው፣ ልኩን ነግራዋለች። እሱም ዝተባታል።

ከሁለት ዐመታት ቆይታ በኋላ፣ አብርሒት፣ ያስራ ሁለተኛን ክፍል ፈተና በሚያስደንቅ ሁኔታ አለፈች። ሌላውን ትግሏን ሙሉ በሙሉ ባታቋርጥም፣ ለሠላዮች ላለመመቸትና ከወንድሚም ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ስትል በተአቅቦ ይዛው ቆይታለች። በወንድሚና በእህቷ መካከል ይካሔድ የነበረውን የቅራኔ መደባዊ ትግል፣ ወላጆቿ በጭራሽ አያውቁም ነበር። የበለጠ ሐዘን ላይ እንዳይወድቁ በማሰብም፣ ይህን ጉዳይ ላባትና ለናቷ ነግራቸው አታውቅም ነበር። ፈተና የማለፏን ዜና፣ ከነአብሒት ጐረቤት ከሚኖር፣ አንድ የድሮ ጓደኛው ሰምቶ ኖሮ፣ ይህን አጋጣሚ ምክንያት በማድረግ፣ በክረምቱ የዕረፍት ጊዜው፣ የረሳቸውን ቤተሰቦች ለማየት፣ ድንገት ከድሮ ቤቱ ከቸች ይላል። የልጅ ነገር የማያስችላቸው እናትና አባት፣ ያለፈውን በደሉን ሁሉ ረስተው፣ በጋለ ደስታ ተቀበሉት። ከዚያ በፊት ከከተማቸው እየመጣ ይምነሸነሽ ያልነበረውን ያህል፤ "ጊዜ ስላልነበረኝ እስከ ዛሬ ሳልጠይቃችሁ ቀየሁ !" እያለ ወሻከተላቸው። እንዳጋጣሚ እሱ በመጣበት ሰዓት፣ አብርሒት ቤት ስላልነበረችና፤ ከሔደችበትም ስትመለስ፣





የወንድሟን መምጣት፣ ገና በውጭ ከጐረቤቶች ስለ ሰማች፣ ላለመገናኘት ወስና ካንድ ጓደኛዋ ቤት ተመልሳ በመሔድ፣ ወንድሟ ተመልሶ እስከሔደበት ቀን ድረስ፣ ተደብቃ ሳትታይ ቀየች። እሊያ ያልታደሉ መከረኛ ወላጆቿ ግን፣ በሱ መገኘት የተደሰቱትን ያህል፣ በሷ መጥፋት ደግሞ፣ ያለመጠን ሲጨነቁ ሰነበቱ። ወንድሟ ለሣምንት ያህል በወላጆቹ ቤት በከረመበት ወቅት፣ ያቺን የዲታ ልጅ ሠፍያን፣ እጮኛው መሆኗን ከማስተዋወቁም በላይ፣ ወሽቱን፣ ከአብርሒት ጋር የሰላምታ ደብዳቤዎች እንደ ሚለዋወጥና፣ ባንዳንድ ነገሮችም እንደማይጣጣሙ ገልፆላቸዋል።

ደቂቃው፣ ለሰዓት፣ ሰዓቱ ለቀን፣ ቀኑ ለሣምንት፣ ሣምንቱ ለወር እያቋጠረ የዚያ አሳዝኝ ቤተሰብ ሁኔታ፣ እንዲያ እንዳለ፣ ዐመታት አለፉ። በዚያም የዘመናት ጉዞ ውስጥ፣ አብርሒት በፖለቲካ ትምህርት ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃ፣ የሚያባብል ወፋራም ደሞዝ ያለው ሥራ ተሰጥቷት፣ ባለ መኪና፣ ባለ ቪላ፣ ለመሆን በቅታለች። ያን ዘመን ሁሉ፣ ታደርገው የነበረው የኑሮ መልክ ሁሉ፣ በመምሰል ላይ የተመሠረተ፣ ፍፁም የማታምንበት ረጋ ሠራሽ ድርጊት ነበር። በልዩ ልዩ ፈተናዎች ታጥራ፣ በምሥጢር ተቆጣጣሪዎች ተወጥራ፣ የተያዘች መሆኑን ስለምታውቅ የልቧን ተምኔት፣ ለማንም አሣይታ አታውቅም ነበር። በዚህም ዝንባሌዋ፣ የረኩ ሰዎች ቢኖሩ፣ ተቆጣጣሪዎቿ የመንግሥት ሠላዮቿና፣ እንዲያ እንድትሆን ይመኙላት የነበረው፣ ወንድሟ ብቻ ናቸው። ማንነቷን፣ ቀደም ሲል ያውቋት የነበሩ፣ የጭቁን ሕዝብ ወገኖች ግን፣ "የኛ ተራማጅ" እያሉ ባዩዋት ቁጥር፣ ያሽሟጥጧት ነበር። አብርሒት ግን፣ በበኩሏ የምታምንበትን አቋም፣ ባደባባይ የምትገልጽበትን ጊዜና ቦታ ስትፈልግ የነበረች ናት።

ወንድሟም በበኩሉ፣ በዚያ የረዥም ዘመናት ቆይታ ውስጥ፣ ብዙ ለውጦችን አድርጐ፣ የለየለት ቱጃር ሆኗል። ያቺን የዲታ ልጅ የነበረች ልጅ፣ ሠፊያን መቀራኘቱም፣ ለዚህ የሀብታምነት ግቡ ረድቶታል። ከሐረሩ የጦር አከዳሚ እንደተመረቀ፣ ወዲያው ጋብቻቸው ተፈጽሞ፣ በሠፍያ አባት ረዳትነት፣ የቡና ርሻቸውን ለመቆጣጠር እንዲረዳቸው አስበው፣ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ባለ፣ የጦር

ክፍል ተመድቦ፣ የጭቁኑን የኢኮኖሚ ዐካል ሲግጥና ሲቦጭቅ፣ ዐመታት አልፈውታል። የወጣለትም ቱጃር ሆኗል። እንዴት ቱጃር አይሆን፣ ገቢው ባራት ማዕዘን ይጕርፋል። የቡናው እርሻ፣ የቢና ቤቱ ንግድ፣ ኋላም በድንገት በመኪና አደጋ ከሞቱት፣ የሦፊያ አባትና እናት የተወረሰ፣ ጠቅላላ ሀብትና ንብረት፤ (ለሀብታቸው ሲባል፣ መኪናቸው ውስጥ ፈንጅ አስቀምጦ ያስገደላቸውም ራሱ ነው እየተባለ ይጠረጠራል) በሺ አለቃነት ሥልጣኑ፣ ያንድ ክፍለ ጦር አዛዥ በመሆኑ፣ ካካባቢው በየምክንያቱ ከሚያጋፍፈው ሀብት ጋር ተደምሮ፣ ቢጠሩት የማይሰማ፣ የነጠጠ ሀብታም ለመሆን በቅቷል። እየዘረፈ ባገኘው ሀብቱም፣ ድፍን የሲዳሞ ሕዝብ ያውቀዋል። ያከባቢውንም ጭቁን ሕዝብ፣ በፈፀመበት ግፍ የማያዝንበትና የማያማርረው ሰው የለም።

ሁኔታውያን፣ በሁለቱም በኩል፣ ይህን መልክ ይዘው እንዳሉ፣ የየካቲቱ አብዮት እንደ ከባድ የክረምት ነጕድጓድ፣ ግምግም ማለት ጀመረ። አብዮቱ የምዝብሮቹን በቀል ለመወጣት፣ የበዘበዦችን በር ማንኳኳት ጀመረች። እንደ መቅድማዊ አመጣጡ ቢሆን፣ ሕዝባዊ መልክ ስለነበረው፣ ለአብርሒት ደስታ፣ ለወንድሟ ግን ሀዘን ፈነጠቀ። የኋላ መፈክሩ ግን፣ በወታደር አርማ ላይ የተቀየሰ በመሆኑ፣ የወንድሟን ዘራፊነትና ሀብታምነት ሸፍኖለት፣ የሐረር ምሩቅ ወታደርነቱን ብቻ አንፀባርቆ፣ የአብዮቱ ቀኝ እጅ አድርጐ አቀረበው። የአፍለኛው ዐብዮት ሁኔታ ይህን መልክ ከማሳየቱ በፊት ግን፣ ዐብዮቱ የመጣው ለነአብርሒት ነው በሚል ፍራቻ፣ የበቀል በትር ታወርድብኝ ይሆናል ብሎ በማሰብ ተምጀርጅሮ፣ ላለፈው ይቅርታ ሊጠይቃት፣ በወር ሦስት ጊዜ ያህል ከሲዳሞ፣ አለችበት ከተማ እየሔደ ይፈልጋት ነበር።

በዚህ ሙከራው፣ ባንደኛው ቀን፣ ድንገት ባገኛት ብሎ ከቤተሰቦቹ ዘንድ ቢሔድ፣ እንዳጋጣሚ አገኛት። አብርሒትም፣ መለስተኛ ጊዝያዊ የነፃነት ትንፋሽ፣ በዐብዮቱ መፈንዳት ተሰምቷት ስለነበር እንደሌላው ጊዜ፣ ወንድሟን ለመዝጋት አላሰበችም። እንዲያውም ልኩን ልትነግረው ፈልጋለች። ጥቂት ያሳዘናት፣ እነዚያ መከረኛ ወላጆቿ በመካከላቸው ሆነው፣ የአለመግባባታቸውን መሠረተ–ምክንያት





ለመጀመርያ ጊዜ በይፋ ለማወቅ መብቃታቸው ነው። ቢሆንም፣ ጨዋነት ባልተለየው አቀራረብ እንዲህ አለችው፤

"ስማ፣ ያንድ ቤተ–ሰብና ያንድ ወላጆች ልጆች ብንሆንም፣ በመደብ አስተሳሰብ አንገናኝም። ያንድ ሕዝብ ወገን፣ ያንድ ሀገር ዜጋ ብንሆንም፣ ጕራችን ለየቅሉ ነው። ያንድ ወጥ–ባሕል፣ ልምድና አከባቢ ውልዶች ብንሆንም፣ ግባችን የተለያየ ነው። ባንድ መልክ ያደግን ብንሆንም፣ በተዥጐረጐረ ባሕርይ ጕልምሰናል። እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶቻችን፣ ፍላጐታችንን ሁሉ ሳይቀር ለያይተውታል። ስለዚህም፣ ለኔ የሚጣፍጠኝ አንተን ይመርሃል። ለኔ የሚጥመኝ አንተን ያቅርሃል። እኔ አጋም ላይ ብተኛ አይቆረቁረኝም፣ አንተ ግን እብቅ ላይ ብትተኛ ይጐረብጥሃል። እኔ ተጀምሮ እስኪጨረስ ሕዝባዊ ነኝ፣ አንተ ግን የማን ወገን እንደሆንክ፣ የተሰለፍክበት የሙያ ምርጫህ መስክሮብሃል። እኔ ለማምንበትና ለቆየሁበት አቋም ታማኝ ነኝ። አንተ ግን ያደግህበትን ዐላማና ግብ፣ በያጋጣሚው የምትለዋውጥ፣ ወላዋይና ከዳተኛ ነህ።

... ዛሬ የመጨረሻ ዕድል ሰጥቼህ የማነጋግርህ፣ ወላጆቻችን ምንነትህን እንዲያውቁና፣ በተለይም ሁለታችንም፣ ካንድ አብራክና ካንድ ማኅፀን ለመገኘት መቻላችን፣ ብቻውን አንድ ዐይነት ሰዎች ሊያደርገን እንደማይችል እንድታውቀውና፤ ከዛሬም ጀምሮ የናት አባቴ ልጅ የሆነች እህት አለኝ ብለህ እንዳታምንና እንዳታወራ ላስጠነቅቅህ ፈልጌ ነው። በኔ ላይ የፈፀምከውን በደሎችና የጅ አዙር አሳዛኝ ሙከራዎችህን፣ ለወላጆቼ መንገር አልፈልግም። ግን መርሳት የሌለብህ፣ ለነዚህ በደሎችህ፣ ጊዜው ይርዘም እንጅ፣ አንድ ቀን ፍርዳዊ ዋጋህን ታገኛለህ ... " ብላ ንግግሯን እንደጨረሰች፣ ወጥመድ እንዳደናቀፋት ቆቅ ቱር ብላ ወደ ውጭ በረረች። በርግጥም ጨክና ኖሯል፣ ወላጆቿም ሆኑ ወንድሟ ፈልገው አላገኟትም።

እነዚያ ያልታደሉ እናትና አባት "እዩዩአቸውን" ይዘው ከቤታቸው ሲቀመጡ፣ ያ የእህቱ ንግግርና ማስጠንቀቂያ ያናወዘው፣ እሷን ካላጠፉ በሰላም እንደማይኖር ተሰምቶት፣ አሠሣ ገባ። ባስቸኳይም፣ ያዲሱ መንግሥት ቀንደኛ ጠላት መሆኗን፣

ለሚመለከተው ባለሥልጣን አመልክቶ፣ በደንብ እንድትፈለግ አዘዘ። ምድረ ነጭ ለባሽና ሠላይ፣ በዚያን ቀን አብርሒትን ፍለጋ ያልደረሰበት ቦታ አልነበረም። አብርሒት በጠፋች በማግሥቱ፣ ደብረ ብርሃን መዳረሻ ላይ ከምትገኝ፣ ቀላጢ ከምትባል ከተማ አውራ ጐደና ላይ፣ መኪናዋ ተገኘች። እሷ ግን የውኃ ሽታ ሆናባቸው፣ እስከ ዛሬ አላገኟትም። ወንድሚም፣ የገዛ እህቱን የመንግሥት ጠላት መሆኗን በመጠቀሙ፣ ልዩ ሽልማትና ልዩ የደሞዝ አበል በመስጠት፣ ታማኝነቱን አደነቀለት መንግሥት ! .

ይህ እንዲህ እንዳለ፣ ዐመታት ተጓዙ። ለካስ አጅሪት አብርሒት፣ ከፋኖ ገዳሟ ገብታ ኖሯል። የሠፈረችበት ጕራ፣ የታጋዮች መናኸሪያ የሆነው፤ ለአሻፈረኝ ባይ፣ ባመችነቱ የታወቀውና የራሱ የሆነ የተፈጥሮ መከላከያ ያለው አርማጮሆ የሚባለው በረሃ ነው። ያኔ በመኪናዋ ሆና የጠፋች ጊዜ፣ ቤንዚኗ በማለቁ ከደረሰችበት ሥፍራ ተነስታ፣ አርማጮኾ ድረስ ለመጓዝ ወራት ፈጅቶባታል። ያን ጊዜ ከመንገዱ ጣመን የተነሣ፣ ብዙ ሥቃይ ቢደርስባትም፣ ዛሬ በረሃውን ለምዳው ከምንም አትቆጥረውም።

ርግጥ ከበረሃው ንዳድና፣ ከትግሉ ውጣ ውረድ የተነሣ፣ ቀድሞ የነበራት ውብትና ላህይ ተሚጦ ጠፍቷል። ያ ሀር ያስንቅ የነበረ ዞማ ፀጉሯ፣ ዛሬ አለመጠን ጕፍሮ፣ አነር ከነግልገሎቹ መደበቅ የሚችል ዱር መስሏል። እልያ አለንጋ ይመስሉ የነበሩ ጣቶቿ፣ ቁሩና ዐመዳዩ፣ ሐሩሩና ንዳዱ ተፈራርቆባቸው፣ መጋዣ መግረፍ የሠለቸውን ጕማሬ ይመስላሉ። የጣቶቿ ጥፍሮች፣ የጠመንጃዋ ቃታ ሞርዷቸው፣ ካረጀ ያንበሳ መዳፍ ጋር ይነፃፀራሉ። ያ፣ መሸት የጀመረ ወይን ይመስል የነበረው የገጿ ላህይ፣ ድራሽ አባቱ ጠፍቶ፣ በምትኩ በፊቷ ላይ አፍጠው የሚታዩትን አጥንቶች አንድ ሁለት ብሎ መቁጠር የቻላል። ያ ጠንበለል ይመስል የነበረ ማራኪ ቁመናዋ፣ ዛሬ ሸንቅጥ ብሎ፣ ቤቴ ብላ ላለችበት በረሃዋ፣ ነብር አስመስሏታል። አጭር ቁንጣዋን ታጥቃ፣ እጀ ጉርድ ኮቷን አጥልቃ የጠፍር ጫማዋን ተጫምታ፣ ካንገቷ ላይ በጠፍር ተጠልቀው፣ በደረቷ ላይ የሚጨፍሩ፣ መርፌ ቁልፍ፣ ወረንጦ ኩክ ማውጫና አነስተኛ የነተበች የጨርቅ ከረጢት





አንጠልጥላ፣ ከግራ ትከሻዋ ላይም፣ የሥንቅ ማከቻ አኩፋዳዋንና አንዳዴም ቦምብ የምትይዝበትን ስልቻ አንግባ፣ በስተቀኝ ትከሻዋ ላይም ሌት ከቀን የማይለያትን "መቅጫ" ብላ የሠየመችውን ጠመንጃ ይዛ ላያት ሰው፣ አብርሒት ጀግና ወንድ እንጅ፣ በጭራሽ ሴት አትመስልም።

ትክሳ፣ ትጥቁር እንጅ፣ ወዘናዋ ጨርሶ አልተሚጠጠም። ስትስቅ፣ የጥርሷ ውጋጋን፣ ጨለማ ይገላምጣል። ኰልል እያለ የሚወጣው ድምጿ፣ የበረደውን ሰው ያሞቃል። ጠቅላላ ሰውነቷ ኵምጭጭ ይበል እንጅ፣ ያላት ዐቅምና ብርታት ከብረት ይጠነክራል። ግርማ ሞገሷም ይገላምጣል ! አብርሒት በዚህ ሁኔታ ነው፣ ያርማጮኾን አካባቢ፣ ፒያሣዋ፣ ሲነማ ቤቷ፣ ቪላዋ አድርጋ፣ ለአመታት ቆይታ የምትኖርበት። ፀለምት መናኸሪያዋ ሆኗል። ድሮ የለመደችው መጠጡ፣ ፍትፍቱ፣ መኪናው፣ ሦፋው፣ ምናምኑ፣ ዛሬ አርማጮኾን ለምዳ፣ ምንም ትዝ አይላት። አንዳንድ አዲስ መጥ ታጋዮች፣ ከቦታው እንደመጡ ሰሞን እንቅፋት እንኳ በመታቸው ቁጥር፣ ሲበሳጩና ለዚያ ዓላማ ወስነው የመጡበትን ቀን ሲረግሙ ስትሰማ፣ "ጓዶች አይዟችሁ ! እያደር ትለምዱታላችሁ" እያለች ታፅናናቸዋለች። እሷም በበኩሏ፣ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ ብሶት ለመበቀልና አዲስ የኅብረተ–ሰብ ሥርዓት ለመመሥረት፣ አርማጮኾን ተለማምዳ ትግል ስታካሒድ ዐመታት አልፏታል። ዛሬማ ትጥቁም፣ ሥንቁም ስላደገ፣ታጋዮችን ይጋብዛል ።

አብረሒት፣ በተመደበችበት የኢሕአሠ አንዱ ኮማንዶ ውስጥ፣ ብዙ ጀብዱዎችን የፈፀመችና፣ በከፈለችው መሥዋዕትነትና፣ የሞራል አራአያነት በጠቅላላው ሠራዊት ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈች ናት። የታጋይነት ሙያዋ በጦር ሜዳ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ ያለችብትን የኰማንዶ አባሎች በማነቃቃትና ከፍተኛ የዐብዮት መንፈሣቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ፣ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በማዘጋጃት፣ ያበረከተችው ድርሻ፣ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሌላው ሌላውን ተግባሮቿን መጥቀስ እንኳ ባይሰፈልግ፣ የሚከተለውን አለማውሳቱ ከበደል ያስቆጥራል።

ከግዳጅ መልስ ማታ ማታ፣ ካርማጭኾ ዋሻቸው፣ ታጋይ ጓዶች በሙሉ ለእረፍት

ሲገናኙ፣ የዕለቱን ሁኔታ ከተወያዩ በኋላ፣ አብርሒት በየቀኑ ትምህርታዊነት ያለው የመዝናኛ ጨዋታ ታቀርባለች። የሚነድ ዕንጨት ያገኙ ለት፣ እሳት አንደው ዙርያውን ከበው፣ ጨዋታው በሷ መሪነት ይቀጥላል። ካሰቂኝ ጨዋታዋ አንዱ እንካ ተጠየቅ ነው።

"እንኪያ ተጠየቅ" ትጀምራለች አብርሒት፣

"በምን ልጠየቅ" ይላል አንዱ ጓድ ይነሣና፣

"በወጨፎ" ትለዋላች አብርሒት ትመልስና።

"ምን አለሽ በወጨፎ" ብሎ ይጠይቃታል አንዱ ጓድ፣

"ብሬዥኔቭ ታየኝ ያ ቀዳው ተገፎ" ብላ ትመልሳለች ‖

ሌላው ጓድ ወዲያው ተነስቶ፣ እኔ ሌላ መልስ አለኝ ይልና፣

"ያ ወልደ ሒትለር ኖሯል፣ ለካስ ባዶ ቀፎ !" የሚል ይሠጣል።

ሌላው ደግሞ ይነሳና፣ እኔ የተለየ መልስ አለኝ !

"ያንን ደርግ አየሁት፣ ከንፈሩ ተንሻፎ፣ ! ሲል ይመልስና፤

በሙሉ ሣቃቸውን ያስነኩታል።

አንዱ ጓድ ይነሳና፣ አብርሒትን ሌላ ተጠየቅ እንድትሰጥ ይጠይቃታል። እሷም ምንጊዜም ዝግጁ ናትና፤

"እንኪያ ተጠየቅ" ትለዋለች

"በምን ልጠየቅ ?" ይላታል፣

"በፋሽስት" ትለዋለች

"ምን አለሽ በፋሽስት ?" ይላታል፤

"የድሮውን ሒትለር፣ ዛሬ አገሬ አየሁት !" ብላ ስትመልስ፣ እያንዳንዱ ታጋይ ጓድ፣ አርማጮኽ ዋሻ ውስጥ መሆኑን እስኪረሳ ድረስ፣ የኩረኩሩትን ያህል ይስቃል።

አብርሒት፣ የጓዶቿ ሣቅ ገና ሳያልቅ ሌላ ጨዋታ ወዲያው ትተካለች። ድምፃዊት በመሆኗ፣ ያቅራራች እንደሆነ፣ የማይነሸጠው ጓድ አይገኝም። የምታዘወትረው፣ "የተው ጉራው" ቀረርቶ ሲሆን በተለይም፤

"በል ግፋ፣ በል ግፋ፣ በል ግፋ ደግን





ዐብዮት ያመጣል፣ ድልን አንድ ቀን !" የሚለው እንጉርጉሮዋ፣ መተከዥዋ ብቻ ሳይሆን፣ ማነቃቂያዋም ጭምር ነው። አብርሒት ታጋይ ጓዶቿን ለማዝናናት በዚህ ብቻ አትወሰንም። ሣቅ በሣቅ የሚያደርግ የቀልድ ጨዋታም አላት። ከዚህም ውስጥ፣ ጓዶች በሙሉ፣ ሰምተው ሰምተው የማይሰለቹት ቀልድ፣ የሚከተለው ነው።

"እያ ብሬዥኔቭ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በቻውሴስኮ ተጋብዞ ቡዳፔስት ይሄዳል። ጉብኝቱን በጀመረ በሦስተኛው ቀን ካጉት ቻውሲስኮ ጋር እየተዝናኑ የግል ጭውውት ለማድረግ፣ ቡዳፔስት ከታወቀው አንድ ረዥም ሕንፃ ጫፍ ላይ ከሚገኝ አንድ የመዝናኛ ሳሎን ውስጥ፣ ከተማውን ቁልቁል ወደ ታች እያዩ ጭውውታቸውን ይቀጥላሉ። አጉት ቻውሴስኮ ድንገት ትዝ ብሎት፤

"ጓድ ብሬዥኔቭ ! ሕዝቡ ዝንባሌው እንዴት ነው ? አሁን በሙሉ ተረጋጋልህን ? ተቃዋሚዎችህስ በሙሉ ጠፋልህ ?" ሲል ይጠይቀዋል።

"እንዴታ ጓድ ! ሕዝቤ ከመረጋጋት አልፎ፣ ሕዝባዊ መሪ መሆኔን አምኖ በገዛ ፈቃዱ፣ ያለአንዳች አማራጭ በማቅረብ፣ ለኩመንስት ፓርቲ ፅንሰ ለሆነው ድርጅት፣ ሊቀ ወንበር እንድሆንለት ከመምረጡም በላይ፣ እያንዳንዱ የሀገሬ ዜጋ፣ ከገዛ ነፍሱ አብልጦ ነው የሚወደኝ" ብሎ በኩራት ይመልስለታል።

"እይ፣ ባጭር ጊዜ እንኳ ያን ያህል ላይወድህ ይችላል ! እኔ እንኳ ይህን ያህል ዘመን ገዥቼው፤ ዛሬም ቢሆን ያለኝ የተቃዋሚ ብዛት፣ ከራስ ፀጉሬ ቢበዛ እንጅ አያንስም !" ይለዋል፣ እውነቱን እንዲነግረው በመጋበዝ።

"ምን ማለትህ ነው አጉት ብሬዥኔቭ እኔ የምነግርህን አታምንም ማለት ነው እንዴ !" ይላል ቻውሴስኮ እንደመሣቅም እንደመቆጣትም ዐይኖቹን እያቁለጨለጨ።

"በጣም በዛ ማለቴ ነው እንጅ፣ ሕዝቡ በጠቅላላው አይውድህም ማለቴ አይደለም ! ግን እንዲህ በሙሉ አንደበትህ፣ ሕዝቡ በሙሉ ይወደኛል ስትል፣ ምን ተጨባጭ ማስረጃ ይዘህ ነው ?" በማለት፣ በዚያ የሚጉመዝዝ ፊቱ የፈገግታ ገጽታ ብልጭ አደረገለት።

"ምን ያህል እንደሚወደኝ፣ ሌላ ማስረጃ ከመዘብዘብ፣ ለምን እዚሁ በዓይንህ አላሳይህም ! እያንዳንዱ ዜጋ በሕዝባዊነት መሪነቴ አምኖ፣ ለኔ ትእዛዛዊ ፍቅር ሲል፣ ለሕይወቱ ሳይሳሳ እንደሚሠዋልኝ እዚሁ አሳይሃለሁ !" ብሎ ከፉከራ ባላነሰ መቅበጥበጥ ተናግሮ፣ አጠገቡ ከነበሩ ፈጣን ጋሻ ጃግሬዎች አንዱን ይጠቅስና፣ "እገሌ፣ እገሌ፣ ባስቸኳይ እዚህ እንዲመጡ ጥራቸው" ብሎ ትእዛዝ አስተላለፈ። ወዲያው ተኰልኩለው እንደመጡም፣ ካጠገቡ የሚገኝ አንድ መስኰት ከፍቶ በመጠቆም፤

"ቆራጥነታችሁን ለማሳየትና፣ ለኔም ሕዝባዊ መሪነት ፍቅር ስትሉ ለሞት እንኳ ቢሆን ወደኋላ እንደማትሉ፣ ጓድ ብሬዤኔቭ ዐይቶ ለማረጋገጥ ፈልጓልና፤ በል እንግዲህ ጐበዝ ! በዚህ መስኰት አንድ በአንድ እመረኝ !!" ብሎ፣ እንደ አራስ ነብር ዐይኖቹን አጉርጦ፣ እንዳያዋርዱት በማስጠንቀቅ፣ ትዕዛዝ ሰጠ። ተወርውሬ አልከሠከሰም በማለት ለጊዜው አሻፈረኝ ቢልም፣ ኋላ እንደ ማይቀርለት የሚያውቀው፣ ያ ምሥኪን ጀሌው ሁሉ፤ ብድግ እያለ በመስኰቱ ጤና ይስጥልኝ! እየዘለለ፣ በዚያ መስኰት ሶተመሪና ! ሦስቱ ያህል እየተውዘገዘጉ ወርደው ሲከሠከሱ፣ ያይ የነበረው ብሬዤኔቭ በሁኔታው ደነገጠና ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ ተነስቶ፣ አራተኛው ሰው ሊዘል ሲል፣ መላ ዐካሉ ወጥቶ የግራ እግሩ እንደቀረ፣ አፈፍ አድርጐ በመያዝ፣ ከመለሰው በኋላ፣ ወደ ቻውሴስኮ ዞር ብሎ "በተናገርከው ሁሉ አምኛለሁ !! የቀረበው ማስረጃ ይበቃኛል። ግን እነዚህን የቀሩትን ለመዝለል የተዘጋጁ ሰዎች አንድ ጥያቄ እንድጠይቃቸው ፍቀድልኝ" ብሎ ባየው ሁኔታ፣ ተደናግጦና ተሸብሮ፣ ጥያቄ ያቀርባል።

"በደስታ !" ሲል ጓድ ቻውሴስኮ የመጠየቅ ፈቃድ ይሰጠዋል።

"ሳትደብቁ ንገሩኝ ! ለመሆኑ በምን ዐላማና ግብ ተነስታችሁ ነው፣ በዚህ ዐይነት ቆራጥነት ተዘጋጅታችሁ፣ የቻውሴስኩን ትዕዛዝ በማክበር ለሞት መሥዋዕትነት የቀረባችሁት ?" ሲል አድናቆት በዋጠው፣ ያነጋገር ዘዬ ጠየቃቸው። የቀሩት ሦስት ነበሩና፣ ብዙ ጊዜ ተማክረውበትና ተዘጋጅተውበት የመጡበት ይመስል፣ እንደ አንድ ዐካልና እንደ አንድ መንፈስ በመሆን "ከቻውሴስኮ ጋር አብሮ ከመኖር ይልቅ፣ ሞት ሳይሻል አይቀርም በለን ነው !!" ሲሉ መለሱለት።





... አብርሒት ይህን መሰሉን ቀልድ ለጓዶቿ ስታጫውታቸው፣ ያ የበረሀ ሌሊታቸው፣ ሳይታወቅ የሚነጋበት ጊዜ ነበር። ቀልድ ብቻውን እንዳያሰለቻቸው በማሰብ፣ አልፎ አልፎ በዚያ ማራኪ ድምጿ፤

"ባርማጮኾ ዋሻ፣ ቅጣው በጄ እስካለች፤

ማንም አይደፍረኝም ነፃነት ከኔ ነች !" እያለች ስታንጐራጕር፣ ያካባቢዋ ያርማጮኾ ገረገንቡና ገደል ማሚቶው ሳይቀር፣ በሚያስተጋባው ጃዙ ያጅባታል።

በዚህ ዐይነት ሁኔታ፣ አብርሒት ከመሰል የበረሀ ጓዶቿ ጋር፣ ትግል ስታካሒድ ረዥም ጊዜ ሆኗታል። ያብርሒት ጣትና፣ የጠመንጃዋ ቃታ፣ በቃል ኪዳን የተጋቡ ይመስል፣ ለደቂቃ ያህል እንኳ ተለያይተው አያውቁም። የጭቁኑን ደም ለመበቀል፣ ባካባቢዋ የሚገኘውን ሠራዊተ–ፋሽስት በየጕራው ስታራውጥ ላያት፣ ወንድ ነኝ ያለ ጐበዝ አይስተካከላትም። በዚህም ዐብዮታዊ ተግባሩዋ በሠራዊቱ ውስጥ፣ ወደር የማይገኝለት ዝናና ትግላዊ ክብር ለመቀዳጀት በቅታለች።

አብርሒት፣ ከምድብ የኰማንዶ ዩኒቷ አሥር አባሎች ጋር ሆና፣ በወዲያኛው ዐመት አንድ ቀን ለግዳጅ ትሠማራለች። ከተሠማሩበትም ጕራ ላይ፣ አንድ የጠላት ባታሊዎን ገጥሟቸው፣ ቁጥራቸው፣ ከጠላት ሠራዊት ያነሰ በመሆኑ በ "አጥቅተህ ተደበቅ" የሽምቅ ውጊያ ዘዴ በመጠቀም፣ ላምስት ተከታታይ ቀናት ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ፣ አስፈላጊውን ቅጣት ከሰጡና ከነሱም በኩል መሥዋዕትነት ከፍለው፤ የጠላት ጦር በማየሉ፣ ወደ ሠፈር ለመመለስ፣ መንገዱን ስለዘጋባቸው፣ ወደ ኋላ አፈግፍገው፣ ካንድ በረሀ ውስጥ ለሁለት ወራት ጊዜ ያህል፣ ከዋናው ብርጌዳቸው ተቋርጠው ያለስንቅና ያለትጥቅ፣ ቆይተው ነበር። ያን ጊዜ ነው፣ አብርሒት ከስንቅ መያዣ አኩፋዳዋ ጋር፣ ምን ትመስል እንደነበር፣ ቀደም ሲል የተገለፀችው። አለያ ግን፣ የዐብዮቱ ሠራዊት ያን ያህል ችግረኛ አይደለም። እንደውም፣ የኢሕአሠ ሠራዊት፣ በዚያ ለጋ ዕድሜው ውስጥ ያን ያህል ድርጅታዊ ትጥቅ አሟልቶ በመገኘቱ፣ ያላደነቁት፣ የዓለም ታጋዮችና የተራማጅ ድርጅቶች አይገኙም።

በዚያ የግዳጅ ቀናት፣ የነአብርሒት ሁለት ጓዶቻቸው በጦርነቱ ላይ ቢወድቁም፣

አስከሬናቸውን ሳያስማርኩ፣ ተደብቀው ከከረሙበት ያርማጮኾ ዋሻ በክብር አሳርፈዋል፣ ያን ጊዜም ነበር፣ በዚያች አቀፋዳዋ ውስጥ የነበረች፣ የጓያ ጭብጦ ሥንቋን ስትቀረጥም የሰነበተችው። ከሁለት ወራት በኋላ ግን፣ የብርጌዳቸው የኋላ ደጀን፣ የት እንደጠፋ፣ እነ አብርሒትን ለማግኘት አሰሳ ሲያደርግ፣ ያ መንገድ የዘጋባቸውና ላምስ ቀናትም ያህል የተዋጉትን፣ የፋሽስት ጦር፣ ከሠፈረበት ጉራ ይደርሳል።

ጠላት የሰፈረው ከራባዳ ሥፍራ ስለነበር፣ ለሣምንት ጊዜ ያህል መሬት እንቅብ ሆኖ፣ እስክትንቀጠቀጥ ድረስ፣ ከባድ ጦርነት ሲያካሔዱ ቆይተው፣ እነአብርሒትም በቃፊርነት ካስቀመጡት፣ ያካባቢው ገበሬዎች አንዱ ካሉበት በረሀ ድረስ ሔዶ፣ ስለጦርነቱ ስለነገራቸው፣ ካሉበት ተጉዘው በሁለተኛው ቀን ማታ ምሽቱ ላይ በመድረስ፣ ከጠላት በስተጀርባ የሚገኘውን ኮረብታ ተገንና መከታ አድርገው፣ ሌሊቱን በጠይትና በቦምብ ሲቀሉት አደሩ። ንጋት ላይ ከማዶአቸው ሆኖ፣ ጠላትን ሲያንገረግብ የሰነበተው፣ የደጀን ብርጌዳቸው፣ የነሱን ድጋፍ በማግኘቱ፣ ከመጠን በላይ በጉራው ፍልሚያ ላይ አይሎ፣ የጠላት ሠራዊት ሰፍሮ ወደሚታኮስበት ረባዳ ሥፍራ፣ መገስገስ ጀመረ። ከፋሽስቱም ሠራዊት ወገን፣ ግብግቡን መቋቋም ያቃታቸው፣ አንዳንድ አምልጦ ለመሸሽ ወደ ኋላው ያፈገፍግ የነበረውን ተባራሪ የፋሽስት ወታደር፣ ከበስተጀርባው ሆነው እንደንብ የሚናደፉት፣ አብርሒትና ጓዶቿ፣ የዘለዓለም ምሱን ያቀምሱት ነበር። በዚያም ረባዳ ጉራ ላይ፣ ቀኑን ሙሉ፣ በዚያ የጠራራ ፀሐይና የበረሀ ንዳድ ውስጥ፣ ከምንጊዜውም የጦፈ ጦርነት ሲካሔድ ውሎ፣ ማታውን የጨበጣ ግብ ግብ ተጀመረ።

ወዲያው የጠላት ጦር ተመታና፣ ማታውን ምድረ–ፋሽስት ትጥቁን እየፈታ መለመላውን፣ ወደኋላው እየመረሸ፣ እግሬ አውጭኝ ማለት ጀመረ። ማምለጥ ግን አልሆነለትም። እነአብርሒት፣ ከበስተ ጀርባው መሽገው የሚራወጠውን ባንዳ ሁሉ፣ በቀላሉ መማረክ ጀመሩ። መንፈቀ–ሌሊት ላይ፣ በሩቅ ይሰማ የነበረው የጥይት ጬኸት ሁሉ "ጭጭ በል"፣ ያሉት ይመስል፣ ጉራው ረጭ አለ።





የነአብርሒት ዩኒት፣ እያንዳንዱ ጓድ፣ ካምስት ያላነሰ የፋሽስት ባንዳ ወታደር ሲማርክ፣ አብርሒት ብቻዋን አሥሩን ትማርካለች። ሌሊቱ በጨረቃ ብርሃን የደመቀ ስለ ነበር፣ ጓዶቹ ከያሉበት ሥምሪታቸው ተጠራርተው፣ ከነ ምርኮቻቸው ጋር፣ አንድ ቦታ ላይ ተሰበሰቡ። በዚያም ሌሊት፣ ከስልሳ ያላነሱ የጠላት ወታደሮችን ማርከው፣ እጅ እጃቸውን በልጥ ጠፍረው፣ በስምንት ጠመንጃቸው አግረው፣ እስኪነጋ ካቆዩ በኋላ፣ ጉሕ ቀዶ ማለዳ ላይ ምርኮአቸውን ሲመለከቱ፣ የቆላ መጋዣ ከመሳሰሉት ምርኩኞች ውስጥ፣ ለካስ፣ የአብርሒት ወንድም የነበረው፣ ያ ሻለቃ ከመሐላቸው ኖሯል።

አብርሒት እንደ ወንድ ታጥቃ፣ የድሮ ገጽታዋ ሁሉ፣ በበረሀው ንዳድ ኃይለኛነት ተለውጦ፣ የቀድሞ ማንነቷ ስለማይታወቅ፣ ወንድሟ ምርኩኛው፣ ሊለያት አልቻለም። እሷ ግን ገና ስታየው አውቃዋለች። እሷንማ እንዴት ብሎ ሊለያት ይችላል? ያ፣ ሰብ ረገብ እያለ፣ ታችና ላይ ይል የነበረ ሽንጧ ሟሙቶ አልቋል። ያ ማራኪ ውብ መልኳ፣ ጠበንጃዋን አንግባ ቆላ ደጋ ስትራወጥ፣ ከሐሩሩና ከውርጩ ጋር ለመላመድ፣ ባደረገችው ስምምነት፣ ውብቷንና ወዘናዋን ገብራለች። ተመልካችን ይገረምም የነበረውን፣ ያን ውብቷን፣ በራሷ ፈቃድ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አሣልፋ በመስጠት፣ ለቀመችለት አብዮት ለውጣዋለች። ስለዚህም፣ ያ ድንባዥም ሻለቃ ወንድሟ፣ ከማራኪዎቹ ውስጥ፣ አንዷ የገዛ እህቱ የነበረችዋ አብርሒት፣ እንደምትገኝበት፣ ማወቅ ቀርቶ መጠራጠር እንኳ አልቻለም። አብርሒት ግን፣ በጂ እንደወደቀ ካወቀችበት ቅፅበት አንስቶ፤ ይህ ነው በማይባል ፈንጠዝያ፣ ልቧ ተነክቶ፣ ሁኔታውን ለማንም ሳትነግር በምሥጢር ለራሷ ብቻ ጠብቃ፣ ወደ ዋናው ደጀን ጦር ለመቀላቀል ምርኩኞቻቸውን በጠመንጃ እየነዱ፣ ጉዞ ጀመሩ። ከአንድ ሰዓት መንገድ በኋላም፤ ደጀኑ ጦር፣ በበኩሉ ያገኘውን የምርኮ ግዳይ ጥሎ፣ ለፍርድ ሲዘጋጅ ከነበረበት ሥፍራ ድንገት ከቸች አሉ። ስልሳውም የፋሽስት ሙርኩኞቻቸው፤ እንደ ብቅል አውራጅ፣ እጆቹን ወደላይ አንከርፎ እየተነዳ ገባ።

ከዚያም ምን ይነገራል ! በሕይወት መኖራቸውና መገኘታቸው ብቻ ሳይሆን፣

የዚያ የፋሽስቱ ሠራዊት ጦር መሪ፣ የነበረውን ሻለቃ ሳይቀር፣ የነበረበትን የስልሣ ምርኮኞች አጀብ፣ ይዘው በመምጣታቸው፤ በቀጣናው ጦር ሜዳ ከተሠማሩበት ጊዜ አንስቶ፣ በብርጌዳቸው ግዳይ ላይ፣ አጋጥሟቸው የማያውቅት ደስታ ተሰማቸው። ከመጠን በላይ ፈነጠዙ። የፌሽታ ጥይት ሩምታ፣ ማንጣጣትና ማንዷዷት ሆነ። በኋላ ስምንተቹን የአብርሒት ጓዶች፣ የፍፁም ጀግናነት መግለጫ የሆነ የበረሃ አበባ ሸለሚቸውና፣ ሰላምታ መለዋወጥ ጀመሩ።

በማግሥቱ ቀትር ላይ፣ የተማረከው ሰው 150፣ የተገደለውም 150 መሆኑም ከራሳቸውም 10 ጓዶች መሠዋታቸው፣ ተነገረና፣ ላገኙት ድል የደስታ መግለጫ ንግግር፣ ለወደቁት ጓዶችም የመታሰቢያ ትውስት ተደረገ። የብርጌዱ መርማሪ ጓዶችም፣ የምርኮኞቹን ምርመራ ጨርሶ ስለ ነበር፣ በምሥጢር የሚጠበቀው ተጠብቆ፣ የቀረው ለሠፊው ሠራዊት ባደባባይ ተነበበ። በሪፓርቱ ውስጥም፣ ያ የማረኩት የፋሽስት ጦር፣ በጨካኝነቱ የታወቀው የነበልባል ብርጌድ ቅርንጫፍ ሠራዊት እንደነበርና፣ ብዙ ግፍና በደል በታጋዮችና በስሜን ጭቁን ሕዝብ ላይ ሕፃናት ልጃገረዶችን ከመድፈር አንስቶ፣ ሽማግሌና አሮጊቶችን ቤት እየዘጋ በእሳት እስከማቃጠል ድረስ፣ ወንጀል ይፈጽም እንደነበር፣ ከማስረጃ ጋር ተነገረ። ይህም ግፈኛ የፋሽስት ብርጌድ፣ ከሐረሩ የጦር አካዳሚ ምሩቅ በሆነ፣ አንድ ሻለቃ ይመራ እንደነበረና፣ ያም ሻለቃ ከነሕይወቱ በጓድ አብርሒት አማካይነት እንደተማረከ ሲነገር፤ ጭብጨባው ቀለጠ። ስብሰባው ከመበተኑ በፊትም፣ አብርሒት በስብሰባው ላይ ለመናገር መፈለጓን አስቀድማ ነግራ ኖሮ፣ ከተቀመጠችበት ተነስታ፣ የጭብጨባውን ማዕበል አብርዳ፣ መናገር ጀመረች።

"ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አርነት የቆማችሁ ጓዶች ! በመራራው ትግላችን ውስጥ፣ ዛሬ ለኔ አዲስ ታሪክ አጋጥሞኛል። ብዙ ሐተታ የሚጠይቀውን ይህን ታሪክ፣ ባጭሩ ለመግለፅ ብሞክር፤ ሊገድለኝ ያሳድድ የነበረው፣ የናቴ የአባቴ ልጅ፣ የጥንቱ አንጀቴ፣ የኋላ ጠላቴ፣ ዛሬ በጄ ወድቋል። እናቴም አባቴም ወንድሜም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ብቻ እንደሆነ አምኜ፣ ለጋራው ትግል ከተሳማራሁበት ወቅት ጀምሮ፣ ብዙ መራራ ቅፀበቶችን አሳልፌ አለሁ። ዛሬ ግን፣ የአብዮት መራራዊ ትግል ዋጋ፣ ድል ነውና፣ ይኸው፣ የማረክነው፣ የፋሽስት ጦር አዝማች ሆኖ የተገኘው ሻለቃ፣ የኔው የራሴ ታላቅ ወንድም የነበረ ነው። ለኔ ከዚህ የበለጠ ደስታ አላገኝም። ወደ ትግል ሜዳ ከመሠማራቴ በፊት፣ በየጊዜው ሊያስገድለኝ አስቦ ብዙ ሙከራዎችን አድርጐ ነበር። ዛሬ ግን ከኔ ቀድሞ ራሱ ወድቋል። ይህ ዓይነቱ ልዩ አጋጣሚ፣ ጠቅላላው የፋሽስት መንግሥትና ሠራዊቱ፣ ከጊዜ በኋላ፣ በተራማጅ ኃይሎች የማያቋርጥ ትግል፣ ተንኰታኩቶ እንደሚወድቅ፣ ይህ ዐይነቱ ድላችን ዐይነተኛ ምስክር እንደሚሆን አምናለሁ። የዛሬው አጋጣሚ፣ ራሱን በራሱ የሚገልጥ ልዩ አብዮታዊ ትንግርት በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ልናገር አልፈልግም። አጭሩን ንግግሬን ከመፈፀሜ በፊት ግን፣ ሁለት ነገሮችን እጠይቃለሁ።

የመጀመርያው፣ ዐብዮት "እየመረረ የሚጣፍጥ" አዝጋሚ ኪደት እንደሆነና፣ ታጋይ ጓዶች ሁሉ፣ ምንም ነገር ሳይፈትናቸውና ተስፋ ሳይቆርጡ እስከ መጨረሻዩቱ የድል ዋዜማ ቀን ድረስ፣ ትግላቸውን እንዲቀጥሉና የመራራ ትግላዊ አዝመራቸውን፣ ጣፋጭ ፍሬ በመጨረሻ ላይ ሊያገኙ እንደሚችሉ አስታውሳለሁ።

ሁለተኛው ጥያቄዬ ደግሞ፤ ይህ የተማረከ ግፈኛ ወንድሜ፣ ከሠራዊቱ ፊት ቀርቦ፣ እኔ እህቱ አብርሒት መሆኔ ተገልጾለትና ተነግሮት፣ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ላይ ለፈፀመው በደል፣ ራሱ የራሱን ፍርድ በሠራዊቱ ፊት እንዲሠጥ እጠይቃለሁ።" ብላ እንደጨረሰች፣ በጭብጨባና በጥይት እሩምታ፣ ጉራው አስተጋባ። ወዲያውም ሻለቃ ወንድሟ፣ የፊጥኝ ታስሮ፣ ሠራዊቱ ከተሰበሰበበት ቦታ ላይ ቀረበ። የማረከቸው የገዛ እሁቱ አብርሒት መሆኗ ከተነገረው በኋላ፣ ሁኔታውን አይቶ እዲያረጋግጥ ተጠየቀ። የተቀለሰ ራሱን አቅንቶ፣ እንባ በሚያዘንቡ ዐይኖቹ ሊመለከት ቢሞክር ማየት አልቻለም። እህቱ መሆን እንዳለባት ግን፣ ለልቅሶ በሚሞክረው ድምፁ "እኔን ያለሷ ማንም ሰው ሊያጠፋኝ እንደማይችል፣ ድሮውን አውቃለሁ !" እያለ ተለፋደደ። በመጨረሻም ላይ፣ የፋሽስት ጦር አዝማች ሆኖ፣ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ላይ ለፈፀመው ግፍ፣

ራሱ ለራሱ ፍርድ እንዲሠጥ ተጠየቀ። በሰማው ዜናና ባጋጠመው ልዩ ሁኔታ፣ ሕሊናው ዞሮበት፣ መናገር ስለተሳነው፣ አንዲት ጣቱን ቀስሮ በማሳየት "አንዲት የአብርሒት ጥይት !" ሲል የግዱን እንባ እየተናነቀው ተናገረ። ወዲያውም "የአብርሒት ጥይት የተከበረ ነው። ላንተ ለርካሹ ሰው፣ ለፋሽስቱ ውሻ አይሆንም ! ክቡር ጥይቷን ያረክስባታል !" ሲል የብርጌዱ፣ የፊልድ ኮማንደር ተናገረና፣ ሻለቃው ያ ሁሉ ሠራዊት ፊት እንደቆመ፣ ሁለት ድግን መትረየስ ይዘው በቀረቡ፣ ሁለት ተዋጊ ጓዶች አማካይነት፣ ራሱ በሰጠው "ያንድ ጥይት ፍርድ" ብቻ ሳይሆን ከመቶ በማያንሱ፣ በሚያንገበግቡና በሚቀጠቅጡ የጥይት ጅራፎች ተገረፈ።


( በምሕርት ታልፎ ቢሆን ኖሮ፣ ራሱን በማረም ይሻሻል ነበርን ?)

------- * * * --------





# ሰ መ ነ



እትብቱ ተቆርጦ፣ካረረበት ምድር፣
የሰው ልጅ ካልኖረ፣ ከራሱ ሕዝብ ጋር፣
ምን መቅኖ ያገኛል፣ያገር ልጅነቱ፣
በቀዘባ ዕድሜው፣ከራቀ ከናቱ!
ወገኑና ሕዝቡ፣እንደሆነው ሆኖ፣
ላብርት ካላደገ፣ምን ያገኛል መቅኖ?
ከወላጆች ጉያ፣ ካልኖረ በሥርዓት፣
እንዴት ሊል ይችላል፣ልጅ ነኝ ለናት ላባት?
ምን ትርጉም ሊሰጠው፣ባሕል ሆነ ሀገር?
ለጋ ልጅ ካደገ፣ በባእዳን ምድር!
በሐቅ "ተቆረጠ"፣የሚባለው" እትብት"!
ሕፃን ሲለቅ ነው፣ የልደቱን መሬት
እንቦቃቅላውን፣ያን ቀዘባ ሕፃን፣
ሳይመርጥና ሳይችል፣ራሱም መወሰን፣
ካገር ጉያ አውጥቶ፣ለሌላ ባሕል መስጠት፣
ወንጀል ነው ኩነኔ፣ አሰቀጭ አለምሕረት።
ዓለም-አቀፍ መንፈስ፣ ቢሆን ለማዳበር፣
በጉልማሳው እንጅ፣ በጨቅላው ባልነበር!
እሱም ይቻል ነበር፣ባገር ውስጥ ማስተማር
ቀዘባ ልጅ ወስዶ፣ ባርማዶ ከመንከር!!

# መንደርደርያ

ሕፃናት በተፈጥሮአቸው ታቡላ ራዛዎች ናቸው። በኅሊናቸው አነፃር፣ ምንም ያልተፃፈባቸው ሌጣ ብራናዎች ! ማንኛውም ሰው፣ በለጋ ዘመናቸው ወቅት፣ የፈለገውን ቢፅፍባቸው፣ ሌጣ የኅሊና ሠሌዳቸው እንዳለ ይቀበለዋል። ማንም ሰው፣ የፈለገውን ቢኩልባቸው፣ የልቡና መድሔታቸው ያንፀባርቀዋል።

የዘመናችን የሀገራችን ኢሕዝባዊ መንግሥት፣ ለኢትዮጵያ ሕፃናት ተቀዳሚነት የሚሰጥበት አንዳንድ አጋጣሚዎች ቢኖር፣ ይህን የተፈጥሮ ልዩ ምሥጢር በመረዳቱ ነው። በየቀበሌው የኪነት ክበብ አማካይነት፣ የሆነ ያልሆነ ምናምንቴውን ሲለቀልቅባቸው ይውላል። የሕፃናት አምባ ብሎ በሠየመው፣ የእምቦቃቅላ–ሕፃናት ማጐሪያው፣ ፈልቶ ያልወጣለትን የግል ራሱን ጥንስስ ድፍድፍ ሲግታቸው ይውላል። ከዚህም አልፎ፣ ከጌታቸው ሀገር ሞስኮ ልኮ፣ ከለሳን ይበግታቸዋል። በርሊን ልኮ፣ የሰላይነት ኢሰብዓዊ ተግባር ያስተምራቸዋል፣ በነዚህ ልዩ ልዩ የንፁሐን ሕፃናት መቅሠፈያዎች አንፃር፣ ወደ ሌላ ወዳጅ ሀገር በብዛት የተላኩትስ ሕፃናት፣ ለምን ዓይነት ግብ ተጠምቀው ሊዘጋጁ ይሆን ?

ዕድሜው እጅግ አጭር እንደሆነ፣ ገና ያልተከሠተለት፣ የኢሕዝባዊ መንግሥት፣ ለረዥም ጊዜ ምኞታዊ እቅዱ፣ የማያዘጋጀው ነገር የለም። ከነዚህ ዝግጅቶቹ ውስጥ፣ እንደ ጭቃ እየጠፈጠፈ፣ በአምሣሉ እየቀረፀ ለማውጣት፣ እንዳሻንጉሊት የሚጫወትባቸው ሠራዊተ–ሕፃናት ይገኙበታል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ፣ ለዚህ ግብ ወደ ውጭ የተላኩት ኢትዮጵያውያን ሕፃናት፣ ወላጃቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጀቱን አቃጥሎበታል። ከሀገሪቱ ውስጥ ያሻቸውን ሁሉ ሀብትና ንብረት እየዘቀ ሲወስዱ ያልቀጨውን ያህል፣ ከአብራኩ ተከፍለው፣ ከማኅፀኑ የወጡትን ልጆቹን፣ ያለወላጅና ያለተወላጅ ግላዊ ፈቃድ፣ በግድ እያንጠለጠለ ሲወስድበት፣ ልቡ እስኪደማ አብግኖታል። ሕፃናቱ ራሳቸው ቢሆኑ፣ ለመከላከል ያልባለቁና አቅም የሌላቸው በመሆናቸው፣ ዝም ብሎ ከመሔድ በስተቀር፣ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። መሔዱንስ ይሒዱ፣ የሆነው ሆኖ፣ በማያውቁት ሀገር፣ በዚያ ለጋ የሕፃናት እድሜያቸው ከተላኩ በኋላ፣

ያጋጠማቸው ሁኔታ ምን ነበር ? "ሠመነ" ከሔዱት ሕፃናት አንዷ ናት። ይህች እምቦቃቅላ ሕፃን፣ የገጠማት መከራና ፍዳ ሁሉ፣ ሌሎቹንም ሕፃናት የጐሸማቸው ስለሆነ፣ የሠመነ ታሪክ ስለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ከርታታ ሕፃናት ጭምር የሚናገር ወኪልና ቀላጤ ነው። ወደ ተከታዮቹ ገጾች ሲያመሩ፣ የሕፃናቱን አሳዛኝ ሁኔታ ተመዝግቦ ያገኙታል።

እንደሚታወቀው ሁሉ፣ ማንኛውም ልጅ በተወለደበት ማኅበረ-ሰባዊ ባሕልና አከባቢ ውስጥ ሆኖ፣ ከወላጆቹ፣ ቤተ-ዘመዶቹ ባልንጀሮቹና ባጠቃላይም ወገኖቹ ጋር ሆኖ ቢያድግ፣ ሰብዓዊነትና የሰብዓዊነትም መብት ጭምር ነው። ይህ እስካልሆነም ድረስ፣ በአንድ ሀገር የተወለደ ሕፃን፣ በሌላ ሀገር እስካደገ ድረስ፣ የባዕድ ስሜት ተገዥ የማይሆንበት ምክንያት የለም። ለጋ ኅሊናው፣ ለባዕዳን አከባቢ በቀላሉ ተገዢ ለመሆን በመቻሉም፣ ጥንተ ባሕሉን፣ ቀስ በቀስ አጥፍቶ ልሙጥ ይሆናል።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያዊ ያለውን ከባድ ባህል፣ እንኳንስ በባዕድ አከባቢ ተቀምጦ፣ ውስጡም እንኳ ሆኖ መንከባከብ ስለሚያስቸግር፤ እነይሉኝታ፣ እነአከብሮተ- ሰብ፣ እነ-ባሕርየ-ጨዋነት፣ እነጠባየ-ሽጋነት፣ እነትህትናና፣ እነማስተዋል፣ ... ድራሽ አባታቸው ይጠፋል። ሕፃኑም፣ ላልተወለደበትና ዘለዓለም ለማይኖርበት ባዕድ ሀገር ባሕል፣ ባሪያ ሆኖ ይቀራል። የኋላ ኋላም፣ ከትውልድ ሀገሩ ቢመለስ፣ የባሕል ግጭት ተፈጥሮበት፣ መላ ሕይወቱ መቅኖ አጥቶ ይኖራል። በሔደበት ቦታ ሁሉም፣ ሁለት ወዥንብር የመታው ባሕል የተጫነ ሠረገላ በመሆኑ፣ መንገዶቹ ቅርቅፍት ይበዙበታል።

የየትኛውም ሕዝብ ቢሆን፣ የማኅበረ-ሰቡ አቋም መላላት ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ያህል ችግረኛ ቢሆን፣ የገዛ ራሱን እምብቃቅላ ለጋ ሕፃናት፣ በባዕድ ሀገር ሞግዚትነት እንዲያድጉ አያደርግም። እንደ ኢትዮጵያውያን ያለ ባሕለ-ወዳድ ሕዝብ፣ ጨርሶ ካላበደና፣ ጨርቁን ጥሎ ካልወፈፈ በስተቀር፣ እንዲያ የሚሳሳላቸውን ልጆቹን ከጉያው አውጥቶ፣ ለሀገሩ ምድርም ሆነ፣ ለሚንገበገብለት ባሕሉ፣ እጅግ በራቀ ሀገር ውስጥ ልኮ፣ በባዕዳን ሞግዚቶች





እንዲያድጉ አያደርግም። በርግጥ ነካ አርጐት ካልሆነ በስተቀር፣ ተተኪ የሚሆኑትን ያዲስ ትውልድ ወኪሎች፣ ከባሕር ማዶ ልኮ፣ በባዕዳን ባሕል እንዲበከሉ በጭራሽ አያደርግም። የትኛውም ሕዝብ፣ ከገዛ አብራኩ የተከፈሉ፣ የገዛራሱን ልጆች፣ ለጋጠ-ወጥ የባዕድን ባሕል መጫወቻ አሻንጉሊት አያደርግም። ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ግን፣ ምንም ያህል የተጠላም ቢሆን፣ ባሳዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ላይ፣ በዘመናችን ተፈጽሟል። ይች አጭር ታሪክ፣ የዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ምሥክራዊ ሥንክሳር ናት።

እዚች መጨረሻ ነጥብ ላይ፣ ላስታውሳችሁና ላስገነዝባችሁ የምፈልገው፣ "መጨረሻው-አያምር" እንደሚሉት ሆኖ እንጅ፣ በበኩሌ ታላቁ ታጋይ የዚያ ሀገር መሪ፣ የነብሬዥኔቭን ግዳጃዊ ምክር ተቀብለው እንዲያ ያለውን አስተዛዛቢ ድርጊት ፈጽመው ይሆናል እንጂ፣ በፊተኛው ዘመናቸው፣ ከእንደዚህ ዐይነቱ ድክመታቸው ባሻገር፣ ጉረቤታቸው ላይ የሚንጐማለለውን፣ የዘመናችንን ጭራቅ ኢምፔሪያሊዝም ገድግደው ያቀሙ፣ ታላቅ ጀግና በመሆናቸው፣ አድናቆቴ ፅንፍ የለውም።

# ሰመነ

"... እንጀራውስ ይቅር፣ ወጡ የታለ ?" አለች ሰመነ በስተጉኗ ግራና ቀኝ ማዕድ ላይ የቀረቡትን ጓደኞቿን እየጉሸመችና በሹክሹክታ እየጠየቀች።

"ዝም ብለሽ ብትበዪ ይሻልሻል ! አለበለዚያ እዚያ ግድግዳ ላይ የተሠቀሉት፣ ጭራቅ ከነነፍስሽ ይውጡሻል !" አለ በማስፈራራት፣ ከበስተቀኟ የተቀመጠው፣ ካብሮ ዘመት ጓደኞቿ ሁሉ ተንኰለኛውና ቀበጡ ኪሩቤል።

"ውነቱን ነው፤ ትላንትና ሞግዚታችን፣ ባለጌ የሆናችሁትን ልጆች ሁሉ እኛ የግድግዳው ላይ አስፈሪ ሰውዬ ይቀጧችኋል ብለን የለ !" አለች ሶስና፣ ጓደኛቸው ኪሩቤል ላቀረበው የማስጠንቀቅያ ምክር ድጋፍ እየሰጠች።

"የቀረበልሽን ዝም ብለሽ ብትጠርጊ ይሻልሻል" አለ ኪሩቤል፣ እያስጠነቀቀ።

"እንዴ ምን ማለታችሁ ነው ! እኔኮ ወጥኮ በጣም ነው የሚጣፍጠኝ ! በተለይ ያኔ እማማ በእንቁጣጣሽ ዕለት የምትሠራው ወጥኮ፣ ከኮረሜላም ሆነ ከቸኩላታ ይበልጥ ያጓጓኛል ! ሲጣፍጥ ሌላ ነው ! እጅ ያስመጥጣል።" አለች ሰመኒ፣ የናትዋ ጣፋጭ ወጥ ትዝ ብሏት እንባዎቿ በሁለት ዓይኖቿ ዳር ዳር ቅዝዝ እያሉ።

"ጠብቂ ! እናትሽ ወጥ ታመጣልሻለች !" አለ ያ አብረው ከዘመቱት ወጣቶች ውስጥ፣ ሞላጫውና አሿፊው ኪሩቤል።

"እዚህ ሀገር እኮ፣ እንኳን ወጥ ሊሠሩ ቀርቶ፣ ራሱ ወጥ የሚለውን ቃል አያውቁትም። ሰመኒ ! እባክሽን እኛ ሁላችንም ብንሆን ወጥ ብናገኝ ጠልተን አይደለም። ግን ባገሩ ውስጥ፣ በጭያሽ ስለማይገኝ ነው፣ አለፍላጐታችን ይህን ፓስታና ሩዝ ከመኩሮኒ ጋር የምንውጠው !" አለች ሶስና የሰመኒን ፊት በማሐረቧ እያባበሰች።

"ሌላ ቀን እሺ፣ የዘወትር ቀን ስለሆነ፣ ማንኛውንም የሚያቀርቡልንን እንብላ ! ዛሬኮ የዕንቁጣጣሽ በዓል ነው ! ሌላው እንኳ ባይገኝ፣ እንዴት ያ የሚጣፍጠኝ ወጥ ይጥፋ ! እማማኮ ትዝ እያለች እያለች ... እያያለለችችኝኝ..." ሰመኒ፣ የናቷ ትዝታ፣ በዕንቁጣጣሹ በዓል ወጥ ምክንያት ተቀስቅሶበት እየተሠቀሰቀች ልቅሶዋን ታስነካው ጀመር።

"ኮምፓኜሮ ! ኮምፓኜሮ ! ምን ሆንሽ !" አለ ከበስተፊቷ ከጠረጴዛው ማዶ የተቀመጠው ሌላ ወጣት፣ የቀዘዘው እንባዋ፣ እየተንሰቀሰቀች ስታለቅስ በፊትዋ ላይ ሸረር እያለ ሲወርድ አይቶ።

"እሷ እባክህ፣ ወጥ ከአዲስ አበባ ካልመጣ ነው የምትለው !" አለ ያ ተንኮለኛው ኪሩቤል፣ እየሣቀ።

"እዚህም አንዷ የንጀራን ያለህ እያለች ትንሾኳሾክ ነበር !" አለ የበስተፊታቸው ልጅ።

"እብሲቱ ተጥሏል፣ ሲደርስ ይመጣልሻል፣ አትላትም" አለ ያ ኪሩቤል።

"ቀልዱን ተውና፣ ዛሬ መነጫነጫቸው ይገባቸዋል። እንዴት በዕንቁጣጣሽ ዕለት፣ በአዲስ ዓመት፣ ዓመት በዓል ምድር፣ ሌላው ቢቀር እንኳ፣ ወጥ አያዘጋጁልንም !





በዚህስ ጉዳይ እነሱን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ደብሮናል !" አለ ከበስተፊታቸው ተቀምጦ ያለው ጓደኛቸው፣ የኪሩቤልን ቀልድ እያከቸለቸለ።

"አንተም ለካ አልጫ መረቅና ደሮ ወጥ፣ በዓይንህ ላይ ብዥ ብሎብህ ነሯል !" አለ ኪሩቤል፣ መልሶ በጓደኛው ላይ እያሾፈ።

"ሁላችሁም ድብርታሞች ናችሁ ! መቀለጃ ብታጡ፣ በጓደኞቻችሁ ታላግጣላችሁ ! አንድ እንኳ ጤነኛ ልጅ ከማሐላችን ላይገኝ ነው !" አለች ሶስና እየተቸች።

"አንቺን ደግሞ ምን ትዝ ብሎሽ ይሆን ? ቀሎ ወይስ አሹቅ ! ቅራሬ ወይስ አሬራ ?" ኪሩቤል ሶስናን ማሽሟጠጡ ነው።

"እኔስ !" አለች ሶስና እንደመቆጣት እየቃጣት፣ "እኔስ የናፈቀኝ፣ የናቴ ወጥና እንጀራ፣ ወይም አንተ እንደምትለው፣ ቀሎና አሹቅ ወይም ቅራሬና አሬራ ሳይሆን፣ ራስዋ እናቴ ናት !" አለች።

"ጠብቂ፣ ከሰማይ ትወርድልሻለች !" አለ ያ ኪሩቤል ይበልጥ እያበሸቃት።

ማዕድ ላይ ተቀምጠው፣ እንዲህ እንዲህ ያለውን ትዝታ እያነሱ ሲበሻሸቁ፣ የሰመኒ የነፈረ ናፍቆት ገንፍሎ፣ ልቅሰዋን ቀጥላ ኖሮ፣ ያ ከበስተፊቷ የተቀመጠው ልጅ፣ ሞግዚታቸውን ካሉበት ክፍል ጠርቶ፣ ስለ ሰመኒ ሁኔታ ይነግርና ሞግዚቷ



ይመጣሉ። ማልቀስ የተከለከለ ስለሆነና፣ ከዲስፕሊን ጉድለቶች እንደከፍተኛም

ስለሚቀጠር፣ ሞግዚቷ ወዲያው አጣድፌው ሰመነን ቢሮአቸው ይወስዷታል። ከሩብ ሰዓት ቆይታ በኋላ፣ ይዘዋት ይመለሱና ከነበረችበት የማዕድ ወንበሯ ላይ ካስቀመጧት በኋላ፣ የቀረበላትን መመገብ ስትጀምር አይተው፣ ተመልሰው ወደ ቢሮአቸው ይሔዳሉ። ሰመነም፣ ውስጥ ውስጡን እየተንሠቀሠቀች፣ የቀረበላትን ያለ ምንም ቅሬታ መጥረግ ጀመረች።

"ኳያ ወይስ አሥር !" አላት ያ ተንኮለኛው ኪሩቤል፣ ገና ተቀምጣ መብላት እንደ ጀመረች፤ ሞግዚታቸውም ካካቢያቸው እንደ ሔዱ አይቶ።

"ኳያ ይሆናል እንጅ ! መዳፏን አታየውም ! ፍም መስሏል !" አለች ሶስና፤ እንደ ማስተዛዘንም፣ ደግሞም ምክሯን ስላልተቀበለቻት እንደ ማቋጨትም እየቃጣት፣

"ወጡን ወይስ እንጀራውን የሰጧት !" አለ ያ ኪሩቤል እየሳቀ።

ሲወረውረውም ሆነ ሲያነሳው አልታየም፤ ያ ከበስተፊታቸውም ያለው ልጅ፣ በኪሩቤል ቀልድ ተናዶ፣ ይበላው የነበረውን ገንፎ መሰል ሾርባ፣ ከነሣህኑ አንስቶ ከኪሩቤል ፊት ላይ ሲለድፍበት ብቻ፣ መላው ማዕድ ላይ የነበረ ወጣት በሁኔታው ይረበሻል። ደግነቱ ሣህኑ ከፕላስቲክ የተሠራ መሆኑ በጀ እንጂ፣ ከኒኬል ወይም ከመስተዋት የተሠራ ቢሆን ኖሮ፣ የኪሩቤልን መላ ገፅታ ወዲያው ባጨራመመው ነበር። በዚያ ግርግር አብዛኛዎቹ ደንግጠው፣ ግማሹ ሹካና ማንካውን ከወለሉ ላይ ሲጥል፣ የቀረው ደግሞ የሚመገቡትን ጠረጴዛ አናግተውት ኖሮ፣ ላጭርም ጊዜ ቢሆን፣ ቀበሮ ከመሐላቸው የገባችባቸው የበግ መንጋ መስለው ነበር።

"እኔ ሞግዚቷን መጥራቴ፣ ብሶቷን እንዲያበርዱላት፣ የለቅሶዋንም መነሾ ተረድተው፣ መፍትሔ እንዲፈልጉላት ነበር እንጂ፣ አንጠረኛ ያቀረበው የጋለ ብረት ይመስል፣ እጇን ፍም እስኪሆን እንዲቀጠቅጡላት አልነበረም አለ" ያ ከበስተፊታቸው የነበረ ልጅ፣ የለበሰውን ሸሚዝ እጅጌ ወደ ላይ እየጠቀለለ፣ ድብድብ የሚፈልግ ቢኖር እየተዘጋጀ። ምግብ አሰላፊዎቻቸው፣ አለወትሮአቸው፣ በወጣቶቹ እንደዚያ መሆን ተደናግጠው፣ የሚይዙትና የሚጥሉት ጠፋባቸው። የምግቡን አዳራሽ፣ ቱማታ ዋጠው። ከጥቂት፣ ዳር ላይ ካሉ ልጆች በስተቀር፣





በመላው ከመቀመጫቸው ተደናግጠው በመነሳት፣ ሁኔታውን ለማየት ይጣደፋሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ሞግዚቶቻቸውም አልመጡም ነበር። ብቻ ያ ኪሩቤል፣ ፊቱ ላይ የተለጠፈበትን ገንፎ መሰል ሾርባ፣ በዐሥር ጣቶቹ ይጧጥጣል። ከመቀመጫውም አልተነሣም ነበር። በጣም የሚገርመው ደግሞ፣ እንደዚያም ያለ ሁኔታ ገጥሞት፣ መቀለዱን አላቋመም ነበር። ልጆቹን ሁሉ ያሣቃችው "...... ሀገራችን ብንሆን ኖሮ፣ በዛሬው ቀን አባባዬ ሆይ ወይም ሆያ ሆዬ እንጨዋት ነበር ! ይኸ አሁን የምታዩት ድርጊትም፣ የእንቁጣጣሽ በዓል መስተናገጃ፣ የዚህ ያለንበት ሀገራችን ያበባዬ ሆይ ጨዋታችን መሆኑ ነው !" ያለው ፌዝ ነው። መጋቢዎቻቸው፣ ሞግዚቶቻቸውን ሊጠሩ ሔደው ኖሮ፣ አምስቱም ሞግዚቶቻቸው ከተፍ አሉ። ወዲያው፣ የዕለቱ የምግብ ፕሮግራም ሰዓት የተፈፀም መሆኑን፣ ለሁሉም ልጆች ነግረው፣ ወደ የመኝታ ቤታቸው ሲበትኑ፣ ለዕለቱ ረብሻ ምክንያት የሆኑትን፣ አምስት ልጆች መርጠው የምርመራና የጠባይ ማረሚያ ብለው ወደ ሰየሙት፣ አንዲት ጠባብ ክፍል ወስደው ያሸጓቸዋል። ሰመነ፣ ሶስናና ኪሩቤል፣ ከቀሩት ሁለት ጓደኞቻቸው ጋር፣ በዚያች ክፍል ብቻቸውን በነበሩበት ወቅት፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው፣ ሞግዚቶቻቸውን የሚመክቱበትን መከላከያ ሐሳብ ይመሣጠራሉ። ያዘጋጁትም ዘዴ፣ "አንዱ መጋቢያችን ነው፣ ኪሩቤል ላይ ሾርባውን አውቆ ከነ ሣህኑ የለጠፈውና፣ እዚህ ሀገር መኖር አንፈልግም ! ለቅጣትም ሆነ ለሌላ፣ ሀገራችን እንድ ትመልሱን እንጠይቃለን" የሚል ነበር። ........"ሀገራችን መልሱን ከሚለው ርእሰ-ሐሳብ ላይ ለመነሳት፣ አሳማኝ የሆኑ ምክንያቶችን መደርደር ነበረባቸው። ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ፣ ያጋጠማቸውን ልዩ ልዩ ችግሮችና ብሶቶች፣ በየመልካቸው መወያየትና መተንተን ነበረባቸው። ለዚህ ዐይነቱ ዝግጅት፣ ያምስቱ ጓደኛሞች ጥፋተኞች መባልና በተወሰነች ትንሽ ክፍል ውስጥ መገለል፣ ጥሩ አጋጣሚና ምቹ ቦታ ሆኖላቸዋል። ለሁለት ዓመታት ጊዜ፣ በሕፃንነት ላጋ ዕድሜያቸው፣ ያለ ውዴታቸው ሲያመነዥኹ የኖሩትን የስቃይ ማዕድ ሁሉ፣ እንደገና ተንትነው በማየት፣ ማመስኳት የጀመሩት በዚያ ወቅት ነው። ቀደም ሲል

ግን፣ የሚፈፀምባቸውን በደል መተንፈሻ ቀዳዳ ባገኙ ቁጥር፣ በያጋጣሚው ለማጋለጥና፣ በትንሹም አቅማቸው ከማመጽ አልተቆጠቡም። ወላጅ አባቶቻቸው፣ የፋሽስት መንግሥት በፈጠረው ለራስመዳኛ ተብለው በተፈጠሩ፣ ምክንያት—የለሽ ጦርነቶች፣ በጦርነት ሜዳው በመውደቃቸው፣ የካሣን ይሉ የማባረርያ፣ ተብሎ በተዘየደ ጥበብ፣ ከአንድ የወላጅ ሀገር መናገሻ ከተማ ከሆነው ውስጥ፣ እየተማሩ እንዲያድጉ፥ የተበየነባቸው አሳዛኝ ወጣቶች ናቸው። ገና ዓላማው ተወጥኖ፣ ሐሳቡ ለወላጅ እናቶች፣ አንዳንድ ልጆቻቸውን፣ ለጉዞው እንዲያዘጋጁ ሲነገር፤ ባሎቻቸውን አለአግባብ ላጡት ወላጅ እናቶች፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖባቸው፣ ለወር ጊዜ ያህል፣ ለቅሶ በለቅሶ፣ እንባ በእንባ ሆነው፣ የወላጅ አንጀታቸው፣ እርር ትክን ሲል ሰንብተ ነበር። ሕፃናቶቹም ቢሆኑ፣ ባጡአቸው አባቶቻቸው፣ የደረሰባቸው ሐዘን ገና እንፋሎቱ ሳይከስም፣ ከወላጅ እናቶቻችሁ ተለዩና፣ ባዕድ ሀገር ሒዱ፣ የሚል አስደንጋጭ መዓት ሲመጣባቸው፣ ሊደርስባቸው የሚችለውን፣ ሠቀቃውና ሆደ ባሻነት፣ ማንም ሰው ሊረዳው ይችላል።

ወደዱም ጠሉም፣ እናቶቻቸውንም ሆነ ሀገራቸውን፣ ከባሕላቸው ጋር ጥለው የመሔዱ ጉዳይ፣ ከላይ በጫና የወረደ፣ ፋሽስታዊ ትእዛዝ በመሆኑ፣ ዝም ብሎ ከመንጉድ በስተቀር፣ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። የህን ትእዛዝ ለመጣስ የሞከሩ፣ ባለአንድዬ ልጅ የሆኑ እናቶች፣ አንድ ልጃችንን አንሰጥም በማለት፣ በማንገራገራቸው ብቻ፣ እውስጥ ይሆን ስመጥ፣ የት እንደደረሱ አይታወቅም። ከያሉበት ተሰባስበው፣ አዲስ አበባ ካለ አንድ የጉዞአቸው መዛጋጃ ሥፍራ በነበሩበት ወቅት፤ አለመጠን አግተ ከነበረው፣ ከያንዳንዱ ተጓዥ ወጣት፣ በየቀኑ ይታለብ የነበረው የዕንባ ፍሳሽ፣ ከጋሎኖች አልፎ በርሜሎችን ሊያጥለቀልቅ ይችል ነበር። እንግዴን ከትብቱ በመቀሥ ተጉመዱትን ያህል ነው፣ እናቶችንም ሆነ ተጓዥ ልጆቻቸውን የተሰማቸው። አንዳንዶቹን እናቶችማ፣ ልባቸውን እንደመንካት አድርጓቸው፤

“ሞትና መለየት ምን አንድ አደረገው፣





እትብቱ ተቆርጦ፤ ከራቀ ከናቱ፤
ምኑን ሰው ይሆናል፤ የሰው ልጅነቱ!

ሞት ይሻል የለም ወይ ቁርጡ የታወቀው !" የሚለውን ዘፈን እያዜሙ፣ የለቅሶ ያህል ተጠቅመውበታል። "የልጆቻችን ሞግዚቶች እንሁን የሚሉትንም እንደ ሆነ፣ እዚሁ ሃገራችን መጥተው፣ ምን ዐይነት ሰዎች እንደሆኑ አይተናቸዋል። እነዚህን እምቦቃቅላ፣ ሕፃናት ከነዚያ ሕዝቦች ሀገር ወስዶ ማስተማሩ፣ የወደፊት ጥፋታቸው እንጂ፣ ልማታቸው አይታየንም።" በማለት፣ ቅን ሀሳባቸውን የሠነዘሩ ሰዎች ሁሉ፣ ሞተዋል ወይም እሥር ቤት ናቸው። ሕፃናቱ ሀገራቸውን ለቀው ለመሔድ ከየናቶቻቸው እየነጠቁ ሲያመጡ፣ የነበረውን ግዜያዊ ትርዒት ለመግለፅ፣ የየትኛውም ቋንቋ ቃላት ቢሆኑ ዐቅም አይኖራቸውም። በእንደዚያ አሸባሪ ግዴታ ተወስደው፣ ከሞግዚት ሀገር ከተማ ከደረሱ በኋላ፣ የመጀመርያውን ዓመት ጊዜ እንዴት እንዳሳለፉት መግለፁ፣ ቋንቋን አያስጠቅስምና፣ ዝም ማለቱ ይበጃል። የሕፃናቱ የመከራ ስንክሳር ይከፈትም ከተባለ፣ ራሳቸው በሦስተኛ ዐመቱ፣ የእንቁጣጣሽ በዓል ዕለት፣ የጀመሩትን የዐመፅ ዝግጅት ሲተነትኑ በነበሩበት ወቅት፣ የሆነውን ራሳቸው ይናገሩ።

"ጠባሳዬ ዛሬም እያመረቀዘ ነው ! ተመልከቱ !" አለች ሰመነ፣ የክንዷን እጅጌ ወደ ላይ እየጠቀለለች፣ የእንቅልፍ መርፌ እያሉ፣ ለዓመት ያህል ሲጠቀጥቋት የነበረውን ክንዷን እያሳየች፤ በዚያች ጠባብ የመቅጫ ክፍል ውስጥ እንዳሉ።

"ማን ያልቀመሰ አለ ብለሽ ነው፣ ለኛ የምታሳዩን ! ይልቁንስ እንዴት ባለ አቀራረብ ብንፅፈው ነው፣ ብሶታቸንን በጉልህ ሊያሳይልን የሚችል ?" አለች ሶስና፣ አቤቱታቸውን ለማቅረብ በሥውር እያዘጋጁ ነው።

"ለመጻፉ ችግር የለም ! ግን ቅደም ተከተሉን ማስተካከል ይኖርብናል !" አለ ያ ኪሩቤል በጸሐፊነት የተመረጠው እሱ ነበርና።

"ቅደም ተከተል፣ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው ?" አለ ያ ፊቱ ላይ፣ ሾርባ የቸለሰበት ጓደኛው።

"ቅደም ተከተል ስል፣ ያኔ ገና ወደ እዚህ አገር ልንመጣ ስንዘጋጅ፣ እናቶቻችን የሆኑትን መሆንን፣ እኛን ከነሱ ላለመነጠል፣ ያደረጉትን የተቃውሞ ተጋድሎ፣





በዚህም መነሻ የደረሰባቸውን ፍዳና ግፍ፣ ኋላም እኛ በዚህ በባዕድ ሀገር፣ እናቶቻችንም በሀገራችን ሆነው፣ የሚሰማንና የሚሰማቸውን የናፍቆት ሰቀቀን፣ እንደ ፋብሪካ እቃ የራሳቸው ሥራ አርገው ለማውጣት፣ በየዕለቱም ስለሚጫወቱብን ድርጊት፣ ..." ማለቴ ነዋ !

"እሱማ ምን ይቀራል ! የእኔ እናት፣ አንድ የነበርኩ ልጇ፣ እኔ ያለፍላጐቷ፣ እዚህ ተገድጄ በመምጣቴ ያለቀሰችበት ሁሉት ዐይኗ ጠፍተ፣ እውር መሆኗን፣ አንድ ጓደኛዬ በተዘዋዋሪ ፅፎልኝ፣ ደብዳቤዋ ደርሶኛል።" አለ 5ኛው፣

"እኔ ከተለየኋት ጀምሮ፣ ከአልጋ ላይ ሳትወርድ፣ እንደማቀቀች ያለች መሆኑን፣ በየጊዜው በመስማቴና የናቴም ጤንነት፣ እንደወትሮ ሊሆን የሚችለው፣ እኔን ስታገኝ ብቻ መሆኑን ስለአማውቅ፣ ለዚህ ግብ መታገል እንዳለብኝ የናንተን ምኞትና ሐሳብ አላውቅም እንጅ፣ የኔ የግሌ ምኞቴና እዚህም እስካለሁ ድረስ፣ የማንቀሳቅሰው መፈክሬ ነው !" አለች ሰመነ፤ ለዚህም አባባሏ፣ ባንድነት "እናቱን የሚጠላ ማን አለ !" አሏት፣

"እኔ ብዙ ጊዜ እንደማስበው ከሆነ፣ ተቃውሞአችን መልክ እንዲይዝና ክብደትም እንዲኖረው ከፈለግን፣ እንደ ጭራቅ ማስፈራርያ የሆነብንን፣ የዚህን የግድግዳ ላይ ሥዕል፣ ከክፍላችን፣ ከምግብ ቤታችን፣ ከመኝታ ቤታችንና እኛ ከምናይበት ቦታዎች ሁሉ እንዲነሳልን እንጠይቅ። አቅማችን የማይፈቅድልንም ቢሆን፣ ቀራጥነታችን በሚያስገኝልን ጉልበት ተደፋፍረን፣ በሕግና በሥርዓት እንዲያነሱልን የጠየቅነውን ባይፈፅሙ፣ በተባበረ ዐመፅ ተነሳስተን ፎቶግራፉ፣ ከተሰቀለበት ቦታ ሁሉ እያወረድን፣ እንክትክቱን እናውጣ። ምናልባት ይኸ ተግባራችን ብቻ ወደ ሀገራችን ለመመለስ የሚረዳን፣ ዐይነተኛ ምክንያት ባይሆንም እንኳ፣ ለጀመርነው ተቃውሞ ጥሩ መነሻ ምክንያት ሊሆን ይችላል እላለሁ" አለ፣ በኪሩቤል ላይ ሾርባ ቸላሹ ወጣት፣ በተግባር እንጅ በጽሑፍ አቤቱታ አለማመን እየገለጠ።

"ምንም ሕፃናት ብንሆንም ቅሉ፣ የደረስብን ችግርና መከራ፣ ያጉለመሰን መሆኑ፣ ሁላችንም የተሰማን ይመስለኛል ! አሁን እሱ ያለው ጥሩ ነው። ግን ሰዎቹ

ሞኞች ስላይደሉ፣ ዐመፃችንን ለማብረድ፣ በጥያቄችን መሠረት፣ የመሪውን ፎቶ አንስተው የኛን "ሀገር መሪ" ይቱኩ ይሆናል። የኛ ዐመጽ ግብ ግን፣ ሀገራችን መመለስ ነው። ታድያ በፎቶው መለወጥ ሊሸነግሉን ቢፈልጉስ ?" አለች ሰመነ።

"እዚህ አምጥቶ፣ መከራችንን እንድንጠብስ ያደረገው ዋናው እሱ አይደለ እንዴ ? የሱንማ ፎቶ ቢተኩ፣ ጭራሽ ከተሰቀለበት አለማውረድ ነው። እዚያው እንዳለ መስተዋቱን እያንከታከቱ በፎቶው ላይ ቀለም መቸለስና፣ የሆነ ያልሆነ ነገር እየፃፉ ማብሸቅ ነው !" አለች ሶስና።

"የራሱን ልጆች ሞስኮ ኤምባሲ ልኮ ያቀማጥላል። እኛን ግን እዚህ አምጥቶ፣ በባይተዋርነት በባቢሎን ከተማ፣ የቸነፈር እሳት ያቃጥላል ---የምትሉት፣ ለመሆኑ እናንተም እንደሱ ልጆች፣ በአምባሳደር የኑሮ ደረጃ፣ ከልዩ ወጭ ጋር ለመንቀባረር ትፈልጋላችሁ እንዴ ?" ያ ነገረኛ ኪሩቤል፣ ከጥቂት ጋብታ በኋላ፣ የተለመደ አሽሙሩን ሲጀምር የተናገረው ነው።

"በላ አንተ ደግሞ፣ እንደቀሩት ቁርጠኛ ደጋፊዎቹ ተከላከልለታ ! እኛ ግን በምንችለው ሁሉ፣ ተቃውሞ ፈጥረን አገራችን የምንመለስበትን መንገድ፣ ከማዘጋጀት ወደ ኋላ አንልም። ሶስናም ያለችው ወርቅ ነው። የሱን ፎቶ መተካታቸው አይቀርም። እንዳለችው መስተዋቱን እየሰባበርን፣ ፎቶው ላይ፤

"ትልቁ ጆኮር፣ ትላንት ቢጠፋ፣

ትንሹ ጆኮር፣ ዛሬ ተስፋፋ !"....እያልን፣ እንለጥፍበታለን" አለ፣ ያ ኪሩቤል ፊት ላይ ሾርባ የቸለሰው ልጅ።

"ይልቁንስ ሌላውን ተውና፣ የተቃውሞ አቤቱታችንን በምን መነሻ ላይ ብናደርገው ይሻላል። እዚህ ላሉትም ጥቂት ደጋፊዎቻቸው አብሮ ዘመቶች፣ ቢቻል ልናሳምናቸው እንሞክራለን፣ አለያም ምሳቸውን እንሰጣቸዋለን" አለች ሰመነ።

"እንግዲያውስ፣ መጀመር ያለብን፣ መሠረታውያን በሆኑ ነገሮች ላይ በመነሳት ነው። ይኸውም፣ "ሰው የአካባቢው ውጤት ነው፣" የሚለውን ትልቅ ሀሳብ፣ በተለይ እኛን በሕፃንነት እድሜያችን፣ ከሀገራችን አስወጥቶ፣ በሌላ ሕዝብ አከባቢ ተወስደን፣ እንድንማር መደረጉ፣ ትክክል አይደለም፣ የሚለውን





መነሻ ይዘን፣ ከዚያ በማከታተል የደረሰብንን፣ መከራና ሥቃይ፣ በደልና ፍዳ፣ ግፍና ጭቆና መዘርዘር ይኖርብናል። ያቤቱታችንንም ትክክል ግልባጭ፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሳይቀር መላክ አለብን !" አለች ሶስና፣ የአቤቱታቸውን ከፍተኛነት እያማሚቀች "ኮፒውንስ ለሰው መብት ጠባቂ ለተባሉ ዓለም-አቀፍ ድርጅቶችና ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፣ ለገለልተኞች ማኅበርና፣ ለቀሩትም ሁሉ እናሠራጫለን !" አለ አምስተኛው፣ ዝምተኛ መሳይ ልጅ።

"በተለይ፣ እርስ በርስ የሚጋጩ ባሕሎች ካሉበት ሀገር፣ እኛን መሳይ ሎጋ ሕፃናት መላክ፣ ወንጀል መሆኑን ካነጠርን፣ አቤቱታችን የሚያስቀጣ ጭምር እንደሚሆን መጠራጠር የለብንም። ምክንያቱም፣ በዚህ እድሜያችን፣ ስንት ዐይነት ቅጠ-ቢስና ጋጠወጥ ዜጋ ካለበት ሀገር፣ "ተማሩ" ብሎ መላኩ፣ ምን ለመማር እንደሆነ፣ የትምህርቱ ይዘት መጋለጥ አለበት" አለች ሶስና።

"በዚያ ሰሞን፣ ሞግዚት እናቴ፣ ቤቷ ይዛኝ ስትሔድ፣ ሁለት ጠና ጠና ያሉ ሴቶች፣ መንገድ ላይ አግኝተውን፣ "የየት ሀገር ልጅ ናት ?" ብለው ጠየቁና፣ ዜግነቴን ከተረዱ በኋላ፣ ሁለቱም፤ "ልጆቻችንን ወስዳችሁ፣ በጦርነት ማጥ ውስጥ አስውጣችኋቸው ቀሩ-የትም ወድቀው ! ደግሞ ይቺ እዚህ ምን ልታደርግ መጣች ብለው !" ተንደርድረው እንዴ በጥፊ ቢወለውሉኝ፣ ምድር ሰማዩ ዞሮብኝ፣ የተፈጠርኩበትን ቀን ሳይሆን፣ እዚህ ሀገር የመጣሁበትን ቀን ረገምኩ ! ይህ፣ ወጣ ባልን ቁጥር የሚያጋጥመን ነው። እንዲህ ያለው ሁሉ፣ አቤቱታችን ውስጥ መጠቀስ አለበት።" አለች ሰመነ በየጊዜው የተፈፀመባትን ትልልቅ በደል እያስታወሰች።

"በዚህ ዐይነት አያያዛችን፣ ምንም መጻፍ እንደማንችል ተረዱ ! ሁላችሁም ብልጭ የሚልባችሁን በደል ብቻ ስትዘበዝቡ፣ በሥርአት አጠናቅረን፣ አቤቱታውን ማቀናጀትና መጻፍ የሚሆንልን አይመስለኝም !" አለ ኪሩቤል ከየአቅጣጫው እየተዝረከረከ የሚቀርበውን ብትን ሐሳብ፣ በመልክ በመልኩ አድርገው ማቅረብ እንዳለባቸው ጓደኞቹን እየመከረ። ይህን ምክሩን ተናግሮ ሊጨርስ ሲል፣ ሁሉቱ ሞግዚቶቻቸው፣ አለወትሮአቸው በጣም ማልደው፣ ወዳሉበት ክፍል በመምጣት፣ ድንገት በሩን ከፍተው ከቸች አሉ። መጨረሻ ላይ

ይናገር በነበረው ኪሩቤል ላይ፣ አጉርጠው አፈጠጡበት። ደግነቱ፣ አቤቱታቸውን ባቀረቡት ወረቀት ላይ አላሠፈሩም እንጅ፣ ጽፈውት እንዳለ ደርሰውበት ቢሆን ኖሮ፣ የሚደርስባቸው ቅጣት ሌላ ይሆን ነበር። አምስቱ ሕፃናት ሌሊቱን ሙሉ፣ ችግራቸውን ሲያወጡና ሲያወርዱ እንቅልፍ የሚሉ ባይናቸው አልዞረ ኖሮ፣ የሁሉም ዐይኖች ቀልተዋል። ነገር ሲጉነጉኑ እንዳደሩ፣ ሁለቱም ሞግዚቶች ጠርጥረው፣

"ተመልከቺው ያ ተንኰለኛ፣ ዐይኑ የጦጣ ዐይን መስሏል !" አለች አንዷ ሞግዚት፣ ለሌላዋ።

"ማ እኔ ! የኔ ዐይን ነው የጦጣ የመሰለው ?" ኪሩቤል ይጠይቃል፣ ለማረጋገጥና መልስ ለመስጠት እያሰላሰል።

"አዎ! ያንተ ነው !" አለች፣ ሞግዚቷ እየተቆጣች።

"በጦጣ ዐይንሽ አይተሽኝ ይሆናል !" አለ፣ኪሩቤል የመጣው ቢመጣ እንደቀረጠ ለማሳየት። ገና እንደገባች የተተናኰለችው ሞግዚት፣ ተንደርድራ ኪሩቤልን አጮለችው። የመገላገያ ዜዴ ያገኘች መሰሏት፣ ድንገት የመጣላትን ሐሳብ ተጣድፋ እያቀረበች፣

"እኔ ሌሊቱን ታምሜ ሳቃስት በማደሬ እንቅልፍ ሊወስዳቸው ባለመቻሉ ነው፣ ዐይናቸው የቀላው !" አለች ሰመነ ዶክተር ለማየት መፈለጓን፣ ለሞግዚቶቹ እየገለፀች። በዚያች የማረሚያ ጣብያ በሆነች ጠባብ ክፍል ውስጥ፣ ጠባያቸውን እንዲያርቁ ተብሎ፣ ያለፍርድ ከተወሰነባቸው አንድ ሳምንት አልፏቸዋል። የሞግዚቶቹና ያምስቱ ሕፃናት የማለዳ ግብግብ፣ ገና በአፈናው ላይ እንዳለ፣ ሁለት የኤምባሲ ባለሥልጣኖች ከውጭ ይገባሉ። ሰላምታ ከሁሉም ጋር ከተለዋወጡ በኋላ፣ ዲፕሎማቶቹ፣ ስለችግሮቻቸው ሕፃናቱን ይጠይቃሉ።

"በርግጥ አእምሮ ያላቸው ወገኖች ብትሆኑ ኖሮ፣ እዚህ እንዲህ ስንሠቃይ እየሰማችሁ ባላስቻላችሁ ነበር !" አለች ሰመነ፣ የኤምባሲ ባለሥልጣኖችን እየነካካችና እየወቀሰች።

"አእምሮማ አላቸው። የሚጠቀምቡት ግን፣ ለእንደዚህ ዐይነቱ ድሪጊት ማራመጃ





ብቻ ነው !" አለ ኪሩቤል፣ የኤምባሲዎቹ ሰዎች፣ በዚያች ጠባብ የጠባይ ማረሚያ ክፍል መገኘታቸው፣ የልብ ልብ ሰጥቶት።

"ታዲያ ይህን መሣዩን አእምሮ፣ ምን አእምሮ ትለዋለህ ! ብሶት የሚያራምድ አእምሮ፣ አእምሮ አይባልም !" አለ ያ ኪሩቤልን፣ የሾርባ ዱላ ያቀመሰው ልጅ። ለካስ አእምሮ፣ አእምሮ፣ እያሉ ደጋግመው ያነሱት አለምክንያት አልነበረም። በዚያ ቀን ማለዳ ከመጡት፣ ሁለት ዲፕሎማቶች ውስጥ አንደኛው፣ አምባሣደሩና የሚጠሩበትም ስማቸው፣ "ኅሊና" የሚባል ኖሯል። እሳቸውም፣ በልጆቹ ድፍረትና የዕብሪት አነጋገር እንደመብሸቅ በለው፤

"ስንት ጨዋ ልጆች አገር ቤት እያሉ፣ እናንተ እዚህ መምጣታችሁ ነው፣ ትልቁ ጥፋት። የምትሠሩትን ጥፋት ሁሉ፣ በየጊዜው ተከታትለን ደርሰንበታል። ይህን ሁሉ የውርጋጥ ጠባያችሁን፣ ለምን እንደምታስፋፉ፣ ዓላማችሁ ግብቶናል። ወልጋዳ ባሕርያችሁ፣ እዚሁ ሀገር ውስጥ እንዲታረቅ ይደረጋል እንጅ፣ ሀገር ቤት እንድትመለሱ አይረዳችሁም። የናንተ የጥቂቶቹ ተንኰልና ሤራ፣ መላውን ሕፃናት፣ ለጊዜው ማሳደም ቢቻልም፣ አድማው ጊዜያዊ ነው። እያደር ይሠክናል። አሁንም ደጋግሜ የምነግራችሁ፣ በእንደዚህ ዐይነቱ የሤራ ሙከራ፣ አገር ቤት የመመለስ እቅዳችሁና ምኞታችሁ፣ በጭራሽ ሊሳካ እንደማይችል ነው..." አሉ አምባሣደር ኅሊና፣ እነኪሩቤልን እያስፈራሩ።

"ማነው ሀገራችን ካልገባን ያላችሁ !" አለች ሰመነ፣ ምሥጢራቸው እንዴት እንደወጣ ለማወቅ እየጓጓች።

"ለምን ትዋሺያለሽ ! ይኸ የማነው ድምፅ !" አለ፣ አምባሣደሩን አጅቦ የመጣው፣ ሁለተኛው ዲፕሎማት፣ ከወደ ብብቱ ስር የወሸቃትን፣ ብልቃጥ የምታህል ድምፀ-መቅርፅ አውጥቶ፣ "ሀገራችን መመለስ አለብን !" የሚለውን የራሷን ድምፅ በጉልህ እያሰማ።

"ለሁሉም" አሉ አምባሣደር ኅሊና "ለሁሉም፣ ሊቀመንበር ስሞኑን ለጉብኝት ስለሚመጡ፣ በዚያን ቀን የወደፊት ሁኔታችሁ ይወሰናል !" ብለው፣ ደኅና ሁኑም ሳይሉ፣ ጭልጥ አሉ። የመጡትም ቢሆን፣ አምስቱን የታሠሩ ሕፃናት ለማየት

ሳይሆን፣ በነሱ ምክንያት፣ ትምህርት አንማርም ብለው፣ ከሁለት ቀናት በፊት አድማ የመቱትን፣ ጓደኞቻቸውን ለማነጋገር ነበር።

"አመፅ ብቻውን፣ ሀገራችን ይመልሰናል !" ደኅና ይሁኑ እንደማለት፣ አምባሣደሩ ሲመለሱ፣ አምስቱም ሕፃናት ያሰሟቸው ድምፅ ነበር። አምባሣደሩም፣ ሌላ መልስ ሳይሰጡ፣ ሽምጥጠው ሲሔዱ፣ ተከትሎአቸው የመጣው ዲፕሎማት፣ እነዚያን ሁለት ሞግዚቶች፣ አምባሣደሩ ሊያነጋግሯአቸው እንደሚፈልጉ ገልጾ፣ ይዟቸው ወጣ። ሞግዚቶቹም፣ በሩን ከርችመው ከወጡ በኋላ፣ እስከቀኑ የምሣ ሰዓት ድረስ፣ ወደ ታሠሩት ሕፃናት አልተመለሱም። ምሳ ሰዓት ላይ፣ አምስቱም ሞግዚቶች፣ ከት/ቤቱ አስተዳዳሪ እመቤት ጋር ሆነው፣ እነሰመነን ለማነጋገር ሲመለሱ፤ እንደወትሮው ለዱላ ሳይሆን፣ አዲስ ዜናና፣ ልዩ ማስጠንቀቂያ ለመንገር ነበር። መላው የት/ቤት ሕፃናት፣ እነሰመነ ከታሠሩበት ነፃ እንዲወጡ፣ ለሁለት ቀናት ያደረጉት የትምህርት ማቆም አድማ፣ ተሰሚነት አግኝቶ ኖሮ፣ ይኸንንው ለመንገር ነበር። ይሁን እንጅ፣ አምስቱ ልጆች ነፃ የሚወጡት፣ በገደብና በልዩ ማስጠንቀቂያ ነበር።

"ዛሬ በነፃ የተለቀቃችሁት፣ የትምህርት ቤቱን አስተዳደርና፣ የመምህራን ጉባኤ፣ አምባሣደራችሁ ይቅርታ እንዲ ደረግላችሁ በመጠየቃቸው ብቻ ሲሆን፣ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት፣ ጠበያችሁን ባታሻሽሉና እንዳለፈው ጊዜ ተመሳሳይ ድርጊት በነጠላም ሆነ በቡድን ስትፈጽሙ ብትገኙ፣ ከፍ ያለ ቅጣት እንደሚጠብቃችሁ ተወስኗል። በተለይም፣ ሰመነና ኪሩቤል፣ ከዚህ በፊት በየጊዜው ለተጫሩ አለመግባባቶች ሁሉ፣ መነሻ ክብሪቶች መሆናችሁ ስለተረጋገጠ፣ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባችሁ ተወስኗል። ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት እረፍት የተሰጣችሁ በመሆኑ፣ ክፍል ባትገቡም አትገደዱም። መልካም ዕድልና የጠባይ መሻሻል እመኝላችኋለሁ !" ይህን ቃል ያሰሟቸው፣ በአምስቱ ሞግዚቶቻቸው ምሥክርነት፣ የት/ቤታቸው አስተዳዳሪ እመቤት ናቸው።

ከዚያች ማፈኛ ክፍላቸው እንደወጡም፣ አድማ ለሁለት ቀናት የመቱላቸው፣ መላው አብሮ–ዘመት ጓደኞቻቸው፣ በሩቅ አዩአቸውና፣ እንደንብ እየሮጡ





ከበቧቸው። ከዚያም፣ ሆ ! እያሉ፣ አምስቱንም ተሸክመው ወደ መሰብሰቢያቸው አደራሽ ከወሰዷቸው በኋላ፣ በመላው ተማሪዎቹ ስም፣ አንድ ወጣት "እንኳን ነፃ ወጣችሁ !" የሚል አጭር ንግግር በማድረግ፣ የመላው ተማሪ መተባበርና አድማ መምታት፣ ነፃ ሊያስወጣቸው እንደቻለ ገልጾ፤ ከታሠሩ ቀን ጀምሮ፣ መላው አብሮ–ዘመት ጓደኛ፣ በሐሳብ አብሮአቸው እንደከረመ አስረድቶ፣ ጭብጨባው ቀለጠ። ለተደረገላቸው ድጋፍና አቀባበል፣ ባምስቱ ወጣቶች ስም፣ ኪሩቤል የሚከተለውን አጭር መልስ ሰጠ።

"ስላደረጋችሁልን ድጋፍና አድማ፣ ባለውለታዎቻችሁ ነን። ነገር ግን፣ ነፃ ወጣችሁ የምትሉንን ጉዳይ ፈፅሞ አንቀበልም። ባሳለፍናት አንድ ሣምንት የመራራ ጊዜያችን ወቅት፣ ለሁላችሁም የሚስማማ አንድ መፈክር አዘጋጅተናል። ይኸውም "ሀገራችን መመለስ አለብን !" የሚለው ነው። ይህ መፈክር ተሟልቶ፣ ሀገራችን እስካልገባን ድረስ፣ እዚህ ሀገር እያለን፣ ነፃ ወጣችሁ ብትሉን፣ አይገባንም !" ብሎ ሲጨርስ፣ የቀሩት አራቱ ያፈና ቤት ጓደኞቹ፣ ከተቀመጡበት ተነስተው፣ ጮክ ብለው በመናገር ባንድነት ድምፅ፣

"ቃላችን ነው" አሉ። ከዛ ወቅት ጀምሮ ነበር፣ የደጋፊዎችና የተቃዋሚዎች የድንበር መስመር በጉልህ የለየው።

"ሀገራችን መመለስ አለብን !" በሚለው መፈክር ያልተስማሙቱ ወገኖች፣ አንድ አንድ እያሉ አዳራሹን እየለቀቁ ወጡ። የመፈክሩን ስንኩልነት ለማስረዳትም፣ ጥቂቶች ሽንጣቸውን ገትረው ተሟገቱ።

"ለመሆኑ እዚህ በመምጣታችሁ፣ ምን ተበደልን ነው የምትሉት ?" የክርክሩ እንብርት ይህ ነበር።

"ያለንበት ሀገር፣ ምን ዐይነት ኅብረተ–ሰብአዊ ሥርዓት ያለበት ሀገር ነው ? ይህ ጥያቄ፣ እዚህ በመምጣታችን ምን ተበደልን ነው የምትሉት ? ለሚለው ጥያቄ፣ መስቀልያና አጠቃላይ መልስ ሊሰጥ ይችላል !!" የሚል መልስ ነበር፣ ከመፈክሩ ደጋፊዎች የቀረበ አስተያየት።

"ይህች ሀገር፣ የኅብረተ–ሰብዓዊ ሥርዓት የሠፈነበት ሀገር ከመሆኗም በላይ፣

ብዙ የትግል ልምድ ያፈራችና በተለይም ሀገራቸውን፣ ከኋላ ቀር የአስተዳደር ቁራኛና ከኢምፔሪያሊስቶች ቀንበር ለማላቀቅ፣ የቅርብ ረዳት የሆነች ሀገር ናት" የሚል መልስ፣ ከመፌከሩ ተቃራኒዎች ቀረበ።

"አይደለችም !" አሉ የመፌከሩ ባለቤቶች።

"ናት !" አሉ መፌከሩን የሚፃረሩ ወገኖች።

"አለመሆኗን እናስረዳ !" አሉ ባለመፌከሮቹ።

"ከሆነላችሁማ ደስ ይለናል !" አሉ ተቃዋሚዎች። በዚያ ጊቢያቸው ውስጥ፣ በዚያ ረዥም የሁለት ዓመታት ጊዚያቸው፣ ነፃ ሐሳባቸውን፣ ባደባባይ ሲገልጹ፣ የመጀመሪያ ጊዜያቸው በመሆኑ፣ ባጋጣሚው ያልተደነቀ የለም።

"ከስር እንጀምር !" አሉ ባለመፌከሮቹ "አንድ ሀገር፣ ወይም አንድ ሕዝብ፣ የምርት ምንጮችን በቁጥጥሩ ስር ማድረጉ ብቻ ኅብረተ–ሰብአዊ ሥርዓትን አስፍኗል ማለት አይቻልም። ዋናው ቁም ነገር ግን፣ የዚያ ኅብረተ–ሰብአዊ ሕዝብ፣ ቁጥጥር ላይ በዋሉት የምርት ምንጮች፣ ምን ያህል ተጠቃሚነትና አዛዥነት አለው ? የሚለው ጉዳይ ነው። ሕዝብ በሚለው ምትክ፣ የዚያ ኅብረተ–ሰብ፣ ላባ–አደር የሆነው ሠራተኛው መደብ፣ ብንል ይሰምራልና፣ የሀገሩ ሠራተኛው መደብ፣ በነዛ የምርት ምንጮች ላይ ምን ያህል የወሳኝነት ሥልጣን አለው? ብትባሉና መልስ ብትጠየቁ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ ኮንግሬስ፣ የሠራተኛው ፓርቲ... ምንትስ፣ ምንትስ የሚወስነው ስለሆነ፣ የሠራተኛው መደብ ተጠሪዎች ናቸውና፣ ላባ–አደሩ ቀጥተኛ የሆነ፣ በምርት ምንጮች ላይ የማዘዝና የማስተናበር ሥልጣን አለው፣ ልትሉን ይሆናል። ይህን፣ በጭራሽ አንቀበልም። ሀገራቸው፣ በተወሰኑ የክሊክ ቁንጮዎች የምተመራ፣ እነዚህም እፍኝ የማይሞሉ ኢዲሞክራታዊ ባለሥልጣኖች፣ ለሀገሪቱ የምርት ምንጮች ፈላጭና ቆራጭ፣ አዛዥና ናዛዥ፣ የአዲሱ ኢምፔሪያሊዝም ገባሮች፣ እጅ ከጓንት ብቻ ሳይሆን፣ ጥርስና ከንፈር ጭምር ሆነው፣ ከሶቭየት ኅብረት ጋር፣ ባንድነት የምትራመድ ሀገር ናት። በዘመናችን፣ በየትኛውም ክፍለ–ዓለም፣ ራሻውያን ከንፈሮች፣ ለብዝበዛ መጠጣ





ተሰማርተው በገለፈጡ ቁጥር፣ የዚህ ሀገር ሰዎች ጥርሶች ወለል ብለው ይታያሉ። ይህም የምዝበራ ዘመቻቸው፣ በዝርዝር ሲተነተን፣ የሚከተለውን ያንፀባርቃሉ።

-- በደካማ ሀገሮች ውስጥ ጣልቃ ባመግባትና፣ የሀገሩን ሥልጣን ከሀገሩ መሪዎች ጋር በሽርክና ተዳብሎ በመያዝ፣ የራሳቸውን ዓላማዎች ለመቀየስና ግቡን ለመትለም፣ ሲያስገድዱ ወይም በራሳቸው የወታደር ኃይል በመጠቀም፣ የቀድሞውን መሪ ከሥልጣን በማውረድ፣ በምትኩ ብጤያቸውን ፑፔት ሲተኩ ታይተዋል። ሶቭየቶች ባፍጋኒስታን፣ ባንጎላና በሀገራችን፣ ይህ ተግባራቸው ተከናውኖ በማየታቸው ተደስተው፣ እስክስታ ሲመቱ፣ የዚህ ሀገር ሰዎች፣ አጨብጫቢዎቻቸው ነበሩ።

-- ከባድ የወታደር ትጥቅና ሠራዊት በማዘጋጀት፣ የቀረውን ዓለም በመርዛማና በአቶሚክ የጥፋት መሣሪያዎቻቸው ያሸብራሉ። በሌሎች ደካማ ሀገሮች ወታደራዊ ምሽጎችን ለወረራ ያዘጋጃሉ። የጋራ ወታደራዊ ስምምነቶች በሚል ሽፋን፣ የደካማ መንግሥታትን ወታደራዊ ኃይል፣ በራሳቸው ቁጥጥር ውስጥ እንዲውል አርገዋል።

-- የወታደርና የሲቪል አማካሪ–ሠራዊት በየሀገሩ በማሠራጨት፣ በባሕል፣ በፖለቲካና በትምህርት ተቋሞች ውስጥ ሠርገው በመግባት ሥር ሰደው፣ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅ መመሪያ በማውጣት፣ ያን ደካማ ሕዝብ ይመርዛሉ፤

-- አንድ ወጥ የሆነ፣ የፋብሪካ እድገት ብቻ እንዲስፋፋ በመገፋፋት፣ ለዚያ ፋብሪካ የሚያስፈልጉትን እቃዎች፣ ከራሳቸው መንግሥት ብቻ ሁልጊዜ ተመፅዋቾችና ገበያተኞች እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል–ዝርዝር ውስጥ እየገባን፣ የኛን አባቶች የበላ፣ የጦር መሣርያ፣ በሶማሌያ በኩል ሆነ በሌላው፣ ከየት የተገኘ መሆኑን አለመግለፃችን፣ ታውቆት ይሆናል በሚል ግምት ነው።

-- ያልተመጣጠነ የንግድ አቋም ስምምነት በመዋዋልና በመደራደር፣ የራሳቸውን፣ ከጥቅም ውጭ የዋለ ሸቀጣ ሸቀጣቸውን፣ ደካማዎቹ ሀገሮች፣ በውድ ዋጋ እንዲገዙና፣ በምትኩም፣ የነሱን ጥሬ እቃ እንዲሸጡ በመገፋፋት፣ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ሲያዳብሩ ይታያሉ።

-- ከፍተኛ ወለድ ያለው ብድር በመስጠትና፣ ያንንም ያበደሩትን ገንዘብ፣ ከዚያው ካበዳሪው መንግሥታቸው ብቻ የሚገኘውን ሸቀጥ እንዲገዙበት፣ በተለዩ የውል ስምምነቶች በመቸንከርና፣ ብድሩም የሚከፈለው፣ በየጊዜው በሚሰጥ ጥሬ እቃ እንዲሆን ያስገድዷቸውና፣ ሲዘርፉ ይኖራሉ፤

-- በተለይም የሦስተኛ ዓለም ሀገሮችን፣ ያረጁባቸውንና ጊዜ የከዳቸውን የጦር መሣሪያዎች እንዲገዙ በመስበክና በማባበል፣ የረከሠ ሸቀጥ መጣያ ያደርጓቸውና፣ ይህም የድራ ገበያቸው እንዳይቋረጥ፣ መለዋወጫ እቃዎቹን ከነሱው ብቻ የሚገኙ በመሆናቸው፣ ከነሱው በስተቀር ወደ ሌላ ገበያ ውልፍት እንዳይሉ በተጠቀሰው የመለዋወጫ እቃዎች እግረ–ሙቅ ከርችመዋቸው፣ ከነሱ ዘንድ በስተቀር እንዳይንቀሳቀሱ አስረዋቸዋል።

-- ከራሳቸው ሀገር ይልቅ፣ ገና ድንግል ከሆኑት፣ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች የተፈጥሮ ሀብት ላይ በመጣበቅ፣ እነዚህንም ያልተቦጠቦጡ ሀገሮች፣ ለጥሬ እቃዎች ፍላጐታቸው ምንጭ በማድረግና፣ በኃይልም ሆነ በዘዴ፣ ወይም በአጋርነት በመጠጋት፣ ፍፁም ጥገኛቸው ያደርጓቸዋል።

-- በኤኰኖሚ ለበለፀጉ ሀገሮች ጥቅምና፣ ለራሳቸውም የዚህ ጥቅም ስውር ሽርክና ሲሉ፣ የኢምፐሪያሊስት ግብረ–አበሮቻቸውን፣ የገንዘብ ዋጋ ከፍ ያደርጉታል።

-- የራሳቸውን ኢምፔሪያሊስታዊ የውጭ ጉዳይ መመሪያዎች፣ ጥገኛ ላደረጓቸው ታናናሽ ሀገሮች ሁሉ፣ በግድም ሆነ በውድ እንዲከተሉ፣ በውል ሳይቀር ያስገድዷቸዋል። ብሬዥኔቭ፣ ወይም፣ ሌላ ሶሻሊስት ነኝ ባይ መሪ የተነፈሰውን የፖሊሲ ድምፅ፣ የሀገራችን አምባገነን ወዲያው ተቀብሎ ሲያላዝንበት የሚከርመው፣ ወዶ ሳይሆን፣ የዚህ የገባበት ውል ግዴታ እንደሆነ ማንም የሚያውቀው ነው።

-- ያንድ ሀገር መሪ፣ የሕዝቡ ቅን አገልጋይ መሆን ብቻ ሲገባው፣ እንደ አማልክት መመለኩ፣ ለዝናውና ለስሙ ብቻ መጠበቂያ እየተባለ የሚፈሰው ገንዘብ፣ በሀገሩ ውስጥ ስንቱን የተራብ አንጀት ማራስ ሲችል፣ ስንቱን ሥራ አጥ





ወገን፣ ሥራ ሊፈጥርለት ሲችል በከንቱ መባከኑ፣ የነዚህ በስም ሶሻሊስት የሆኑ ሀገሮች፣ መንግሥት አንቀሳቃሽ የሆኑ የጥቂት ቡድን (ክሊክ) ቁንጮዎች፣ መመዘኛ የሚሆን ሌላው ጠባያቸው ነው።

"እንግዲህ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው፣ ጉልሆቹ የኢምፔሪያሊስትነት መንፀባረቂያ ባሕርያት ናቸው። ይህች ሀገር፣ እናንተ እንደምትሉት፣ ሶሻሊስት ሀገር ሳትሆን፣ የነዚህ ኢምፔሪያሊስታዊ ባሕርያት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሠረፀባት የመጣች ሀገር ናት። በስመ–ሶሻሊስትነት ካልሆነ በቀር፣ ዘመኑ በሚጠይቀው የኢምፔሪያሊስነት ታክቲክ ከመጠቀሟ በስተቀር፣ በዓለም ኢምፔሪያሊስትነቱ ከለየለት፣ ከአሜሪካ መንግሥት፣ በምንም ዐይነት የምትለይ አይደለችም። ስለዚህም፣ በኢምፔሪያሊስት ቁጥጥር ስር በወደቀ ሀገር፣ የሚገኙ የዋሃንና ለጋ ሕፃናት፣ ምንም ዓይነት ችግር የለባቸውም የምትሉን፣ በጭራሽ አይገባንም። ሊገባንም አይችልም..." በማለት ሰፊና አጠቃላይ የሆነ መልስ፣ ለተቃዋሚዎቻቸው አቀረቡ።

"ምን ይቸግረናል ?" የሚል ጥያቄ ያቀረቡላቸው፣ ተቃዋሚዎቻቸውም፣ ወዲያው በማከታተል፤

"ብዙ በማታውቁት፣ የፖለቲካ ማጥ ውስጥ ገብታችሁ ዳክሩልን አላልናችሁም ነበር። በጣም የተጠቃለለ ዲስኩራችሁ ውስጥ ከመግባት ይልቅ፣ እዚህ ሀገር ሳላችሁ፣ ምን የከፋ ችግር አጋጥሟችኋል ? ነበር፣ ጥያቄያችን። ደግሞስ፣ ሀገራችን እንመለስ የሚል ጥያቄ እስከማቅረብ፣ የሚያደርስ ምን በደል ተፈፀሞባችኋል ? ነበር እንድታስረዱን የፈለግነው..." አሉ፣ ተቃዋሚዎች፣ የሰጧቸውን መሠረታዊ መልስ በማቃለል።

"ሌላውን እንተውና፣ ለዚህም ጨቅላ ጥያቄያችሁ፣ መልስ እንስጥ ! መልሳችንም ጥያቄ ይሆናል። ከሀገራችን ወደዚህ ሀገር ስንመጣ፣ ለመምጣት ምክንያት የሆነው መሠረታዊ ዓላማ ምን ነበርን ?" አሉ የመፈክሩ ደጋፊዎች።

"ትምህርት !" አሉ፣ ተቃዋሚዎቻቸው በጣም ተጣድፈው።

"ጥሩ ! ትምህርት ነው። ትምህርት በበኩሉ፣ የኅብረተ–ሰቡ ሥርዓታዊ ይዘትና

የኢኮኖሚው ነፀብራቅ ነው። እፍኝ የማይሞሉ የክሊክ አባሎቻቸውና ቁንጮው፣ በፈለጉት ሚና ለሚረጩት የኤኮኖሚ ሀብት፣ እንደፈለጉ ለሚያዘብት የምርት ምንጭ፣ በፈለጉት አቅጣጫ ለሚነዱት ያስተዳደር ሠረገላ፣ እንደሞኞታቸው ለሚዳኙበት መቅጫ ሕግ... ዐይነተኛ ዋና መሣሪያቸውና መገልገያቸው፣ ትምህርት ነው። በዚህ ዐይነቱ የትምህርት ፋብሪካዎቻቸው ውስጥ፣ እንደናንተ ያሉትን ደጋፊ ዎቻቸውን፣ በሚፈልጉት የባሕርይ ቅርፅ ዐይነት፣ አቅልጠው፣ ጨፍልቀው፣ አድቦልቡለው ወቅረው፣ በመጨረሻም ላይ፣ አጥበውና ቀብተው፣ ወልውለው ያወጣሉ። ይህ ዐይነቱም ሰው—ሠራሽ ሰው፣ ሞቱን ሳይቀር የማይፈራ አገልጋያቸው ይሆናል። ይህ ዐይነቱ ትምህርት፣ ከሚሰጥበት የትምህርት ፋብሪካዎቻቸው መገኘታችን፣ ራሱ የበደል በደል ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ነን። ባሕላችንም ሆነ ኢትዮጵያዊ ሰብዕናችን፣ በረጋ—ሠራሽ የጭንቅላት አጣቢዎች፣ መታጠብ የለበትም። ሀገራችንም እንመለስ የምንለው፣ ከዚህ ነጥብ ላይ በመነሳት ነው። ...” አሉ።

“ባሕላችን የምትሉት፣ የቱን ባሕል ነው ? የፌውዳሉን ወይም የግማሽ ከበርቴውን ባህል ነው !...” አሉ ተቃዋሚዎች፣ መከራከሪያ ነጥብ ያገኙ መስሏቸው።

“ከቤተ—ሰብ ያስተዳደግ ሥርዓት አንስተ፣ በሕይወት ጉዞአችን ውስጥ የምንጠቀምባቸው፣ ምግባችን፣ የየብሔረ—ሰቡ ቋንቋችን፣ ሕዝባዊ በዓላችን ሐቀኞች አንጋፋዎችን ማክበራችን፣ ብሔር ወጥ ልብሳችን ...ሁሉ፣ ከትውልድ የተላለፋልን፣ በሔራዊ ቅርሶቻችን ናቸው። ሰፋ ባለ አመለካከት ብትመረምሯቸው፣ እናንተ ሳትጠመቁ ከምታምኑበት፣ ከዚህ ሀገር ረጋ—ሠራሽ የሶሻሊስት ባሕል መቶ በመቶ ይበልጣል !” አሉ።

“ስንኩል መልሶቻችሁን ማዳመጡ ቢሰለችንም፣ ድምር ትችታዊ መልስ መስጠቱ ይሻላልና፣ ዓለም—አቀፍ ይዘት ስላለው፣ እዚህ ስለምንማረውስ ትምህርት ምን ትላላችሁ !”

“የምናጠናው ጆኦግራፊ ሳይቀር፣ የኢትዮጵያን ዐባይ፣ ራስ ዳሽን፣ጣና ሳይሆን፣



# እትብቱ አሻራ !

ሥጋ ለብሶ ያለ ባለንበት ምድር፣
ጭራሽ አላየሁም፣ እንብርት የለሽ ፍጡር፣
አሻራ ማንተም ምንጭ እሚመሠክር።
እትብት ነው ሰሙ እናት ልጅ አሳሪ፣
ተፈጥሮ ያተመው፣ ያንድነት አብሣሪ!
ገዶታ እንኳ ሆና፣ ቢቆረጥም ቶሎ፣
አብረው እንዲኖሩ አብረው የበቀሉ፣
እትብት ማስረጃ ነው፣ ከሌላውም ሁሉ።
ተወላጅ ከወላጅ ተራርቆ እንዳይኖር
እትብት ማስረጃ ነው የተፈጥሮ ምሥጢር!
አብረው እንዲኖሩ ሰዎች የሚመክር!
ናሽናሊስት ሁሉ፣ ገብቶት ያለም ሥርዓት፣
ተለውጦ ቢሆን ኢንተርናሽናሊስት
የሰው እኩል መሆን ገብቶትና አምኖበት፣
ማነው ከቶ በምድር ተደስቶ እማይኖት!!
ይህንን ለማድረግ የዘየዱት ሥርዓት፣
ትክክል አይደለም፣ ያንዳንዶች መንግሥታት፣
የተጠቀሙበት የዘዴያቸው ዓይነት።
ሆያ ሆዬ ባዩን፣ ያልባለቀ ሕፃን፣
ገና በለጋነት፣ ሲቦርቅ ያለውን፣
ከወላጅ ከሀገር፣ ነጥቆ ወስዶ በግድ፣
በባዕዳን ምግዚት፣ እንዲያድግ ማስገደድ፣
በወላጁም ሆነ ያለራሱም ፈቃድ፣
ትክክል አይደለም፣ ያድራጎቱ ሥራት፣
ካልሆነ በስተቀር፣ በሕፃን መጫወት፣
ባሕር ማዶ ወስዶ፣ ማስጨነቅ ሕፃናት፣
አሳልፎ መስጠት ለባዕድ ሞግዚትነት።
ኋላም ከውጭ አድገው፣ በሌሎች ባሕል ውስጥ፣
እጠራጣሪ ነው ጠባያቸው በርግጥ፣
ይሆናል ማለቱ፣ መሰል እንዳገር ወጥ።
በግሉ መወሰን፣ የማይችልን ሕፃን፣
ለሞግዚት መስጠቱ፣ ያውም ለባዕዳን፣
ከወንጀል አያንስም፣ ቢታይ በፍትህ ሥልጣን።
ለጋ ሕፃን ሁሉ፣ ቢወድም ባይወድም፣
ማደግ ይሻለዋል፣ እናት ሀገሩ ዓለም፣
ወጉ እንደሆነው፣ ሆና ለዘለዓለም፣
አፈር ቅሞም ቢሆን፣ ቢያጋጥመው ሌላም፣
ለየትኛውም ልጅ፣ ሀገሩ ናት ጣዕም፣
ባሕሉን ይዞ እንዲያድግ፣ ሌላ አማራጭ የለም
ነውና እትብቱ፣ አሻራው ማንተም፣

የዚህን ሀገርና የሩስያን ወንዞች፣ ተራሮች፣ ባሕሮች ነው። የራሳችንን ቋንቋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረሳን፣ በነሱው ቋንቋ እየተካን ነው። በለጋ እድሜያችን ላይ፣ ካገር የወጣን በመሆናችን፣ ስናጠነጥን የቆየነው የአእምሮችን ዕውቀታዊ ክር፣ ጠንካራ ባለመሆኑ፣ በቀላሉ ሊተረተር ከመቻሉም በላይ፣ የዚህ ሀገር መሪዎች በትምህርት ስም አስታከው የሚያቀርቡልንን፣ ብሔራዊ ፍላጐትና ምኞት መከላከልም ሆነ መመከት አልቻልንም። ከተወሰነልን ጊዜ በኋላ፣ ሀገራችን የመመለስ ዕድል እንኳ ቢገጥመን፣ እናቶቻችኚንም ሆነ፣ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን፣ ብምን ቋንቋ ማነጋገር እንደምንችል አናውቅም። በተለይም ይብልጥ እየገፋፋ ለአመፅ የሚያዘጋጀን፣ ትምህርት ተብሎ ከሚቀርብልን፣ ሦስት አራተኛውን እጅ የሚሸፍነው፣ ሙዚቃ፣ ቲአትርና መዝሙር ነው። ጭቁን ሕዝባችንን በሚመለከት ይዘት ላይ ያተኰረ ቢሆን እንኳ፣ ብንማርም ምንም አልነበረም። የሚያሳዝነው ግን፣ ያ ሁሉ የሙዚቃ፣ የቲአትርና የመዝሙር ዝግጅትል፣ ውዳሴ የኢት.ና ያለንበት ሀገር መሪዎች ብቻ መሆኑ ነው። ላንቃችን እስኪደርቅ ድረስ መሸተ በነጋ ቁጥር "ውዳሴ–ከንቱ" ሲያስጮሁን ይውላሉ። ይህ ዐይነቱ ትምህርት፣ ለኢትዮጵያ ዐብዮትም ሆነ፣ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ፣ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደማይችል፣ ከገባን ቆይቷል። ይህ ሁሉ ብሶት ተጠራቅሞ ነው፣ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ተሰብስበን ለመወያየት ያበቃን !" አሉ፣ የመፈክሩ ደጋፊ ዎች።

"አሁን ፍጆታው የኛ ነው ! ለቀባጠራችሁት ምላሽና፣ ላነገባችሁት ሰንካላ መፈክር፣ ትክክለኛውን አስተያየታችንን እንሰጣለን። በተቀዳሚ ልትረዱልን የምንፈልገው፣ የዓለም–አቀፍ ወንድማማችነት መንፈስ ተጀምሮ እስኪጨረስ ያልሠረፀባችሁ መሆናችሁን ነው። ይህ መንፈስ ቢኖራችሁ ግን፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ባሕላችን፣ እያላችሁ በውሱን ናሽናሊስትነት ባላናፋችሁም ነበር። ግን ወደዳችሁም ጠላችሁም፣ ያለማችን ባሕልም ሆነ የተራማጆች ኪደት፣ የሚያመራው፣ ወደዚሁ እናንተ ወደ ጠላችሁት ግብ ነው። ዓለም–አቀፋዊነት ዳብሮ በሚጐለብትበት ጊዜ፣ ሀገራችን እያላችሁ ያቅነዘነዛችሁ፣ ኢትዮጵያ





የሚለው ሥያሜ ሳይቀር ተውጦ፣ የሚጠፋበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። የዚህ ትግል አሮበኞችም እነብሬዤኔቭ፣ የሀገራችሁና የዚህ ሀገር መሪዎች ናቸው። የኛም በዚህ ተራማጅ ሀገር መገኘት፣ የነሱ ትግል ያስገኘው ፍሬ ነው። የወዳሴ መዝሙር እንዳላችሁትም ብንዘምርላቸው፣ ቢያንሳቸው እንጅ አይበዛባቸውም። የዚህን ሀገር መሪ እንኳ ትተን፣ የሀገራችሁን መሪ፣ በሀገራችሁ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ረሀብ፣ሥራ አጥነት፣ ድንቁርና፣ በሽታ፣ ድራሽ አባታችው ጠፍቶ፣ ለምልክት ያህል እንኳ አይገኙም። ከሀገር ቤት ተርፎ፣ ይኸው እኛንና እናንተን ተቃዋሚዎቹን ጭምር እዚህ ሀገር ድረስ እንድትመጡ አስደርጎ፣ ይኸው ተንቀባራችሁ እስክታስችግሩ ድረስ አብቅቷችኋል። ደግሞም..." ብሎ የተቃዋሚዎች ተጠሪ ወኪል፣ ንግግሩን ሳይጨርስ፣ ቀደም ብለው አዳራሹን ለቀው በወጡ የተቃዋሚ ወገኖች ጠቋሚነትና መሪነት፣ ተራ ልብስ በለበሱ ፖሊሶች፣ አዳራሹ ተወረረ። ከዚያም የመፈክር ደጋፊዎችና የመፈክር ተቃዋሚዎች፣ ሁለት ስዓት በፈጀ ጊዜ ውስጥ ተበጥሮ ተለየና፣ የመፈክር ተቃዋሚዎች ከሌሎቹ እንዲገለሉና እንዲዝናኑም ታስቦ፣ ልዩ መኪና ቀርቦላቸው፣ ወደ ኤምባሲ ሲወሰዱ፣ የቀሩት የመፈክር ደጋፊዎች ግን፣ እንደ ወንጀለኞች ተቆጥረው፣ ቅጣትና ምርመራ ለማድረግ፣ ሁለት ሁለት አርገው እያጣመሩ፣ ወደ አልታወቀ ቦታ ተወሰዱ። በአፈሣው ግርግር ጊዜ፣ ያ የመፈክር ተቃዋሚዎች ተጠሪ ሆኖ፣ ንግግር ያደረገውና አጠገቡ የነበረ ጓደኛው ብቻ፣ የፊት ጥርሶቻቸውን፣ በተሠነዘሩ የተቃዋሚዎቻቸው ቡጢዎች ሲያጡ፣ ሌላ ኮሽ ያለ ነገር አልነበረም። ከዚያ ቀን ጀምሮ፣ ያ በሕፃናት ሁካታ ሲምቧች የነበረ የት/ቤታቸው ግቢ፣ ለወር ጊዜ ያህል ጭር ብሎ ሰነበተ። የመፈክር ተቃዋሚዎች ሲዝናኑ፣ የመፈክር ደጋፊዎችም ሲሠቃዩ፣ ከከረሙባቸው ቦታዎች፣ በአንድ ቀን ውስጥ ወደ ት/ቤታቸው ተመለሱ። ተዝናኚዎቹም ረክተው፣ ተሠቃይዎችም መሮአቸው ሳይሆን፣ ወደ ት/ቤት የተመለሱት፣ የሀገራቸው መሪ የመጎብኛ ጊዜ የተቃረበ በመሆኑና፣ ከመጡ ጀምረው ሲያጠኑ የኖሩትን፣ ሙዚቃ፣ ቲአትር፣መዝሙር፣ እንደገና እየከለሱ እንዲያዘጋጁ ታስቦ ነው።

ሁለቱ የለየላቸው ተቃራኒ ወገኖች፣ በየቀኑ የጐሪጥ እየተያዩ፣ ዝግጅቱ ሲደረግ ሰነበተ። ከዚህ በፊት ለአምባሣደሩ ቃል በገቡላቸው መሠረት፣ የመፌክሩ ባለቤቶች፣ በልመና ሳይሆን በአመፅ፣ መፌክራቸው በሀገራቸው መሪ የጉብኝት ጊዜ እንዲፀድቅ ለማስደረግ፣ ልዩ የሆነ የስውር ዝግጅት ማቀናበር ጀመሩ። በዚህ ዝግጅታቸው ውስጥ፣ የራሳቸውን መፌክር የሚመለከት፣ ልዩ መዝሙር ይገኛል። እንደተባለውም፣ "የሀገራቸው መሪ" ለአሥር ቀናት ኦፌሲያል ጉብኝት ለማድረግ ካሉበት ሀገር ገባ። ከነዚህ ቀናት ውስጥ፣ የአንደኛው ዕለት ፕሮግራም "የታዳጊ ተራማጅ ኢተዮጵያውን ተማሪዎች ጉብኝት" የሚል ነበር።

ገና ስምንት ቀን ሲቀረው፣ ያገር ሠራተኛ ተሰብስቦ፣ የት/ቤቱ በርና መስኰት ሣንቃዎች፣ ልዩ ልዩ ቀለሞች ተቀቡ። ወሃ ነክቶአቸው የማያውቁ የወለል እንጨቶች በናፍታና በዘይት ተወለወሉ። ሣር እንኳ ተጉዝጉዞባቸው የማያውቁ የሲሚንቶ ወለሎች፣ ቀይ ግምጃ በመሰለም ንጣፍ ተሸፈኑ። በመኝታ ቤቶችም ውስጥ፣ እየተንጣጣ እንቅልፍ አላስወስድ ብሎ የከረመ፣ የእንጨት አልጋ ሁሉ፣ በሚያረገርጉ የሽቦ አልጋዎች ተተኩ። ለወራት ሳይቀየርና ውሃ ሳይነካው የነበረ አንሶላና ብርድ ልብስ ዝተት፣ በወርጀናሌ መብሩቅና በሱፍ ብርድልብስ ተቀየረ። የሽንት ቤቶች አሸንዳዎች ሳይቀሩ፣ ተረስተውና ዝገው ሲኖሩ፣ ባዳዲስ ተተኩ። ሙጃ ለብሶ፣ የቢንቢና የትንኝ መፈንጫ የነበረው የኳስ መጫወቻው ሜዳ፣ ከስታዲየሞች አንዱን ይመስል ያህል አማረበት።

ጫማ ተነፍጓቸው የከረሙ፣ የሕፃናት ሻካራ እግሮች ሁሉ፣ በካልሲ ሳይቀር ተዋቡ። በዚያ ከተማ ታይቶ የማይታወቅ ዩኒፎርምም ስለተሰጣቸው፣ እላያቸው ላይ አልቆ የነበረው ቡትቶ ልብሳቸው፣ መጣል ብቻ ሳይሆን ተቃጠለ። ዘይት ያላየው ሾርባቸው፣ በቅቤና በሥጋ ሳይቀር ተዝናና። ውሃ መጠጫቸው ብርጭቆ ሳይቀር ተለወጠ። የፍራ ፍሬ ጭማቂ መጠጦች፣ በምግብ ቤት ቧምቧዎቻቸው ሁሉ፣ እንደውሃ ፈሰሱ። እንዲያ እንዲያ ተደረገና፣ የት/ቤታቸው ሁለንተና ሲያሸበርቅ፣ የተባለው የሀገራቸው መሪ፣ ከክብር አጃቢዎቹ ጋር፣ በአንደኛው ሰንበት ከቸች አለ። አበባው ባንገታቸው ሳይቀር ተጠለቀ። ዙሪያውን ጐበኙ፣ ማሸብረቁን





ዐይተው፣ በልጆቹ እድለኛነት ቀኑ። ቅልጥ ያለ የምሣ ድግስ ተበላ። የሀገሩ መሪና የሀገራቸውም ከተማ ገዥ ንግግር አደረጉ። ተጨበጨበ። የመጨረሻው ፕሮግራም፣ በተማሪዎቹ የሚቀርበው፣ የሙዚቃ፣ የቲአትርና፣ የመዝሙር ዝግጅት ስለነበር፣ ልዩ ልዩ የውዳሴ ዝማ ፈሰሰ። አባባ መሪ፣ እማማ ገዥ ተባሉ። ሊያልቅ አሥር ደቂቃዎች ሲቀር፣ ነገር መጣ። እነዚያ "አገራችን መልሱን" የሚሉት ወገኖች፣ የሚከተለውን ልዩ መዝሙር ይዘው አናወጡት ॥

<u>ሰው ባገሩ</u> !

"አዕላፍ ነው ክብሩ !
ሰው ባገሩ ! ሰው ባገሩ፣ ሰው ባገሩ !
　　አዝማች፡– ከውድ ሀገራችን፣
　　　　　　አትሔዱም ብትለን፣
　　　　　　ባመፅ እንገባለን !
ቢበላ ሣር፣
ምናምንቴ ቢማር፣
　　ቢበላ መቅመቀ፣
　　ቢማር ከጨለንቀ፣
እየዋጠ ዶኬ፣
እየሳለ ቀኬ፣
　　ይከበር የለም ወይ፣ ሰው መሆኑ ታወቀ፣
　　በባዕዳን ሀገር፣ ከሚኖር ወላልቆ።
ለያይቶ ከናቶች፣
ለጋ ሕፃናቶች።
　　ሆነ ማሠቃየት፣
　　ምልክት የፋሽስት !

መልሰኝ ብያለሁ ከሀገሬ፣
ከዚህ ሀገር ትምህርት፣ ይሻል መደንቀሬ።
የቀረጠ አንጀት፣ እንደተከሉኝ ቅጠል፣
አያቀጠቁጥም ምንጊዜም ቢቀጠል ‼ ...”



በዚህ፣ ዜማው ከይዘቱ በተዋጣለት፣ ከተቀመጡበት በሚያስነሳ መዝሙር፣የነበሩበትን አዳራሽ ብቻ ሳይሆን፣ የት/ቤቱን ጊቢ ሳይቀር አናጉት። አብሮ የነዘረ ልብ ቢኖር፣ የሀገራቸው ገዥ ጭምር ነው። ከተተረጐመ በኋላማ ያሉብትንም ሀገር መሪ ቀሽት አደረቀው። ይሉኝታም ይሁን ሀፍረት አይታወቅም፣ ቀራጦቹ ሕፃናት ያን ፀረ–ፋሽስት የሆነ መዝሙራቸውን ይዘው ሲደልቁት እስተናጋጁም የሀገሩ መሪ ሆነ፣ እንግዳው ያገራቸው አምባ–ገነን፣ ትንፋሽም አልወጣቸው። ምድረ–አንጋች ሁሉ ሲቅበጠበጥ፣ አጃቢዎቹ ተከታዮች በሙሉ





ሽምቅቅ ብለዋል። ያ እንደ ማዕበል ሞገድ፣ አዳራሹንና ጊቢውን ያናወጠው መዝሙር በሚዘመርበት ወቅት፣ በተሰጣት መምሪያ መሠረት፣ ሰመነ ከመሐላቸው ወደ መድረኩ ጫፍ ብቅ እያለች፣

“አመፅ ብቻውን ሀገራችን ይመልሰናል !”

የሚለውን መፈክራቸውን፣ ጣልቃ እያስገባች፣ ጮክ እያለች ታሰማ ነበር። የሀገራቸውም አምባገነን ገዥ፣ ያልጠበቁት አባዜ መጨረሻ ላይ ገጥሟቸው፣ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ዝምታ ውጧቸዋል። አምባሣዳሩ እንኳ፣ መዝሙሩን አቁሙ ለማለት አስቦ፣ ያሉትን የውጭ እንግዶችና ዲፕሎማቶች፣ የበስተኋላ ትችት የፈራ ይመስላል፣ አልደፈረም። ወጣቶቹ ራሳቸው መዝሙሩን አሉት፣ አሉትና ሲበቃቸው፣ መጨረሻ ላይ “በትዕግሥት ስላዳመጣችሁን እናመሠግናለን !” በሚል የተባበረ አንድነት ድምፅ ተናገሩና እንግዶቹን አሰናበቱ።

“ከመሔዳችን በፊት ስላቀረባችሁት አሳብም ሆነ ሌላ ነገር እናነጋግራችኋለን!” የምትለውን ዐረፍተ–ሐሳብ ብቻ፣ እንደምንም ተንፍሰው ሲመጡ የተደሰቱትን ያህል፣ ሲመለሱ በሽቀው ጭልጥ አሉ። ምድረ–አጃቢ ሁሉ በሆዱ ጉድ እያለ፣ እንግዳውን አምባገነን ተከትሎ ሸመጠጠ። የበዓሉ ዝግጅት በዚህ ሁኔታ ከተፈፀመ በኋላ፣ ለዕለቱ ሁሉም ተማሪዎች፣ የቀሩትን ተጨማሪ ሰዓቶች፣ እንደፍላጐታቸው እንዲዝናኑበት ተፈቀደላቸው።

በዚህ በዓል ላይ፣ ለሕፃናቱ በበጐ ፈቃድ የተመደቡ፣ ያሉብት ሀገር ቤተሰቦች ጥሪ ተደርጐላቸው መጥተው ስለነበር፣ ለሰመነ የተሰጡትም የሀገሩ ቤተሰቦች ተገኝተው ነበር። የፕሮግራሙ ዝግጅት እንዳበቃ፣ ሁሉም ቤተ–ሰቦች ምድብ ልጆቻቸውን እየተሰናበቱ፣ ወደየቤታቸው ሲሔዱ፣ የሰመነ ቤተሰቦች ግን በተለይም የዚያ ሀገር ሞግዚታዊ እናቷ፣ በጣም ስለሚወዷት፣ በዚያንም ወቅት ረዘም ላለ ጊዜ እቤታቸው ያልሔደች መሆኗን፣ ለአንድ ለሚያውቋት ሞግዚቷ ነግረው ወደ ቤታቸው ይዘዋት ይሔዳሉ። የሰመነ ቤተ–ሰብ የሚጨነቁላት፣ በተለይ ስለወላጅ እናቷ የሚሰማትን ጭንቀት ስለሚያውቁ ነው። እነሱም ቢሆኑ ደስ ብሏቸው የሚኖሩ ሰዎች አይደሉም። በተለይ ባልየው በፖለቲካ ግፊት ምክንያት፣


እንደታሠረና እንደተፈታ የኖረ ነው። ያ ትልቅ በዓል፣ በነሰመኒ ት/ቤት ከተከናወነ በኋላ፣ በማግሥቱ አንድ ትንግርት ተፈጠረ። ሰመኒ ለአንድ ቀን ዕረፍት፣ ከሀገሩ ሞግዚታዊ ቤተሰቦቿ ጋር ለመቆየት፣ አብራቸው ከሔደች በኋላ እንደገና አልተመለሰችም። በጣም የሚደንቀው ደግሞ፣ እሷ ብቻ ሳትሆን የጠፋችው፣ ሁለቱ ቤተሰቦቿ ባልና ሚስት ጭምር ናቸው። የቀሩት የሰመኒ ጓደኞች ሁሉ፣ የሷ መጥፋት ከታወቀ በኋላ፣ ብረት በያዙ ወታደሮች መጠበቅ ተጀመረ። ካሉበት ክፍልም፣ ደጋፊዎች ሳይቀሩ፣ ወደ ውጭ መውጣት ተከለከሉ።

በዓሉ በተከናወነ በአራተኛው ቀን፣ የሀገሩ መሪና እንግዳው አምባገነን ወደ ትምህርት ቤቱ ተመልሰው መጡ። አመጣጣቸው ሌላ በዓል ለማክበር አልነበረም። በቀረበላቸው የምርመራ ውጤት መሠረት፣ በት/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይዘሮ አማካይነት፣ ሕፃናቱን ለማነጋገርና፣ ፍርድ ለመስጠት ነበር። ግን በተማሪዎቹ አድማ ምክንያት፣መልስ የሰጣቸው አንድም አልነበረም። የሀገራቸው እንግዳ አምባገነን፣ "ውስጄ ሀገሬ ፍርድ ልስጥ" ሲሉ፣ ያገሩ መሪ ደግሞ "እድሜያቸው አይፈቅድም" ሲሉ፣ አምባገነኑ እንግዳ "ባገራችን፣ ወንጀለኛ ፍርድ አያስፈልገውም !" ሲሉ፣ ክርክር ገጥመው ከቆዩ በኋላ፣ እዚያው ባሉበት ከተማ እንዲቀጡ ተበይኖ፣ ዛሬም ሕፃናቱ ቅጣት ላይ ይገኛሉ። ሰመኒ ግን፣ ከሀገሩ ሞግዚቷ የመረራቸው ቤተሰቦቿ ጋር፣ በዚያ ሰሞኑ የጀልባዎች ጉዞ፣ ወደ ጎረቤት ሀገር ከተሰደደች በኋላ፣ አሁን አውሮፓ ትገኛለች። የምትናፍቅ እናቷን ግን ዛሬም አላገኘችም !

______________***__________



# እናቴን ለመቅበር



አንድን ሕዝብ ለመግዛት፣ ዓይነተኛው ጥበብ፣
"መበተን፣ማራራቅ፣ ግንኙነቱን ማጥበብ!"
ነው አሉ ሲታውቁን፣ ያጠኑ ሥነ-ሕዝብ።

ከፋፍሎ ለመግዛት፣ ለገዥ እንዲያመች፣
ዕድሞ፣ ወሰን፣ አጥር፣ ያበጃል ሳይሰለች።

እናትን ከልጅዋ፣ ሳትወድ ይነጥላል፣
አንድ ላይ ካሉማ፣ ራሱም ይደግማል!

ስለዚህኮ ነው፣ ይሰፍ ፈቃድ ጠፍቶ፣
የማያፈናፍን፣ የውስጥ ደንብ ሠርቶ፣
ከርችሞ ወጥሮ፣ በሮቹን ዘጋግቶ፣
ፋሽስት የሚያስጨንቅ፣ ሕዝቦችን በላልቶ!